ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ

84ኛ ዓመት ቁጥር 065 ኅዳር 5 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# “የኮሪደር ልማት ዋነኛ ግብ ለትውልድ የተሻለ ከተማና ሀገር መገንባት ነው”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)



**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኮሪደር ልማት ሥራ ዋነኛ ግብ ለትውልድ የተሻለ ከተማና ሀገር መገንባት ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በአዲስ አበባ እየተከናወነ ያለውን ሁለተኛ ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ሥራ አፈፃፀም ገምግመዋል።

በግምገማ መድረኩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤን ጨምሮ የኮሪደር ልማት ሥራዎችን የሚያስተባብሩ የከተማዋ ከፍተኛ አመራሮች ተሳትፈዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚሁ ጊዜ እንዳሉት የኮሪደር ልማት ዋነኛ ግብ የተሻለ ከተማና ሀገርን ለትውልድ መገንባት መሆኑን ተናግረው፤ ትውልዱን ለከተሜነት እድገት ማዘጋጀት ስለመሆኑም ጨምረው ገልጸዋል።

ከተሜነት በፍጥነት እያደገ መሆኑን የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከዚህ አኳያ ትውልዱ አሁን የሚገነቡ መሠረተ ልማቶችን ጠብቆ በአግባቡ እንዲጠቀም ከወዲሁ መሥራት እንደሚገባም ነው ያነሱት።

የኮሪደር ልማት ሥራዎች የከተማዋ አመራሮች የሕዝብን ችግር ቀረብ ብለው እንዲመለከቱና ሰው ተኮር በሆነ አግባብ ለመፍትሄው እንዲሠሩ እድል የፈጠረ መሆኑንም ነው ያብራሩት።

ከተማና ሀገርን የመገንባቱ ሥራ በአንድ ጊዜ ተከናውኖ የማይጠናቀቅና በትውልድ ቅብብሎሽ የሚከናወን መሆኑንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

አሁን ላይ የሚከናወኑ ሥራዎች ኢትዮጵያ በቀጣይ ለመድረስ ላቀደችው የእድገት ርዕይ መሠረት የሚጥሉ መሆናቸውን ገልጸውም፤ ሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ሥራ በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑንም ተናግረዋል።

“የኮሪደር ልማት... ወደ ገጽ 8 ዞሯል







# ታሪክ ቀያሪዎቹ የቱሪዝም ዘርፉ ፍሬዎች

**ሳሙኤል ወንደሰን**

**ዜና ትንታኔ**



በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በበሰቃ ሀይቅ ላይ የተገነባውን “ቤኑና መንደር”ን መርቀው ከፍተዋል። በመዲናዋ በገበታ ለሸገር፣ በክልሎች ደግሞ በገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች ታሪክ ቀያሪ የቱሪዝም ልማት ሥራዎች ተከናውነው ለአገልግሎት በቅተዋል።

እነዚህ የቱሪስት መዳረሻ ፕሮጀክቶች ለቱሪዝም ዘርፉ እድገት ምን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ? ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆንስ ምን መደረግ ይኖርበታል? በሚሉና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ የዘርፉ ባለሙያዎች ሙያዊ ሃሳባቸውን አጋርተውናል።

ከፍተኛ የቱሪዝም ባለሙያው አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በአስደናቂ ታሪኳ፣ በተለያዩ መልከዓ ምድሮች እና ህያው ባህሏ የጉዞ መዳረሻ ሆና ይበልጥ እንድትቀጥል በአሁኑ ጊዜ በቱሪዝም መሠረተ ልማት እየታደሰች ትገኛለች። የገበታ ለሸገር፣ ገበታ ለሀገር፣ ገበታ ለትውልድ ፕሮጀክቶች የኢትዮጵያን የቱሪዝም ገጽታን በመሠረታዊነት እየቀየሩ ናቸው። ከገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች መካከልም ሀላላ ኬላ፣ ጨበራ ጩርጩራ፣ ወንጪ እና ጎርጎራ ይገኙበታል፡፡

እነዚህ ፕሮጀክቶች ከቢሮ ወደ ከተማ፣ ከከተማ ወደ ሀገር እየሰፉ፣ ከመሀል ሀገር ራቅ ያሉ የመስህብ ሥፍራዎች፣ መልከዓ ምድሮች እና ፓርኮችን በመሠረተ ልማቶች

ታሪክ ቀያሪዎቹ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



## “የኢትዮጵያ የመልማት እጣ ፈንታ የሚወሰነው በዓባይ ተፋሰስ ወንዞቻችን ነው”

- ፕሮፌሰር መኮንን አያና የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የውሃ ምህንድስና ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ

8





## በተኪ ሕክምና ግብዓት አቅርቦት ከ50 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪን ማስቀረት ተችሏል

- የሀገር ውስጥ የመድሃኒትና የህክምና መገልገያ አቅርቦት ሽፋኑ 36 በመቶ ደርሷል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በ2017 በጀት ዓመት መጀመሪያው ሩብ ዓመት በሀገር ውስጥ ሕክምና ግብዓት የምርት አቅርቦት ከ50 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ወጪን ማስቀረት መቻሉን የፕላንና ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ። የሀገር ውስጥ የመድሃኒትና የህክምና መገልገያ አቅርቦት ሽፋኑ 36 በመቶ መድረሱም ተጠቁሟል፡፡

በፕላንና ልማት ሚኒስቴር የኢኮኖሚ ትንተና እና ፖሊሲ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሀብታሙ አስፋው እንደገለጹት፤ በ2017 በጀት የመጀመሪያ ሶስት ወራት የሕክምና ግብዓት የምርት አቅርቦቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካት እና ተደራሽነቱን ለማስፋፋት በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሶስት ወራት የሀገር ውስጥ ሕክምና ግብዓት የምርት አቅርቦት በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት ከ50 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ወጪን ማስቀረት መቻሉን አመልክተው፤ ከውጭ የገባው የመድሃኒት እና የህክምና መገልገያ ቁሳቁስ መቀነሱንም አስታውቀዋል፡፡

ከዚህ በፊት በሀገር ውስጥ የህክምና ግብዓት አምራቾች የሚመረተው የመድሃኒትና የህክምና መገልገያ አቅርቦት ስምንት በመቶ ብቻ ሽፋን እንደነበረው ገልጸው፤ በ2017 በጀት የመጀመሪያ ሶስት ወራት የመድሃኒትና የህክምና መገልገያ አቅርቦት ሽፋኑን ወደ 36 በመቶ ማሳደግ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል በሩብ ዓመቱ ምርትን በሀገር ውስጥ በመተካት በፓስታና በመኮረኒ 115 ሚሊዮን ዶላር፣ ከምግብ ዘይት 80 ሚሊዮን ዶላር፣ ከብቅል 63 ሚሊዮን ዶላር ማዳን መቻሉን አስረድተዋል፡፡

በአጠቃላይ በሩብ ዓመቱ ከውጭ የገቡት የምግብና መጠጥ ምርቶች ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ44 በመቶ እንደሚቀንስ አመላክተዋል፡፡

የጫማ የውጭ ምንዛሬን በሚመለከት 51 ሚሊዮን ዶላር ማዳን የተቻለ ሲሆን፤ ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ25 ነጥብ 63 ሚሊዮን ዶላር ከፍ እንደሚል አብራርተዋል፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ተግባራዊ መደረጉ ለተኪ ምርት የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ በማስቀረት ምርትን በሀገር ውስጥ ለመተካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

# ጠቃሚ ሃሳቦችን በረቂቅ አዋጁ የማካተት ሥራ ይሠራል

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- የሪል ስቴት ልማትና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይትና ግመታ ረቂቅ አዋጅ ላይ ገዥ እና ጠቃሚ የሆኑ ሃሳቦችን በማካተት አዋጁ እንዲጸድቅ የማድረግ ሥራ እንደሚሠራ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሪል ስቴት ልማትና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይትና ግመታ ረቂቅ አዋጅ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተወያይቷል።

በውይይቱ ወቅት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ሄለን ደበበ፤ የሀገር ግንባታ ሊሳካ የሚችለው ሁሉም አካል በነቂስ ሲሳተፍ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

በአዋጁ ላይ ለወደፊትም ማሻሻያዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ያመላከቱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ አዋጁ መርቀቅ የጀመረው ረጅም ጊዜ ቢሆንም አሁን ላይ ያሉ መሠረታዊ ለውጦችንና ማሻሻያዎችን ግምት ውስጥ ያስገባ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፤ በኢትዮጵያ የቤቶች ዘርፍ የአቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠን ችግሮች ያሉበት እንደሆነና ችግሩ ጥልቅ በመሆኑ ከሀገር ውስጥ አልሚዎች በተጨማሪ የውጭ ባለሀብቶች ወደሀገር ውስጥ በመምጣት በቤት ልማት ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ እሸቱ ተመስገን (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በሪል ስቴት ልማት ዘርፍ ላይ የሚታየውን የፋይናንስ ክፍተት ለመሙላት ከተናጠል እንቅስቃሴ ይልቅ በጋራ በመሆን ለቤቶች ልማት ብድር የሚሰጡ ባንኮችን (mortgage bank) ለመመሥረት የሚያስችሉ አሠራሮች ሊኖሩ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

ምክትል ሰብሳቢው እንዳሉት፤ ከመድረኩ ለአዋጁ ውጤታማነት ግብዓት የሚሆኑ ሃሳቦች እንደተነሱና ረቂቅ አዋጁ ረጅም ጊዜ የሚያገለግል እንዲሆን ተጨማሪ አስተያየቶችን በጽሁፍ ማድረስ እንደሚቻል ገልጸው፤ ዘርፉን ለማሳደግ በዘርፉ ላይ የሚገኙ ተዋናዮች በጋራ መሥራት እንዳለባቸውም ጠቁመዋል።

የረቂቅ አዋጁ አስፈላጊነትም የማይንቀሳቀስ ንብረት ግመታ ሥርዓትን ዘመናዊና በመረጃ የተደገፈ ለማድረግ፣ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመገንባት፣ የሪል ስቴት ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፣ ለዜጎች የቤት አቅርቦት እንዲሻሻል ለማድረግ እንዲሁም ልማቱና ግብይቱ እንዲቀላጠፍ ለማድረግ መሆኑን ተነግሯል፡፡

በሪል ስቴት ልማት ዘርፍ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የቅድሚያ ሽያጭ የሚፈቀድ ሲሆን ይህም ለውጭ አልሚዎች የተከለከለ እንደሆነና በዝግ የባንክ ደብተር ተከፍቶ የሚቀመጥ ሲሆን፤ እንደአስፈላጊነቱ የሚለቀቅ እንደሆነ በረቂቅ አዋጁ ተመላክቷል፡፡

በረቂቅ አዋጁ መሠረትም ለሪል ስቴት አልሚዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፣ የቦታና የተናጠል ይዞታ ማረጋገጫ አሰጣጥ፣ የሪል ስቴት አልሚዎችና የቤት ገዥዎች ግዴታ፣ እንዲሁም ዋስትናንና ድጋፍ መስጠትን ያጠቃልላል፡፡

በሌላ በኩል ረቂቅ አዋጁ ያስፈለገው የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይትና ግመታ አስፈላጊነት የፋይናንስ ተደራሽነትን ለማመቻቸት፣ የገበያ ግልጸኝነትን ለመፍጠር፣ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፣ ሀብት ለመፍጠር፣ የከተሞችን ገቢና ልማት ለማሳደግ እንደሚያስችል ተመላክቷል፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት ግመታው በመደበኛነት በየአምስት ዓመቱ እንደሚካሄድ የተገለጸ ሲሆን፤ ይህም ለንብረት ግብር፣ ለሽያጭና ግዥ፣ ለባንክ ብድር ማስያዣ፣ ለፍርድ ቤት ክርክር፣ ለውርስ፣ ለኢንሹራንስ፣ ለኪራይና ለሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች እንደሚያገለግል በረቂቅ አዋጁ ተጠቅሷል፡፡

በውይይቱ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት ረቂቅ አዋጁን በሚመለከት አስተያየትና ጥያቄዎችን ያነሱ ሲሆን፤ በዘርፉ ላይ የፋይናንስ፣ የመሬት፣ የቴክኖሎጂ አቅርቦት እንደሚያስፈልግ አንስተው፤ በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ሄለን ደበበ አማካኝነት ምላሽ ተሰጥቷቸዋል።

በውይይቱ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር የሥራ ኃላፊዎች ፣ከኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማህበር፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ ቲንክታንክ ቡድን እና ሌሎችም በዘርፉ የሚመለከታቸው አካላት ተገኝተዋል።

# ኢትዮጵያ በማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ያላት ተሞክሮ የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ያደርጋታል

**ተስፋ ፈሩ**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ያላት ተሞክሮ የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት እንደሚያደርጋት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ገለጹ፡፡

የደቡብ ሱዳን ከፍተኛ ሥራ ኃላፊዎች የተካተቱበት ልዑክ በሃዋሳ ከተማ እና በድሬዳዋ አስተዳደር በመገኘት የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች በኢትዮጵያ ያላቸውን ተሞክሮ ተመልክቷል፡፡

በፕሮግራሙ ማጠቃለያ ላይ ንግግር ያደረጉት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር)፤ ኢትዮጵያ በማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ያላት ተሞክሮ እንደ ጥሩ ትምህርት ተወስዶ ለሌላ ሀገር ማካፈላችን፣ ሀገራችን የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት የምትሆን ሀገር መሆኗን ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራም ረጅም ዕድሜ ያለው ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ በኢትዮጵያ ከ1950ዎቹ ጀምሮ መንግሥት ለችግር የታጋለጡ ወገኖችን ለመርዳት የራሱን ፕሮግራም ቀርጾ ይንቀሳቀስ ነበር፡፡ በ2007 ዓ.ም. የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ መውጣቱን ተከትሎ ስትራቴጂ ወጥቶለት ፕሮግራሞቹ በተደራጀ መንገድ እንዲከናወኑ ሲደረግ ቆይቷል ነው ያሉት፡፡

በሴፍቲኔት ፕሮግራም ደግሞ ሰዎች የገንዘብና የምግብ ርዳታ የሚያገኙበት ብቻ ሳይሆን ሰዎች ሠርተው መለወጥ የሚችሉበት ፕሮግራም መሆን አለበት ተብሎ ሰዎች ባገኙት ትንሽ ድጋፍ የራሳቸውን ሥራ ሠርተው ከተረጅነት እንዲወጡ ምርታማ ፕሮግራም መቀረጹንም ገልጸዋል፡፡

ፕሮግራሙ ሲጀምር በገጠር ያሉ ለችግር የተጋለጡ ወገኖችን ለመደገፍ እንደነበር ጠቁመው፤ በገጠሩ ላይ የተመዘገበውን ውጤት በማየት ከግብርና ሚኒስቴር እና ከከተማ መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት የከተማ የሴፍቲኔት ፕሮግራም መጀመሩን አመላክተዋል።

እንደ ኢትዮጵያ ከሌሎች የምንማረው ነገር እንዲሁም ለሌሎችም የምንሰጣቸው ነገር አለ ያሉት ኤርጎጌ (ዶ/ር)፤ ማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን እና የመንግሥት ለመንግስት ግንኙነትን ያጠናክራሉ ብለን እናምናለን፡፡ ከወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ጋር በተያያዘ በጅቡቲ የጀመርነው ሥራ አለ፡ ፡ አንዱ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት የምንሰጠው የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት ነው። ይህን ሥራ ወደ ደቡብ ሱዳን እና ወደ ሌሎች ጎረቤት ሀገራትም የምንወስደው ይሆናል ብለዋል፡፡

የደቡብ ሱዳን ጀንደር፣ ህጻናት እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር አያ ቤንጃሚን በበኩላቸው፤ ልዑካቸው የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች በኢትዮጵያ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ በመመልከት ደቡብ ሱዳን ከተሞክሮው ልምድ መውሰድ የምትችልበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ ቆይታ ማድረጉን ጠቁመው፤ በኢትዮጵያ በተለያዩ ሱሶች ተጠምደው ወደ ጎዳና የሚወጡ ዜጎችን አንስቶ በማገገሚያ ማዕከላት ውስጥ እንዲያልፉ በማድረግ መደበኛ ሕይወትን እንዲቀላቀሉ የሚደረግበት ሂደት እንዳስደነቃቸውና ሀገራቸው ከዚህ ተሞክሮ ትምህርት እንደምትወስድ ተናግረዋል፡፡

በደቡብ ሱዳን መንግሥት በማህበራዊ ጥበቃዎች ላይ በጀት በመመደብ የሚያደርገው አስተዋጽኦ ባለመኖሩ እንደ ዓለም ባንክ ባሉ አጋሮች በሚመድቡት በጀት እንደሚሠራ ጠቁመው፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በራሱ አቅም ለዜጎች የሚያደርገው አስተዋጽኦ መኖሩ ትልቅ ተሞክሮ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ጤንነቱ የተጠበቀ ማህበረሰብ ከሌለ አምራች ማህበረሰብ አይኖርም ያሉት ሚኒስትሯ፤ በደቡብ ሱዳን የጤና መድህን ዋስትትና ፕሮግራም እንደሌለ እና በተለይም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የጤና አገልግሎትን ተደራሽ ከማድረግ አንጻር የማህበረሰብ ጤና ኢንሹራንስ ብዙ ጥቅም እንደሚሰጥ ተገንዝበናል ነው ያሉት።

# ኢትዮጵያና ሩሲያ ኢኮኖሚያዊ አጋርነታቸውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር እንደሚሠሩ አስታወቁ

## • ኢትዮጵያ በብሪክስ አባልነት መካተቷ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት የበለጠ ያጠናክራል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያና ሩሲያ ኢኮኖሚያዊ አጋርነታቸውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር እንደሚሠሩ ተገለጸ፡፡ በተለያዩ የቢዝነስ መስኮች ላይ ትኩረት ያደረገው የኢትዮ-ሩሲያ ቢዝነስ ፎረም ትናንት በአዲስ አበባ ተካሂዷል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ በቢዝነስ ፎረሙ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ ሁለቱ ሀገራት ከ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የነበራቸውን ጥልቅ ታሪካዊ ግንኙነት እያጠናከሩ መምጣታቸውን ጠቅሰዋል፡፡ ሁለቱ ሀገራት በሁለትዮሽ የንግድ ግንኙነት ላይ ያላቸውን አቅም በማጉላት ኢኮኖሚያዊ አጋርነታቸውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር እንደሚሠሩም ገልጸዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት የሩሲያ ኢንቨስተሮች ማዕድንና ማኑፋክቸሪንግን ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች ኢንቨስት እያደረጉ እንዳለ አምባሳደር ምስጋኑ አመላክተዋል፡፡

በንግዱ ዘርፍ ኢትዮጵያ እንደ ቡና፣ አትክልት፣ ጥራጥሬና የቅባት እህሎችን ወደ ሩሲያ ስትልክ፤ በአንጻሩ የግብርና ማሽኖች፣ ብረት፣ ስንዴ፣ የምግብ ዘይትንና ሌሎች ምርቶችን ከሩሲያ እንደምትቀበልና ይህን የንግድ ልውውጥ ለማሳደግም የተቀናጀ ጥረት እንደሚጠይቅ ገልጸዋል፡፡



ፎቶ ዳኜ አበራ

ሚኒስትር ዴኤታው፤ ኢትዮጵያ የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጣና አባልነትን እና የኢንቨስትመንት ሁኔታዎችን አስመልክቶ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን ማድረጓን ገልጸዋል፡፡ በቅርቡ የተከፈቱትን የቴሌኮም እና የፋይናንስ ዘርፍ እድሎችን ጨምሮ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ሳቢ የኢንቨስትመንት መዳረሻ እንዳደረጓትም ተናግረዋል፡፡ በዚህም የሩስያ ኩባንያዎች በተለያዩ የጤና አጠባበቅ፣ ፋርማሲዩቲካል፣ አይሲቲ፣ ግብርና፣ አግሮ ፕሮሰሲንግ፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ ቆዳ ውጤቶችና ታዳሽ ኢነርጂ ላይ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

አምባሳደር ምስጋኑ የሩስያ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ ያሉትን በርካታ እድሎች እንዲጠቀሙ በማበረታታት፤ ፎረሙም አዲስ አጋርነት እንደሚፈጥር እና በኢትዮጵያና በሩሲያ ሕዝቦች መካከል ያለውን የቆየ ግንኙነት እንደሚያጠናክር ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።

ሩሲያ እና ኢትዮጵያ እንደ ብሪክስ ቤተሰብ አባልነታቸው፤ ኢትዮጵያ የሩሲያ የኢንቨስትመንት እና የንግድ መዳረሻ በመሆን ረጅም ጊዜ ያስቆጠረውን የሁለትዮሽ ግንኙነት እንዲጠናከር ቁርጠኛ መሆኗን ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ የሩሲያ ፌዴሬሽን አምባሳደር ኢቭጌኒ ተርኪሂን በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ እና ሩሲያ በተለያዩ ዘርፎች የላቀ የሁለትዮሽ ግንኙነት እንዳላቸውና በተለያዩ ዘርፎች ያለውን ግንኙነት የበለጠ ለማሳደግ እየሠሩ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ለረጅም ዓመታት የቆየው የሁለቱ ሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እያደገ መምጣቱ ጠንካራ የንግድ እና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ለመፍጠር ከፍተኛ ፍላጎት ማሳደሩን አስታውቀዋል፡፡

የኢትዮጵያ ባላት ምቹ የንግድ ሁኔታ ከፍተኛ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መኖሩን ጠቅሰው፤ የሩሲያ ኩባንያዎችም ካፒታላቸውን በማውጣት በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች በመሳተፍ ላይ እንዳሉ ገልጸዋል፡፡ በቀጣይም የሩሲያ ኩባንያዎች በተለያዩ ዘርፎች መዋዕለ ንዋያቸውን በኢትዮጵያ ለማፍሰስ ፍላጎት እንዳላቸው ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ሰፊ የለውጥ ሥራዎችን እየሠራ እንዳለና ይህም ተስፋ ሰጪ ውጤት እያስመዘገበ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ያላት ስትራቴጅካዊ አቋም፤ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እና በብሪክስ አባል መካተቷ አሁን ያለውን ግንኙነት የበለጠ ያጠናክራል ነው ያሉት።



መቅደስ ዳባ (ዶ/ር)



መሳይ ሃይሉ (ዶ/ር)



ኖንህላንህላ ድላሚኒ(ዶ/ር)

# ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ የጤና መስፈርቶችን በማሟላት በድንገተኛ አደጋ ዝግጁነት ትልቅ ለውጥ አሳይታለች

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ የጤና መስፈርቶችን በማሟላት በተለይም በድንገተኛ አደጋ ዝግጁነት ፣ ቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ምላሽ አቅም ላይ ትልቅ ለውጥ ማሳየቷን የኢትዮጵያ ጤና ሚኒስትር ዶክተር መቅደስ ዳባ ገለጹ፡፡

በዓለም የጤና ድርጅትና በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የተዘጋጀ ለሶስት ቀናት የሚቆይ ዓለም አቀፍ የድንገተኛ አደጋ ሥራዎች ሥልጠና (GEOCX 2024) በትናትናው ዕለት መሰጠት ጀምሯል፡፡

ጤና ሚኒስትር ዶክተር መቅደስ ዳባ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ የጤና መስፈርቶችን በማሟላት በተለይም በድንገተኛ አደጋ ዝግጁነት ፣ ቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ምላሽ አቅም ትልቅ ለውጥ አሳይታለች።

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ በጤናው ዘርፍ ያላት አቅምም ሀገራዊ የህብረተሰብ ጤና ጂኖሚክ ላብራቶሪ እና በመላ ሀገሪቱ የተስፋፋ የላብራቶሪ ንብረቶችን ያጠቃልላል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ይህን ዓለም አቀፍ ሥልጠና ማዘጋጀቷ ያላትን አቅም ለመገምገም፣ ያሉትን ክፍተቶች ለማሻሻል እንዲሁም የምላሽ ስልቶችን የማጥራት እድል ይሰጣል ያሉት ሚኒስትሯ፤ እንደዚህ አይነት ሥልጠናዎች በጤናው ዘርፍ ያሉ ትብብሮችን እንደሚጨምሩ ተናግረዋል፡፡ እንዲሁም በጋራ በመሥራት የዓለም አቀፍ የጤና ስጋቶች መከላከል እንደሚቻልም ገልጸዋል፡፡

እንደ ዶክተር መቅደስ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አገልግሎት ፣ በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም እንዲሁም የቤተሰብ ጤናን በማጠናከር ለገጠሩ ማህበረሰብ ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ ተችሏል። ሆኖም እንደ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና ሊከሰቱ የሚችሉ ሌሎች ድንገተኛ የጤና አደጋዎችን ለመቆጣጠር ጠንካራ የጤና ሥርዓት መዘርጋት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ የጤና ጥበቃን ለማጠናከር ያላት ቁርጠኝነት የበሽታ ክትትልን በዲጂታል እስከ ማድረግ ድረስ ይዘልቃል፡፡ ይህም የህብረተሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎችን በበለጠ ፍጥነት እና ትክክለኛ ምላሽ እንድንሰጥ ያስችለናል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር መሳይ ኃይሉ (ዶ/ር)፤ እነዚህ የመሰሉ ዓለም አቀፍ ሥልጠናዎች ለወደፊት የህብረተሰብ ጤና ስጋቶች ውጤታማ ምላሽ ለመስጠት የጋራ አቅምን የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያም ለህብረተሰብ ጤና ደህንነት ያላትን ቁርጠኝነት በትብብር፣ በሥልጠና እና የአደጋ ጊዜ ዝግጁነት እያሳየች ትገኛለች ብለዋል፡፡

የዓለም ጤና ድርጅት ተወካይ ኖንህላንህላ ድላሚኒ (ዶ/ር) በበኩላቸው ፣ ኢትዮጵያ የዚህ ሥልጠና አዘጋጅ እንደመሆኗ መጠን የምትጫወተው ሚና ለዓለም አቀፍ የህብረተሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎችን ለመመከት ያላትን ቁርጠኝነት ያሳያል። የ GEOCX 2024 ሥልጠና ለአባላት ሀገራት የአደጋ ጊዜ ዝግጁነት እና የምላሽ ሥርዓቶቻቸውን እንዲያጠናክሩ እድል የሚፈጥር ነው ብለዋል።



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

# የካፒታል ገበያ ያለንን ሀብት በማስተባበር ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማፋጠን ያግዛል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የካፒታል ገበያ ወደ ሥራ መግባት ያለንን ሀብትና እውቀት በማስተባበር የተጀመረውን ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማፋጠን እንደሚያግዝ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዢ አቶ ማሞ ምህረቱ ገለጹ፡፡ የመጀመሪያው የካፒታል ገበያ ጉባዔ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ተወካዮች እና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በአዲስ አበባ ትናንት መካሄድ ጀምሯል፡፡

አቶ ማሞ ምህረቱ በመድረኩ ላይ ባደረጉት ንግግር እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት በሁሉም ፈጣን እድገት አስመዝግባለች፡፡ ወደተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርም ትግበራም ገብታለች፡፡

የካፒታል ገበያው የተጀመረውን የኢትዮጵያን ማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ለመደገፍ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዘርፉ ብቁ የሰው ኃይል ማፍራትና በጋራ መሥራት ከተቻለ ጠንካራ ኢኮኖሚን መገንባት እንደሚቻል ገልጸዋል።

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ መንግሥት በፋይናንስ ዘርፉ ያሉ ተግዳሮቶችን የሚቀርፉ አዳዲስ አሠራሮችን እየተገበረ መሆኑን ገልጸዋል።

የካፒታል ገበያ ምህዳሩን በማስፋት በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ የግሉን ዘርፍ ጨምሮ አነስተኛና መካከለኛ ተቋማትን መደገፍ፣ ለዜጎች የሥራ እድል መፍጠርና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በዘላቂ መሠረት ላይ መገንባት የሚያስችል ነው ብለዋል።

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በፈጣን እድገት ላይ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ በቅርቡ የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ደግሞ ይህንን የሚደግፍ መሆኑን ገልጸዋል። በተጨማሪም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስመንትን ለመሳብና ሰፊ የሥራ እድል በመፍጠር በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል ብለዋል፡፡

እንደዚህ አይነት ጉባዔዎችም ልምድን ለመጋራትና ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓት እንዲኖር ሊወሰዱ ስለሚገባው ርምጃዎች ትልቀ ግብዓት ለመሰብሰብ የሚያስችሉ መሆናቸውን ሚኒስትር ዴኤታው ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ሃና ተልህኩ፤ በኢትዮጵያ የፋይናንስ ሥርዓት ውስጥ የተረጋጋና ዘላቂ ኢኮኖሚን ለመገንባት የካፒታል ገበያ ወሳኝ ነው ብለዋል።

የካፒታል ገበያ ምህዳሩን አካታች፣ ንቁ፣ ችግሮችን መቋቋም የሚችል ሆኖ ከተገነባ የፋይናንስ ሥርዓቱን ቀላል ማድረግና ሁሉንም ዜጎች ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚቻል ጠቁመዋል።

በጉባዔውም ባለሥልጣኑ እስካሁን ያከናወናቸውን ሥራዎች ለሕዝብ ለማስተዋወቅ፣ በሂደቱ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችንና መልካም እድሎች ላይ ምክክር እንደሚደረግ ገልጸው፤ ለኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ጠንካራ መሠረት ለመጣል ሲዘጋጅ የቆየው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለሕዝብ ሽያጭ ማቅረብና የግብይት መመሪያም ይፋ እንደሚደረግ አመላክተዋል፡፡

ጉባዔው "ቀጣይነት ያለው መንገድን ማበጀት" በሚል መሪ ቃል እየተከናወነ ሲሆን፣ ለሦስት ተከታታይ ቀናት እንደሚቀጥል የወጣው መርሃግብር ያስረዳል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የበለጸጉ ሀገራት በቁርጠኝነት ሊሠሩ ይገባል!

የአየር ንብረት ለውጥ የዓለማችንን ተፈጥሯዊ አካባቢን በከፍተኛ ሁኔታ እየተፈታተኑ ካሉ ችግሮች በዋነኛነት የሚጠቀስ ነው። የችግሩ ቀዳሚ ባለቤቶች የበለጸጉት/ ያደጉት ሀገራት ቢሆኑም ፤ ጫናው ግን ከፍ ያለ ዋጋ እያስከፈላቸው ያሉት ድሃዎቹ የዓለም ሀገራት እንደሆነ መረጃዎች በስፋት ያትታሉ።

አሁን ላይ ከመቼውም ጊዜ በላይ የበለጸጉት ሀገራት ኃላፊነት በማይሰማው መልኩ ወደ አየር ከሚለቋቸው በካይ ጋዞች ጋር በተያያዘ የዓለማችን የተፈጥሮ አካባቢ በብዙ መልኩ እየጎዳ ነው፤ የከባቢ አየር ሙቀት መጨመርም ሆነ ፤ እሱን ተከትሎ እየተፈጠረ ላለው የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት በዋነኛነት የሚጠቀስ ነው።

በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የሚስተዋሉት የአየር ንብረት ለውጦች ፤ ጎርፍ ፣ አውሎ ንፋስ ፣ የበረሃማነት መስፋፋት ፣ የውቅያኖስ የውሃ መጠን መጨመር ፣ የመሬት መንሸራተት ..ወዘተ ከዚሁ ችግር ጋር በቀጥታ ተያይዞ ፣ፈጣን ዓለም አቀፍ ምላሽ ካላገኘ ወደ ከፋ ደረጃ ሊሻገር እንደሚችል ይታመናል።

በሽታ አማጭ ቫይረሶች መድሃኒቶችን መልመድ ፣ አዳዲስ የበሽታ ዓይነቶች መከሰት ፤ የሰዎች በሽታን የመቋቋም አቅም እየቀነሰ መምጣት ፤ በመሬት ላይም ሆነ በባህር ውስጥ በሚኖሩ ፍጥረታት ላይ እየደረሰ ያለው ጥፋት ፤ የተፈጥሮ ሚዛንን በማዛባት ሊያስከትል የሚችለው አደጋም አስጊ ስለመሆኑ እየተነገረ ነው።

አደጋው በተለይም ችግሩን በመፍጠር ሂደት ይህ ነው የሚባል አስተዋጽኦ ለሌላቸው ድሃ እና ኋላቀር ሀገራት "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" በመሆን ፤ የዜጎቻቸውን የለት ተዕለት ሕይወት የበለጠ እያወሳሰበው ፤ ኑሯቸውን እያከበደው፤ ተስፋ የሚያደርጓቸውን ነገዎች እያደበዘዘባቸው ይገኛል።

የችግሩን አሳሳቢነት በተመለከተ አንቱታ ያተረፉ በዘርፉ ምርምር የሚያካሂዱ ተመራማሪዎች ፣ በመስኩ የተሠማሩ ባለሙያዎች እና የችግሩ ሰለባ እየሆኑ ያሉ ሀገራት መንግሥታት መግለጫዎች እና ማሳሰቢያዎች ቢያወጡም ፤ የችግሩ ዋነኛ ባለቤት ከሆኑት የበለጸጉት ሀገራት ተገቢውን ምላሽ ሊያገኙ አልቻሉም።

ሀገራቱ ለችግሩ የሚጠበቅባቸውን ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ፤ አዘናጊ ምክንያቶችን በመስጠት ችግሩ ከትናንት ዛሬ ለመላው ዓለም የበለጠ ስጋት ወደ ሚሆንበት ደረጃ እንዲሻገር አስቻይ ሁኔታዎችን እየፈጠሩ ነው። በዚህም የድሃ እና የኋላቀር ሀገራት ሕዝቦችን ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍሉ እያስገደዷቸው ነው።

ስለፍትሃዊነት ብዙ በሚዜምበት አሁነኛው ዓለም ፤ የበለጸገው ዓለም በብልጽግና ላይ ብልጽግና እየደረበ ፤ እርሱ ለሚፈጥራቸው ችግሮች ዓለም ያልተገባ ዋጋ ሊከፍል አይገባም ፤ ይህ ከራስ ወዳድነት በላይ የሆነ ፤ ከዓለም አቀፍም ሆነ ከሞራል ሕግ አኳያ ፣ አጠቃላይ በሆነው የተፈጥሮ አካባቢና የሰው ልጅ ላይ የሚደረግ ወንጀል ነው።

የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የእያንዳንዱን ቤት እያንኳኳ ላለው ለዚህ ችግር የበለጸጉት ሀገራት "ጆሮ ዳባ ልበስ" ማለታቸው፤ በየጊዜው ከችግሩ ጋር በተያያዘ የመፍትሄው አካል ለመሆን ለሚገቧቸው ቃላት ተፈጻሚነት ደንታ ቢስ መሆናቸው ፣ ነገ ላይ የታሪክ ተጠያቂ የሚያደርጋቸው ነው።

ሀገራቱ ዛሬ ለችግሩ የመፍትሄ አካል መሆን እየቻሉ ባልተገባ መንገድ ፈጥኖ መንቀሳቀስ ባለመቻላቸው ዓለም ዋጋ እየከፈለች ነው ፣ ችግሩ በተለይም በታዳጊ ሀገራት የሚኖሩ የዓለማችን ሕዝቦች ከድህነት እና ከኋላቀርነት ለመውጣት የሚያደርጉትን ትግል ክፉኛ እየተፈታተነው ነው።

የተፈጥሮ አካባቢን መንከባከብ እና መጠበቅ ከሁሉም በላይ የሰው ልጅ ኃላፊነት ነው ። ይህን ኃላፊነት ለመወጣት በተለይም የችግሩ ዋነኛ ባለቤት የሆኑት የበለጸጉት ሀገራት የማይተገበር ቃል ከመግባት ወጥተው ችግሩን ለዘለቄታው ለመፍታት ለሚደረገው ጥረት የሚጠበቅባቸውን ፈጥነው መወጣት ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ ደግሞ ነገን መጠበቅ ሳይሆን ዛሬ ላይ በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በግእዝ የጣልነውን - በጊዜ እናንሳው

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ታላቋ ኢትዮጵያ በትልቁ ሀምራዊ የጥበብ ዘርፏ ሥልጣኔ የተነቀሰበት የታላቅነት ዘመን እንደነበራት ለሁላችንም እሙን ነው። ላላመንን ምልክት ይሆን ዘንድ ደግሞ ርዝራዥም ይሁን በገፍ ዛሬም ድረስ በዓይኖቻችን የምንመለከታቸው ማሳያዎች እንዳሉን ማናችንም አንክደውም።

ከሞት ባህር ዳርቻ የቆመው የግእዝ ቋንቋም ሁሉን ሊነግረን የሚጠብቀው እኛኑ ነው። ይሁን እንጂ እሱ ያውቀናል እንጂ እኛ ስለማናውቀው ግድ አልሰጠንም። እነዚህን እውነታዎች ጥቁር ደም ያለው ሀበሻው ቢክድ እንኳን ነጩ ፈረንጅ በአሥር ጣቶቹ ይፈርምበታል። ዓለም በሙሉ በእግር ጣቱ ቆሞ ይሄንን ሀቅ ፍለጋ ላይ መሆኑንም አይስተውም። ዓይኖቹ በግእዝ ቋንቋ ላይ ናቸው። ምክንያቱም የታላቁ ሚስጢር ቁልፍ በግእዝ ፊደላት ተቀርጾ ብራናዎች ላይ ሰፍረዋልና፡፡

ብራናዎቹን ታቅፈናል። ለኛ የረከሰው ወርቅ ደግሞ ለእነርሱ የእስትንፋስ ያህል ነው። "በእጅ ያለ ወርቅ እንደመዳብ..." ብንል እንኳን ፈጽሞ አይገልጸንም። አሳዛኙ ነገር የኛ መጣል ብቻ አይደለም። እኛ ጋቢ በርዶን የነጮችን ነጠላ ፍለጋ በምንማስንበት ዘመን እነርሱ ደግሞ ወደኛ እየፈጠኑ፣ እየገሰገሱ መሆኑ እንጂ።

ታዲያ እኮ እኛን ፍለጋ አይደለም። የእኛን ፍለጋ ነው። የኛ የምንለው ግእዝ ሳይገባን እነሱ አሳምሮ ገብቷቸዋል። በገዛ ወርቃችን «እንቁልልጭ» ለመባልም ተቃርበናል። የጣልነውን ካላነሳን ግን መሃል ከተማ ላይ እንደነጋበት ጅብ መቅበዝበዛችን ነው፡፡

ከምድር አጽናፍ እስከ አጽናፍ፣ ከሰማይ ከዋክብት እስከ ጨረቃ፣ ከኪነ ጥበብ እስከ ኪነ ህንጻ፣ ከመድኃኒት እስከ ተፈጥሮ ምትሀት በግእዝ ተጽፎ የማይገኝ ዕውቀትና ጥበብ እንደሌለ ሁላችንም በልበሙሉነት እናወራለን። እስኪ ከተጻፈው? ተብለን ብንጠይቅ ግን የምናውቀው ምንም የለም።

ታዲያ «አለኝ! አለኝ!» ብለው ጉራ ቢቸረችሩ ምን ሊረባ? ለማንበብ የማንችለውን ግእዝ በጭንቅላት ተሸክመነው ብንዞር ከድካም በቀር ትርፉ ምንድነው? በድንገት ዓለምን ሙሉ ሊለውጥ የሚችል የግእዝ መጽሐፍ እጃችን ቢገባ አንብበን ምን እንደሆነ ለመለየት የማንችል ነን። ተራው ግለሰብ ቀርቶ ስንቱን ተአምር ስለመሥራት የሚያስቡ አብዛኞዎቹ ሊቀ ምሁራኑም ከእጃቸው የገባውን ብራና ገልጦ ለመረዳት ተስኗቸው "ቄሱም ዝም፤ መጽሐፉም ዝም" ዓይነት ሆኖ ተፋጠዋል፡፡

ችግሩ የእነርሱ የመረዳት ችሎታ ስላነሰ አይደለም። ስንቱን የባዕድ ቋንቋ ፈትፍቶ የሚያበላን የትምህርት ሥርዓቱ ስለዚህ ቁምነገር ያለማለቱ ነው። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የሚታዩ ጥረቶች እንዳሉ ሆነው ። እንዲያም ሆኖ ጠብሰቅ ባለ የትምህርት ሥርዓት እስካልታቀፈ ድረስ በስንጥር ለኮፍ! ቢያደርጉት ተነስቶ እንደ ወፍ አይበርም።

ግእዝን እናንሳ ብለን ስንነሳ በመጀመሪያ ሊታየንና ቦታ ሊሰጠው የሚገባው በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ነው። በትምህርት የጣልነውን ነገር በምክርና ዝክር ልናመጣው አንችልም። በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ለምናደርገው ጉዞም መንገዱ ጥርጊያ ያሻዋል። እያንዳንዳችን ስለ ግእዝ ቋንቋ የያዝነውን አላግባብ የሆነ አመለካከትን ማስወገድ ግድ ይለናል፡፡

ዓላማው ለሀገር ትንሳኤ እንጂ ለፖለቲካ ፍጆታ ስንል አንድ ሰሞን ላይ ሆይ! ሆይ! ብለን «ሥራ ያውጣህ» የምንለው ጉዳይም አይደለም። ዛሬ ላይ ጀርመን በዩኒቨርሲቲዎቿ ግእዝን ታስተምራለች። የሚዘረፈው ቅኔያችን ብቻ ሳይሆን እኛ ጭምር ነን። እኛ ግን ይኸው በገዛ ራሳችን ላይ እንቀናለን። እነርሱ ማስተማር ሲጀምሩ ቃል ያልወጣው አንዳንዱ፤ ግእዝ በዩኒቨርሲቲዎቻችን ሊጀመር ነው ሲባል"...የሚያምረው በባለቤቱ አፍ ሲነገር ነው...ግእዝን ለባለቤቱ ለቀቅ..." የሚሉትን እና መሰል ቃላትን ከማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ተመለከትኩ።

መጥበብን የምንወድ ብሄርና ሃይማኖት ላይ ሸነቆርነው እንጂ ግእዝ በትንሹ ከአክሱም፣ ከኩሽ...ምድር አልፎ እስከ ማያ ሥልጣኔ ድረስ የነበረ ቋንቋ ነው። እንኳንስ ኢትዮጵያን መላው አፍሪካን አልፎ እስከ መጓዝ ደርሷል። ይሁን እንጂ ደርሰን ለራሳችን ጠላት ራሳችን እንሆናለን። የኖህን መርከብ ሠርታ ግእዝን ከጥፋት ውሃ ያዳነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እንኳን የኔ ነው ብላ አታውቅም። ለዚህ አበርክቶዋ እውቅና ሰጥቶ ምስጋና ይገባታል፡፡

በትምህርቱ ሥርዓት ውስጥ መሠራት አለበት ስንል የተሠራና የታሰበ የለም ማለት አይደለም። ግን የተሞከረበት መንገድ መሠረቱ ሳይቆም በመሆኑ ተጨባጭ ለውጥ ለማየት አልተቻለም። ምስኪኑ ገበሬ ጠዋት በማለዳ ተነስቶ መሬቱን ሊያርስ ግርጌው ይወርዳል። እርፍና ማረሻውን ጨብጦ ይቆፍራል። በሬውን ጠምዶ መሬቱን ይገነድፋል። ሰርዶ መንቀሉን በጉልጓሎው መድከሙን ይያያዘዋል፡፡

ምንም አዝመራ ለማይታይበት መሬት ነጭ ላቡን ያንጠፈጥፋል። በነጋታውም እየሄደ ይህንኑ ግብሩን ይቀጥላል። ገበሬው ትርፉ ከሚዘራው ላይ ሆኖ ሳለ ስለምን ለመሬቱ ይዳክራል? ምክንያቱም መሬቱን በመንከባከብ ያፈሰሰው ላብና ድካሙ ሁሉ ለመሬቱ ብሎ ሳይሆን ገና ለሚዘራት ዘር ሲል ነው። መሬቱን ሳያለማ ዘር ቢዘራ ያለውንም ያጣል እንጂ በተስፋ የሚጠብቀው አዝመራ አይኖረውም።

ያ ሁሉ የምንናፍቀው ዕውቀትና ጥበብ ያረፈው በግእዝ መሬት ላይ እንደመሆኑ አስቀድመን ግእዝን እስካልጠበቅን የምንጠብቀው ሁሉ ከንቱ ምኞትና ተስፋ ነው። ያልመገቧትን ላም ወተት አምጪ አይሏትም። አርግተው ካልናጡት ወተት ውስጥም አይቤና ቅቤ አይወጡም። ታላቁ የአባቶች ጥበብ ላም አለኝ በሰማይ...የሆነብንም ለዚሁ ነው። አሁን ማሰብ ያለብን በአንድ ጀንበር በግእዝ ስለመጥለቅለቅ ሳይሆን አንድ ሁለት እያሉ የማይነቃነቅ መሠረት ስለማጽናት ነው። ሀሁ ተብሎ ፊደል ሳይቆጠር ቃል ልመስርት ማለት ዋጋ ቢስ ነው። ቃላትን ሳያውቁም ቅኔ ካልዘረፍኩ አይባልም።

ከጅምሩ በኬጂና አንደኛ ደረጃም ይሁን በሁለተኛ እናስተምር ብለን ብንጀምር አስተማሪው ማን ሊሆን ነው? መቼም የኔታና መሪጌታ ልንቀጥር አይሆንም። አጀማመራችን መሆን ያለበት የሚያስተምረውን ከማፍራት ነው። እንቅስቃሴውን ስንጀምር ግእዝ የራሱ የሆነ መንግሥታዊ ተቋም ሊኖረው ይገባል። አሊያ ግን ከሌላው ጋር አደባልቀን እንሂድበት ብንል ትርፉ ድካም ነው፡፡

በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ለመጀመር በታሰበው ዕቅድ ውስጥ ሃላፊነቱ የተተወው ሙሉ ለሙሉ ለራሳቸው ለዩኒቨርሲቲዎቹ በመሆኑ የቻሉት በራሳቸው መንገድ ጥቂት ጥረዋል። ሌላውም መንገዱ ጠፍቶት ይሁን ችላ ብሎት ከነአካቴው ትቶታል ፡፡ግእዝ እንዲሁ ለይስሙላ በራስ መንገድ የሚጀማመር ሳይሆን በዩኒቨርሲቲዎች በራሱ የትምህርት ክፍል የሚመራ፣ በሀገር ደረጃም ከላይ ሆኖ መንገዱን የሚቀይስ ተቋም ያስፈልገዋል። ምንም ስለቋንቋው የማያውቁቱ እንኳን ሰጥ ለጥ አድርገው የሚመሩትን ጉዳይ እኛ እንደምን ያቅተን።

በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ የጥንታዊቷ ኢትዮጵያ የታላቅነት ቁልፍ ያለው በግእዝ ስለመሆኑ እያስተማረ፤ ግእዝን ካሸሸው "እየው ግን አትብላው" ዓይነት አሳይቶ መንሳት ነው። ትንሳኤ ኢትዮጵያን ለማቆም የግእዝን ምርኩዝ መያዙ አማራጭ አናድርገው፡፡

የግእዝ ቋንቋ የትምህርት ሥርዓቱ ዋነኛ አጀንዳ መሆን አለበት ስንል ቋንቋውን ከመጥፋት አደጋ ለመታደግ? ወይንስ ለጥንቱ ትዝታና የኛ ስለመሆኑን ለዓለም ለማሳየት? ሁለቱም የእግረ መንገድ እንጂ ዋነኛ ዓላማዎቻችን ሆነው አይደለም። "ብልጥ ከሰው፣ ሞኝ ከራሱ ይማራል" ብለን ተርተን በዚህ ግን ከየትኛውም ለመማር የቻልን አይመስለኝም። ቆጭቶን ከውድቀታችን ለመማር አልተነሳንም።

እንግሊዝ ያን ሁሉ መጽሐፍቶቻችንን ስታግዝ፣ ጀርመን ቆማ በኛ ግእዝ ቅኔ ስትዘርፍ አይሞቀን! አይበርደን! ጆሮ ዳባ አልን። ለምንድነው ይህን ያህል የሚቋምጡት? ብለን እንኳን አንጠይቅም። ጀርመኖች ግእዝን ለማስተማር ሲነሱ ለቋንቋው ውለታ ለመዋል አይደለም። ደስ ስላላቸው ብቻ ከመሬት ተነስተው ከዚህ ሁሉ የዓለም ቋንቋ ግእዝን ሁለተኛቸው ለማድረግ ሲያስቡ አንድና አንድ በግእዝ ቋንቋ የተጻፈ ትልቅ የዓለም ሚስጢር በመኖሩ ነው።

ዓለም እንኳንስ ስለጨረቃና ክዋክብት ቀርቶ ስለምትኖርበት ምድር እንኳን በቅጡ ሳታውቅ በፊት የኛ አባቶች መንኩራኩር ሳይፈልጉ፣ ሳተላይት ሳያስወነጭፉ እዚህ ቁጭ ብለው ህዋ ላይ ነበሩ። ዓለም በሽታ ምን እንደሆነ ሳያውቅ የኛ አባቶች ግን መድሃኒት ሲቀምሙ ነበር። አሁን ግን የተገላቢጦሽ ሆኗል። ፊት ፊት ስንመራ በወደቅንበት ሳንነሳ ስለቀረን ኋለኞች ፊተኞች ሆነው አሁን አዋቂም ጌታም፣ ሰጪኝም ነሺም እነርሱ ሆነዋል።

ታዲያ የትና የት ጥለውን ከሄዱ በኋላ እጃችን ያለውን ግእዝን ሊቀበሉን ወደኋላ አቆራርጠው ከወደቅንበት ሲመለሱ ምን ሽተው ነው የሚመስለን? መቼም እንደ ደጉ ሳምራዊ ሊጸድቁብን ነው ብለን የምናስብ አይመስለኝም። ከገባን ግእዝ ጉዳያቸው አይደለም። ጉዳዩ በግእዝ የተጻፈውን ማወቁ ላይ ነው። አውቆም ዓለምን መዘወሪያ ቁልፍ መጨበጥ ነው። ጨብጦም የታላቅነት ማማ ላይ መውጣት ነው። ወጥቶም ሁሉንም ቁልቁል እያዩ፣ ዓለም ሁሉ የሚነጠፍለት ጌታ መሆን ነው። ከዚያስ? እንደማንል ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# “ለሕዳሴው ግድብ እየተደረገ ያለው የሕዝብ ድጋፍ በታሪክ ተሰንዶ ሊቀመጥ የሚገባው አኩሪ ተግባር ነው”

*-ፕሮፌሰር መኮንን አያና*

*በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የውሃ ምህንድስና ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ*

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

የግብጽ ፖለቲከኞችና ምሁራን ዓባይን የራሳቸው ንብረት አድርገው ከመመልከት ባለፈ ከፈጣሪ የተሰጠን ስጦታ ነው በማለት እነሱም አምነው የግብጽንም ሕዝብ እስከማሳመን ደርሰው ነበር። በዓባይ ወንዝ ላይ ኢትዮጵያ ምንም መሥራት የለባትም ብቻ ሳይሆን ካለ ግብጽ ፈቃድም መንቀሳቀስ የለባትም የሚልም እምነት አዳብረው ቆይተዋል።

ይህን ሃሳባቸውን ሥጋ አልበሰው እውነት ለማድረግ እንደ ማስረጃ የሚያቀርቡት ደግሞ የቅኝ ግዛት ዘመን ውሎችን ነው። በታሪክ ተዘግቦ እንደምናገኘው በ1902 ዓ.ም እና በ1959 ዓ.ም የነበሩት ስምምነቶች ኢትዮጵያን የሚመለከቱ ሊሆኑ አይችሉም። ምክንያቱም እነዚህ ስምምነቶች ኢትዮጵያ የተሳተፈችባቸው ወይም የኢትዮጵያን ስምምነትና ይሁንታ ያገኙ ሳይሆን ከቀኝ ገዥዎች ጋር የተደረጉ ስለነበሩ ነው።

በዚህም ዓይነት ግብጻውያን በልበ ሙሉነት የሕዳሴው ግድብ ሊሠራ እንደማይገባ ሲወተውቱ ቆይተዋል። በቻሉት መጠንም የግድቡን ሥራ ለማደናቀፍ ያልሞከሩት ሴራ፤ ያልደረሱበት ቦታ አልነበርም። ነገር ግን ሁሉም ነገር ሳይሳካ ቀረና ግድቡም ተጠናቆ አንደኛውን፣ ሁለተኛውን፣ ሶስተኛውን እና አራተኛውንም ሙሌት ማጠናቀቅ ተቻለ። ይህም ሆኖ ግብጻውያን ግድቡ ከተጀመረም በኋላ በየደረጃው ተቃውሟቸውን ከማሰማት ብሎም ከማስፈራራት ተቆጥበው አያውቁም። ነገር ግን ያልታሰበው ሆነና የሕዳሴው ግድብ በኢትዮጵያውያን ትብብርና ተሳትፎ ዛሬ ላይ ደርሶ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት በቃ።

ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ለተፋሰሱ ሀገራት ትሰጥ የነበረው ውሃ ብቻ ሳይሆን ለም አፈርም ነበር። በዚህ ዓይነት የተፋሰሱ ሀገራት በተለይም ግብጻውያን ከሺህ ዓመት በላይ ሲጠቀሙ ቆይተዋል። የእነሱ ተጠቃሚነት ዛሬም ባይቋርጥም ኢትዮጵያ ግን የውሃ ሀብትን በመጠቀም ረገድ አዲስ ምዕራፍ ለመጀመር በቅታለች። ለመሆኑ የታላቁን የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ እውን በማድረግ ሂደት በነበሩት ውጣ ውረዶች እንደ ሀገር ምን ተጠቃሚነት ተገኘ ስንል በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የውሃ ምህንድስና ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ፕሮፌሰር መኮንን አያና ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ያላት የውሃ ሀብት እና ተጠቃሚነት እንዴት ይገለጻል?**

**ፕሮፌሰር መኮንን፡-** ኢትዮጵያ ከፍተኛ መጠን ያለው የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ሀብት ያላት ሀገር ናት። ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ በሚጠበቀው ደረጃ ሥርዓቱን ጠብቆ ለመጪውም ትውልድ በሚጠቅም መልኩ እየተገለገልንበት አይደለም። የውሃ ሀብት በባህሪው ከተፈጥሮ፤ ከአየር ንብረት ለውጥና በሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች እየቀነሰ የሚመጣ ነው። በመሆኑም ይህንን ከፍተኛ ጥቅም ያለውና ለትውልድ ሊተላለፍ የሚገባ ሀብት በአግባቡ እያበለጸጉ መጠቀም ይጠበቃል። በርግጥ በአሁኑ ወቅት እንደ ሀገር በበርካታ ችግሮች ውስጥ መሆናችን ይታወቃል።

ዛሬም ድረስ ለአብዛኛው ሕዝብ በምግብ ራስን መቻል፤ የንጽህና መጠበቂያ እና ንጹህ መጠጥ ውሃ ማግኘት፤ ኤሌክትሪክ አቅርቦትና ሌሎችም እንደ ቅንጦት የሚታዩበት ነው። በጥቅሉ በድህነት ውስጥ እየኖረ ያለው ሕዝብ ቁጥር ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል። ይህንን ችግር ለመሻገርም በመንግሥት በኩል እንደ ሀገር ኢኮኖሚውን ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ለማሸጋገር እቅድ ተይዞ እየተሠራ ይገኛል። ተስፋ የምንጥልበትና ብዙ እየተሰራበት ያለው የግብርናው ዘርፍም ከውሃ አቅርቦት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው።

እነዚህ ሁሉ እቅዶች እውን ሊሆኑ የሚችሉት ግን ውሃን ብቻ ሳይሆን ከውሃ የሚገኘውንም የኤሌክትሪክ



ኃይል በአግባቡ በማልማት መጠቀም ሲቻል ነው። በተጨማሪ ዛሬ ላይ በስፋት እየተሄደባቸው ያሉት ከተሞችን ለማዘመን የተጀመሩ ሥራዎችም በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል እና በቂ ውሃ የሚጠይቁ ናቸው። እንደ አጠቃላይ የውሃ ሀብትን መጠቀም በተለይም ትልልቅ ወንዞችን እየገደቡ ከፍተኛ የኃይል አቅርቦት ማመንጨት መቻል ለኢኮኖሚው ብቻ ሳይሆን ለሀገር ሉዓላዊነትም መጠበቅ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል።

ይህም ሆኖ በየዘመኑ የነበሩ የሀገሪቱ መሪዎችም ሆነ ሕዝቡና ምሁራን፤ የውሃ ጥቅምን በአግባቡ ተረድተውት የነበረ ቢሆንም ያሉትን ተግዳሮቶች በአግባቡ መረዳት የተቻለው አገልግሎት ላይ ለማዋል እንቅስቃሴ ሲጀመር ነበር። በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በዓባይ ወንዝ ላይ ግድብ ለመሥራት ታቅዶ በአሜሪካውያን ጥናትም ተካሂዶ እንደነበር ይታወሳል።

ንጉሱ፣ በወቅቱ ብድር እንዳይገኝ ከማድረግ ጀምሮ ከፍተኛ ጫና ይደረግባቸው ስለነበር ሊሳካላቸው ባለመቻሉ «እኛ ባይሳካልን ወደፊት ልጆቻችን ይሰሩታል ይቀመጥ» ብለው ነበር ጉዳዩን በእንጥልጥል ያቆዩት። እነዚህ በጣም ከፍተኛና የተወሳሰቡ ሴራዎች ኢትዮጵያ ብዙ የተዘፈነለትን ዓባይን አልምታ አቅም ፈጥራ ወደ ሌሎች ወንዞችና የውሃ ሀብቶቿ እንዳታማትር እንቅፋት ሆኖባት ቆይቷል።

ዛሬም ድረስ ግብጽና ሱዳን በዓባይ ወንዝ ላይ ምንም ልማት እንዳይከናወን እንደ ሀገራቸው ፖሊሲ በማድረግና ትኩረት በመስጠት ኢትዮጵያ ላይ ጫና ለመፍጠር እየሠሩ ይገኛል። የታላቁ ሕዳሴ ግድብ መጀመር እነዚህን በስውርና በተለያየ አካሄድ አሻጥር ሲሰሩ የነበሩ ሴረኞችን ግልጽ አውጥቷል።

በርግጥ የኤሌክትሪክ ኃይልን ከተለያዩ ምንጮች ማግኘት እንደሚቻል ይታወቃል። ነገር ግን በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ዘላቂ የሆነው መፍትሔ የሚገኘው ከውሃ በምናመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል የሚወሰን ይሆናል። ይህም ሆኖ ትልልቅ ግድቦችን በመሥራት ኃይል ለማመንጨትና ለመስኖ ለማዋል በአግባቡ እንዳንጠቀም ፍላጎቱ ቢኖርም የተለያዩ ተግዳሮቶች ነበሩብን። ከዚህም ውስጥ የአቅም ውስንነት ቀዳሚው ነበር።

አቅም ስንል በዚህ ረገድ በጥቅሉ የሰለጠነ የሰው ኃይል፤ የቴክኖሎጂና ከፍተኛ የበጀት እጥረት ነበረብን። ከንጉሱ ዘመን ጀምሮ እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት እንደ አማራጭ ሲወሰድ የነበረው ወደ ውጭ መመልከት ነበር። ከውጭ ሀገራት የሚጠበቁ አቅሞች በተለይም ብድር ደግሞ በቀላሉ የማይገኝ ሲሆን ቢገኝም ይዞት የሚመጣው መሰናክልም ነበር።

እናም ይህንን ህልም እውን ለማድረግ የነበሩትን ክፍተቶች ማስታረቅ ይጠበቅ ነበር። በአንድ ወገን የራስን የፋይንስ አቅም፤ የሰለጠነ የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ በማሳደግ በራስ አቅም መገንባት ሲሆን ፤ ሁለተኛው በዲፕሎማሲው ጫና ፈጥሮ የሚተባበርና ድጋፍ የሚያደርግ አጋር ማግኘት ነው። ሁለተኛው መንገድ ለረዥም ዘመናት ተሞክሮ ያልተሳካ በመሆኑ አማራጭ የተደረገው ዛሬ የተደረሰበትን ውጤትም ሊያስገኝ የቻለው የራስን አቅም አሟጦ መጠቀም ነበር። ይህም ቢሆን ግን ረዥምና ውስብስብ ሂደቶችን ያለፈ አሰልቺና ፈታኝ ነበር ለማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ የውሃ ሀብቷን ለማልማት፣ ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር ያላት አቅም እንዴት ይታያል ?**

**ፕሮፌሰር መኮንን ፡-** ኢትዮጵያ ይህንን የሚያህል የውሃ ሀብት ተሸክማ በዘርፉ ጥናትና ምርምር ማካሄድ የጀመረችው ዘግይታ ነበር ለማለት ይቻላል። በ1970 ዎቹ ዓ.ም በአሁኑ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የወቅቱ አርባ ምንጭ ውሃ ቴክኖሎጂ ከተመሰረተ በኋላ በርካታ በዘርፉ የሰለጠኑ ባለሙያዎች መውጣት ጀምረዋል። በወቅቱ በቴክኖሎጂው ግቢ ውስጥ በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ይጻፉ የነበሩ ጥቅሶች ምን ያህል ቁጭት እንደነበር የሚያመላክቱ ነበሩ።

በተለይም እንደ መፈክር በየቦታው ተጽፎ የነበረው «የውሃ ሀብታችን ለሀገራችን ብልጽግና ይውላል» የሚለው እስከ ዛሬም ድረስ የዘለቀ ጥቅስ ለመሆን በቅቷል። ከዛም በኋላ በዘርፉ ትምህርት የሚሰጡና ምርምር የሚያደርጉ ዩኒቨርሲቲዎች እየተስፋፉ መምጣትና የተለያየ ፕሮግራሞች መከፈት በሰለጠነ የሰው ሀብት ረገድ ያሉትን ክፍተቶች እያጠበባቸው መጥቷል። ከመስኩ ስፋትና ከሚጠበቀው የሰው ኃይል አኳያ ግን ዛሬም ቢሆን ሙሉ ለሙሉ ተቀርፏል ለማለት አይቻልም።

**አዲስ ዘመን፡- ዓባይ ወንዝ የተፋሰሱ ሀገራት በተለይም ኢትዮጵያውያንና ግብጻውያን ተስማምተው ለመጠቀም መሰናክል የሆነባቸው መሠረታዊ ጉዳይ ምንድን ነው ?**

**ፕሮፌሰር መኮንን ፡-** የኢትዮጵያ 70 በመቶ የውሃ ሀብትና ሌሎች እምቅ ሀብቶች ያሉት በዓባይ ተፋሰስና ወደ ትልቁ ናይል በሚገቡ ወንዞችና አካባቢው ነው። ግብጻውያን «የናይል ውሃ የመኖርና ያለመኖር እጣ ፈንታችንን የሚወስን ነው» እንደሚሉት ሁሉ በአንጻሩ የኢትዮጵያ የማደግና ያለማደግ፤ የመልማትና ያለመልማት እጣ ፈንታም የሚወሰነው በዚሁ ነው። ይህንን በመገንዘብ የናይል ተፋሰስ ሀገራት ተቀራርበው እንዲነጋገሩ እና መተማመንና ህብረት እንዲፈጥሩ የናይል ቤዝን አንሼቲቭ የሚባል ወደ ሥራ ገብቶ ስምምነት ተፈጥሮ ብዙ ሲሰራበት ነበር።

ይህ ሲደረግ የነበረውም ታላላቅ በሚባሉት ሀገራት በሰጡት የገንዘብ ድጋፍ ነው። በወቅቱም የነበሩት ደቡብ ሱዳንም ራሱን ችሎ ሲጨመር አስራ አንድ ሀገራት ተቀራርበ የመነጋገር ፕሮጀክት የመቅረጽ ተግባራት ሲያከናወኑ ነበር። ይህ የተጀመረበት ዋነኛ ምክንያትም የተፋሰሱ ሀገራት የሚካፈሉት የዓባይ ወንዝ ብዙ ውዝግቦችን እንደሚያስነሳ ስለሚታወቅ ሊፈጠር የሚችለውን እሰጥ እገባ በማስቀረት በትብብር ለመሥራት ሲባል ነበር።

በዚህም ውስጥ ሊተገበር የታሰበው ዓለም አቀፍ የውሃ ሕግ እነዚህን የጋራ ውሃዎች በትብብር፣ በፍትሃዊነትና በምክንያታዊነት ላይ የተመሠረተ አጠቃቀም እንዲኖር የሚያደርግ ነው። ኢትዮጵያም በዚሁ ማሕቀፍ ውስጥ በመሆን የሕዳሴው ግድብ እንዲጀመር ለማድረግ በቅታለች። ግብጻውያን የሕዳሴው ግድብ እውን መሆን እነሱ ላይ ምንም ተጽእኖ እንደማያመጣ ይልቁንም ዓመቱን ሙሉ የተመጣጠነ የውሃ ፍሰት እንዲኖር በማድረግ ለጎርፍ አደጋ እንደሚታደጋቸው ቢያውቁም ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበሩም።

ምክንያታቸው ደግሞ ለዘመናት የዘለቁበትን የበላይነታቸውን የሚያሳጣና ኢትዮጵያን ተከትለው ሌሎች ሀገራት ይጠቅመናል የሚሉትን መሥራት ጀምረው የግብጻውያን የበላይነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ እንዳይገባ በማሰብ ነበር።

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

# ወቅታዊ

## "ለሕዳሴው ግድብ እየተደረገ ያለው የሕዝብ ድጋፍ...

ከገጽ 6 የዞረ

**አዲስ ዘመን ፦ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ በተጀመረበት ወቅት እና ዛሬ እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ የግብጽና ግድቡን ሲቃወሙ የነበሩ ሀገራት ምላሽ እንዴት ያዩታል?**

**ፕሮፌሰር መኮንን፦** በዓባይ ግድብ ላይ ዛሬ በመጠናቀቅ ላይ ያለው የሕዳሴው ግድብ ሲጀመር ቀድሞ ከነበረው ሙከራ ሙሉ ለሙሉ በተለየ አካሄድ ነበር። ከዚያ በፊት የተደረጉት ሙከራዎች በገንዘብም በቴክኖሎጂም በሰው ሀብትም ረገድ ምንጭ ሊደረግ የነበረው ከውጭ በመጠበቅ ነበር። ይሄኛው አካሄድ ግን በይፋ ምንም ዓይነት ነገር ርዳታ ሳይጠየቅ ሙሉ ለሙሉ የራስ አቅምን በመጠቀም እውን ለማድረግ ወደ ሥራ መገባቱ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ ብዙዎችን ያስገረመ ነበር።

በሌሎች በርካታ ሀገራት በኩል ጅምሩ ከግብ የማይደርስ በእንጥልጥል የሚቀር ነው የሚል ጠንካራ ግምትም ነበራቸው። በአንጻሩ በኢትዮጵያውያን በኩል በግልባጩ የአንድነት የህብረት ማጠንከሪያና በራስ መተማንን ያጎነጸፈ ለመሆን ቻለ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዛሬም ድረስ የዘለቀው የመንግሥት ጥሪን ተከትሎ ለሕዳሴው ግድብ እየተደረገ ያለው የሕዝብ ድጋፍ እንደ ታሪክ ተሰንዶ ሊቀመጥ የሚገባው አኩሪ ተግባር ነው።

እ.ኤ.አ በ2010 ብዙዎቹ የናይል ቤዚን ፕሮግራሞችም እያለቁ ሲሄዱ የጋራ ማሕቀፍ የሚባለውን ዶክመንት ለማዘጋጀት በቁ። በዛው ዓመት በግንቦት ወር ስምምነቱን ኢትዮጵያ፣ ሩዋንዳ፣ ታንዛንያ ዑጋንዳ በኢንተቤ የፈረሙ ሲሆን፣ ከአምስት ቀን በኋላ ኬንያም ፈረመች። እንዲህ እንዲህ እያለ ቆይቶ በቅርቡም ደቡብ ሱዳን ፈርማ በምክር ቤቷ ለማጽደቅ በመብቃቷ ለኮሚሽን ምስረታው ምቹ ሁኔታ ተፈጠረ ማለት ነው። ይህም ሆኖ ግን የግብጽ መንግሥት ገና ከሕዳሴው ግድብ ግንባታ ከተመሰረበት ጊዜ አንስቶ ሥራውን ያስቆሙልኛል አልያም ያስተጓጉሉታል ያላቸውን የተለያዩ ጠንካራ ዘመቻዎች ሲያካሂዱ ቆይተዋል።

እ.ኤ.አ በ2015 «ፕሪንስፕል ኦፍ ዲክላሬሽን» የሚባል ኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብጽ ተስማምተው ፈርመዋል። እዚያ የስምምነት ዶክመንት ውስጥ የተቀመጠው ሃሳብ ኢትዮጵያ ግድቡን መገንባት እንደምትችል ነገር ግን ሌሎች ዓለም አቀፍ ሕጎችና መመሪያዎችን እየተጠበቁ እና በትብብር መቀጠል እንዲቻል ማረጋገጫ የሚሰጥ ነበር። ኢትዮጵያ በዛ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኗ የግድቡን ሥራ ብትጀምርም በግብጻውያን በኩል ሌሎች በርካታ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች መቅረብ ጀመሩ።

ግድቡን እንደ ማስያዣ በመጠቀም ነገር ግን የእነሱን የተለየ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ በቅኝ ግዛት ዘመን የነበሩ ውሎችን በማንሳት እንዲተገበሩ መወትወታቸውን ቀጠሉ። ከአሜሪካ ጋር በመተባበርም በዓባይ ተፋሰስ ወንዞች ላይ ምንም ሥራ እንዳይካሄድ የሚያደርግ እና ሌሎች ድብቅ ሴራዎችን የያዙ ውል እስከ ማዘጋጀት ደርሰውም ነበር።

በአንጻሩ ደግሞ በወቅቱ በኢትዮጵያ በኩል የነበረው ሁኔታ የሕዳሴውን ግድብ በተመለከተ ከፍተኛ አቅም እየተፈጠረ የነበረበትና ሕዝቡም ከመንግሥት ጎን በመቆም ትልቅ ተሳትፎና ትኩረት የሰጠበት ነበር። ድርድሩን ሲያደርጉ የነበሩትም ኢትዮጵያውያን ይቀርብላቸው የነበረውን የሀገርን ጥቅም የሚነካ ስምምነት ለመፈረም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል።

በተጨማሪ ግብጻውያን ጉዳዩን ለተባበበሩት መንግሥታት ምክር ቤትም በተደጋጋሚ ሲያቀርቡት ነበር። በአንድ ወቅት ግብጻውያን 63 ገጽ አቤቱታ አቅርበው የነበረ ሲሆን፣ በሶስተኛው ቀንም ኢትዮጵያ 79 ገጽ የያዘ ማብራሪያ እና ምላሽ ሰጥታለች። የተባበሩት መንግሥታት ምክር ቤትም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ጉዳዩን ወደ አፍሪካ ህብረት ወስዳችሁ ተደራደሩበት የሚል ምላሽ ሰጥቷቸዋል።

ጉዳዩ አፍሪካ ህብረትም ከመጣ በኋላ በተለያዩ ጊዜያት በርካታ ድርድሮች ቢካሄዱም ሊሳኩ አልቻሉም፤ ምክንያቱም ሱዳንና ግብጽ ከላይ እንደተገለጸው ለዘመናት የቆየውን አቋማቸውን መቀየር ባለመፈለጋቸው ነበር። አቋማቸው ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር በፍጹም የተቃረነ ውሃ መቀነስ የለበትም፤ የተፈጥሮ



**ግብጻውያን የሕዳሴው ግድብ እውን መሆን እነሱ ላይ ምንም ተጽእኖ እንደማያመጣ ይልቁንም ዓመቱን ሙሉ የተመጣጠነ የውሃ ፍሰት እንዲኖር በማድረግ ለጎርፍ አደጋ እንደሚታደጋቸው ቢያውቁም ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበሩም**

ፍሰቱም መቀየር የለበትም የሚል የራሳቸውን የበላይነት የሚያስጠብቅ ብቻ ነበር። ኢትዮጵያ ደግሞ በግዛቷ ውስጥ የሚመነጩ ውሃዎችን ከመጠቀም የሚያግድ ምንም ዓይነት ሕግ ባለመኖሩ በእነሱ በኩል የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ሳትቀበል ለመቆየት ተገዳለች።

ከዚህም በኋላ በቅርቡ ኢትዮጵያ ውስጥና ካይሮ የተጀመረ ውይይት የነበረ ቢሆንም ሊሳካ አልቻለም። ምክንያቱ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው ግብጻውያን ለዘመናት ከዘለቀው ሃሳባቸው የማይላቀቁ በመሆኑ በሰጥቶ መቀበል መርህ ለመንቀሳቀስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ነው።

በተለያየ መንገድም ጉዳዩ ዓለም አቀፍ ትኩረት እንዲያገኝና መላውን አረብ ሀገር የሚመለከት እንደሆነ ለማስመሰል ያልሞከሩት ቀዳዳ ያልሄዱበት መንገድ አልነበረም። ይህ ሁሉ ሲሆን የግብጽ ባለሥልጣናትና ተደራዳሪዎች ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሲገልጹ የነበሩት ኢትዮጵያ ፈቃደኛ አለመሆኗን ነው።

በኢትዮጵያ በኩል ግን በዚህ ውጣ ውረድ ውስጥም በመሆን በርካታ ድርድሮች እየተደረጉ የግድቡ ሥራ አልተቋረጠም ነበር። በመንግሥት በኩል የተሰጠውም ትኩረት ሕዝቡም ሲያደርግ የነበረው ድጋፍ ሳይቀዛቀዝ በመቀጠሉ ግድቡ ውሃ ወደመያዝ ለመሸጋገር ቻለ። ያንንም ተሻግሮ አራቱ ተርባይኖች ሥራ ለመጀመር የበቁ ሲሆን በኢትዮጵያ በኩል ግድቡ ሲጀመር የተገባው ቃል እውን ሆኖ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ የጎረቤት ሀገራትም ከግድቡ ተጠቃሚ እየሆኑ ነው።

ዛሬ ላይ ከግድቡ የሚመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል ለኬንያ ለሱዳን ለታንዛንያ የሚቀርብበት ሁኔታ እየተመቻቸ ይገኛል። በቅርቡም ተጨማሪ ተርይባኖች ወደሥራ የሚገቡ ሲሆን፣ ይህም የሕዳሴው ግድብ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እንጂ ማንንም ለመጉዳት አለመሆኑ የሚረጋገጥበት መሆን ችሏል።

**አዲስ ዘመን፦ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ከኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ባለፈ ለኢትዮጵያ ምን ትሩፋት ይዞ መጥቷል ለማለት ይቻላል ?**

**ፕሮፌሰር መኮንን፦** የሕዳሴው ግድብ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በብዙ መንገድ እንደተ ፈተኑበት ሁሉ ውጤቱም ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ነው። ሲጀመር ግድቡ ግዙፍ በመሆኑና ብዙ ወጪና አቅም የጨረሰ ነው። ከአስር ዓመት በፊት ግድቡን በሚቃወሙ አካላት በኩል የሌሎች ሀገራት ድጋፍ ካልታከለበት አይጀምሩትም ቢጀምሩትም አይጨርሱትም የሚል ምልከታ ነበር።

ይልቁንም ለዚህ በሚል ከሕዝቡ የሚሰበሰበውም ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ የትም ባክኖ ይቀራል ብለውም ነበር። ትኩረታቸውንም አድርገው ሲሰሩ የነበሩት ድጋፍ ያደርጋሉ ብለው በገመቷቸው ሀገራት ላይ ነበር። ቀስ በቀስ ወደተግባር ሲገባና ግንባታው እውን እየሆነ ሲመጣ እነሱም ዘመቻቸውን በዛው ልክ እያጠናከሩ ለመሄድ ተገደዱ።

ውጤቱ ግን ኢትዮጵያ ካለ ማንም ድጋፍ መሥራት እንደሚቻል በተግባር ያሳየችበት ለመሆን በቅቷል። ግብጻውያን በቀጣናው በአንጻራዊነት ያላቸውን እድገትና የተሻለ የጦር ኃይል የሚመጣጠን ሀገር ኢትዮጵያ መኖሯን ያመላከተም ነው። በኢትዮጵያውያን በኩልም በራስ አቅም በራስ ጥረት ብዙ መሥራት ፤ መልማት እንደሚቻል ለሕዝብም ለመንግሥትም ማረጋገጫ የሰጠ ሆኗል።

ለጎረቤት ሀገራትም ቢሆን ኢትዮጵያ ልማት እንጂ ሌሎችን መጉዳትን ማዳከምን መዳረሻው ያደረገ አላማ እንደሌላትም ህያው ምስከር ለመሆን በቅቷል። በቅርቡ ጠቅላይ ሚንስትሩ ለምክር ቤት የተናገሩት ለዚህ ጥሩ ማሳያ ይሆናል። «ጎረቤቶቻችን እየተቸገሩ ማየት አንፈልግም፤ ካጠራቀምነው ራሱ እንልክላቸዋለን» ብለው ነበር።

የኃይል አቅርቦቱ ለሀገር እድገት ያለው ጠቀሜታ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያ በቀጣናው ያላትን ተደማጭነት ያሳድጋል። ከሕዳሴው ግድብ የሚገኝ ገቢ ሌሎች ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ይረዳል። ቱሪዝምና ሌሎችንም ማንሳት ይቻላል። ከምንም በላይ በሌሎች ወንዞች ላይ ለሚከናወኑ ግድቦችም ይሁን ለሌሎች ትልቅ አቅም የሚጠይቁ ፕሮጀክቶች ይቻላልን ያቀዳጀ ነው።

ከዚህም በላይ የትኛውም ሀገር ይሁን ቡድን አቅም የሌለውና ደሃውን ወዳጅ ተባባሪ ማድረግ አይፈልግም። የሕዳሴው ግድብ ኢትዮጵያን በወዳጅነት የሚቀርቧትን አካላት እንዲኖሩ የሚያደርግ ነው። የሕዳሴው ግድብ እውን መሆን ከምሥራቅ አፍሪካ ተሻግሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውንም እይታ የሚነካ ነበር።

አሜሪካ ትልቋ የግብጽ ተባባሪ እንደመሆኗ በአሁኑ ምርጫ ባሸነፉት የቀድሞው ፕሬዚዳንቷ ዶናልድ ትራምፕ በኩል ጠንካራ ጫና ሲደረግም እንደነበር እናስታውሳለን። ያንን ጫና በመቋቋም የዛሬውን ብቻ ሳይሆን የመጪውን ትውልድም ጥቅም ማስጠበቅ መቻል ትልቅ ድል ነው።

እዚህ ላይ ግንዛቤ መደረግ ያለበት እንደ ሀገር የሚደረጉ ውሎች ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልጉ መሆናቸውን እና ብዙ እንደተለፋባቸው ነው። እንደዚህ ያሉ ሀገራዊ ስምምነቶች ሲካሄዱ በጽሑፍ ከሰፈረው ጀርባ የሚኖሩ አጀንዳዎችን ሴራዎችን መገንዘብ ይጠበቃል።

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ያልፈረመችበትና የማትቀበለውም ቢሆን ግብጻውያኑ የሚያነሱት ለእነሱ ብቻ ጥቅም የሚሰጣቸውን ውል መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል። ለምሳሌ ግብጻውያን ደግመው ደጋግመው የሚያነሱት ለዘመናት የኖረውን ፍሰት አናስተጓጉልም የሚል ስምምነት እንዲደረግ የሚያቀርቡት ጥያቄ አለ። ይህንን መቀበል ማለት በዓባይ ገባር ወንዞች ላይ ምንም አይነት ልማት አናከናውንም እንደማለት ነው።

ይህ የመጪውን ትውልድ የልማት ጥያቄ መዝጋት እንደማለት ነው። ዛሬ ላይ የመጪውን ትውልድ ተጠቃሚነት የሚያጓድል የሀገርን ሉዑላዊነት የሚነካ ስምምነት ቢደረግ ከዓመታት በኋላ ተስቦ መውጣቱ አይቀርም። በመሆኑም በሕዳሴው ግድብ ዙሪያ የተደረጉ የስምምነት ሂደቶች እንደ አጠቃላይም በቀጣይ በሌሎች ጉዳዮች በሚካሄዱ ሀገራዊ ስምምነቶች ላይ ምን ዓይነት ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ ትምህርት የተወሰደባቸው ናቸው ለማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፦ ስለነበረን ጊዜ ከልብ እናመሰግናለን።**

**ፕሮፌሰር መኮንን፦** እኔም አመሰግናለሁ።

# “የኢትዮጵያ የመልማት እጣ ፈንታ የሚወሰነው በዓባይ ተፋሰስና ወደ ትልቁ ናይል በሚገቡ ወንዞቻችን ነው”

- ፕሮፌሰር መኮንን አያና

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የውሃ ምህንድስና ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የማደግና ያለማደግ፣ የመልማትና ያለመልማት እጣ ፈንታ የሚወሰነው በዓባይ ተፋሰስና ወደ ትልቁ ናይል በሚገቡ ወንዞቻችን እንደሆነ የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የውሃ ምህንድስና ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ፕሮፌሰር መኮንን አያና አስታወቁ።

ፕሮፌሰር መኮንን በተለይ ለአዲስ ዘመን እንዳስ ታወቁት፣ ግብጻውያን «የናይል ውሃ የመኖርና ያለመኖር እጣ ፈንታችንን የሚወስን ነው» እንደሚሉት፣ የሀገራችን የማደግና ያለማደግ፣ የመልማትና ያለመልማት እጣ ፈንታም የሚወሰነው የሀገሪቱ 70 በመቶ የውሃ እና ሌሎች እምቅ ሀብቶች ባሉበት በዓባይ ተፋሰስ እና ወደ ትልቁ ናይል በሚገቡ ወንዞች እና በወንዞቹ አካባቢዎች ነው።

እንደ ፕሮፌሰሩ ገለጻ፣ የውሃ ሀብት በባህሪው ከተፈጥሮ ፣ ከአየር ንብረት ለውጥና በሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች እየቀነሰ የሚመጣ ነው። በመሆኑም ይህንን ከፍተኛ ጥቅም ያለውና ለትውልድ ሊተላለፍ የሚገባ ሀብት በአግባቡ እያበለጸጉ መጠቀም ይጠበቃል።

አሁን እንደሀገር የያዝናቸው የልማት አቅዶች እውን ሊሆኑ የሚችሉት ውሃን ብቻ ሳይሆን ከውሃ የሚገኘውንም የኤሌክትሪክ ሃይል በአግባቡ በማልማት መጠቀም ሲቻል ነው ያሉት ተመራማሪው፣ ዛሬ በስፋት እየተሠሩ ያሉ ከተሞችን የማዘመን ሥራዎችም ቢሆኑ



በቂ የኤሌክትሪክ ሃይል እና በቂ ውሃ የሚጠይቁ ናቸው ብለዋል።

የውሃ ሀብትን መጠቀም፣ በተለይም ትልልቅ ወንዞችን እየገደቡ ከፍተኛ የሃይል አቅርቦት ማመንጨት መቻል ለኢኮኖሚው ብቻ ሳይሆን ለሀገር ሉዓላዊነትም መጠበቅ ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረውም ፕሮፌሰር መኮንን ገልጸዋል።

እርሳቸው እንደሚሉት፣ ግብጻውያን የህዳሴው ግድብ እውን መሆን እነሱ ላይ ምንም ተጽእኖ እንደማያመጣ ይልቁንም ዓመቱን ሙሉ የተመጣጠነ የውሃ ፍሰት እንዲኖር በማድረግ ከጎርፍ አደጋ እንደሚታደጋቸው ቢያውቁም፣ ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበሩም።

ምክንያታቸው ደግሞ ለዘመናት የዘለቁበትን የበላይነታቸውን የሚያሳጣና ኢትዮጵያን ተከትለው ሌሎች ሀገራት ይጠቅመናል የሚሉትን መሥራት ጀምረው የግብጻውያን የበላይነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ይከቱታል በሚል ፍራቻ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ዛሬ በመጠናቀቅ ላይ ያለው የህዳሴው ግድብ ምንም አይነት ነገር ርዳታ ሳይጠየቅ ሙሉ ለሙሉ የራስ አቅምን በመጠቀም እውን ለማድረግ ወደ ሥራ መገባቱ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ ብዙዎችን ያስገረመ ነበር ብለዋል። የህዳሴው ግድብ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በብዙ መንገድ እንደተፈተኑበት ሁሉ ውጤቱም ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ነው ሲሉም ተናግረዋል፡፡

የሕዳሴ ግድቡ ከምንም በላይ በሌሎች ወንዞች ላይ ለሚከናወኑ ግድቦችም ይሁን ለሌሎች ትልቅ አቅም የሚጠይቁ ፕሮጀክቶች ይቻላልን ያቀዳጀ ነው ያሉት ተመራማሪው፣ ከዚህ በኋላ ለሚከናወነ ሥራዎችም አቅም የፈጠረ ነው ብለዋል፡፡

በህዳሴው ግድብ ዙሪያ የተደረጉ የስምምነት ሂደቶች እንደ አጠቃላይም በቀጣይ በሌሎች ጉዳዮች በሚካሄዱ ሀገራዊ ስምምነቶች ላይ ምን አይነት ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ ትምህርት የተወሰደባቸው እንደሆኑም አስታውቀዋል ።

ከፕሮፌሰር መኮንን ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ ሙሉቃል በገጽ 6/7 ወቅታዊ አምዳችን ላይ ያገኙታል።

# ስምምነቱ በቱሪዝም ሀብትን ወደ ኢኮኖሚ መለወጥ የሚያስችል ብቁ አመራር መፍጠር ያስችላል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ- ቱሪዝም ሚኒስቴርና የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ያደረጉት ስምምነት ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ የቱሪዝም ሀብት ወደ ኢኮኖሚ መለወጥ የሚያስችል ብቁ አመራር መፍጠር እንደሚያስችል የቱሪዝም ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

ቱሪዝም ሚኒስቴርና የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ብቁ አመራሮችን ለመፍጠር የሚያስችላቸውን የስምምነት ሰነድ ትናንት ተፈራርመዋል፡፡

በስምምነቱ ወቅት የቱሪዝም ሚኒስትሯ ወይዘሮ ሰላማዊት ካሳ እንደገለጹት፣ እንደሀገር ዋና ዋና የማክሮ ኢኮኖሚ የዕድገት ምንጭ ተብለው ከተለዩት ዘርፎች መካከል የቱሪዝም ዘርፉ አንደኛው ነው፡፡ በሂደቱ በመንግሥት በኩል ፖሊሲ ተነድፎ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ለዘርፉ ኢንቨስትመንትም በርካታ ድጋፎች እየተደረጉ ነው፡፡ ይህ ከሀገር ውስጥ ባሻገር በቀጣናውና በአህጉር ደረጃ መታየት የሚችሉ ለውጦችን ማምጣት ተችሏል፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፣ ዘርፉ የሚፈልገውን የሰው ኃይል ለማፍራት የአቅም ማሳደግ ሥራ መሥራት ወሳኝ ነው። ስምምነቱም ኢትዮጵያ እምቅ የቱሪዝም ሀብት ያላት ሀገር እንደመሆኗ መጠን ሀብቱን ወደ ኢኮኖሚ መለወጥ የሚያስችል ብቁ አመራር መፍጠር እና በዘርፉ ያለውን ስብራት በመጠገን ወደ ውጤት ለመቀየር ያለመ ነው ብለዋል።

ሚኒስትሯ፣ በንግግራቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኢጋድ የቱሪዝም ሻምፒዮን ሆነው መመረጣቸው አስታውሰው፣ በአፍሪካ ህብረት ጭምር ኢትዮጵያ ያላት ዕምቅ የቱሪዝም አቅም እውቅና ተሰጥቷታል፡፡ የብሪክስ አባል መሆኗ ከሀገራት ጋር በጋራ የሚሠራበት የቱሪዝም ዘርፍ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በአባል ሀገራቱ ያለው የቱሪዝም አቅም መጠቀም የሚቻልበትን እና በሀገራቱ መካከል የአመራር አቅም ማሳደግ አብሮ የሚሄድ ጉዳይ መሆኑን ጠቁመው፣ ዘርፉ የሚፈለገውን ዕድገት ማምጣት እንዲችል እና በሀገር ውስጥ ኢኮኖሚ ላይ ያለውን አስተዋጽኦ ከፍ ማድረግ የሚቻለው በዘርፉ ውስጥ ያለው መዋቅራዊ ስብራት ማከም ሲቻል መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በዘርፉ በተለያዩ የሙያ መስክ ያሉ አካላትን በአመራር የአቅም የማሳደግ፣ የማላቅ ብቁ አመራሮችን የመፍጠሩ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶተታል ብለዋል፡፡

የቱሪዝም ዘርፉ ከመንግሥት ባሻገር የግል ዘርፉ ከፍተኛ የሆነ ተሳትፎ ያለበት መሆኑን ያስታወሱት ሚኒስትሯ፣ በዘርፉ ያለው አመራር አቅም ማሻሻል አስፈላጊና ብቁ አመራሮችን ለመፍጠር ስምምቱ ትልቅ ፋይዳ አለው ብለዋል፡፡

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ፕሬዚዳንት አቶ ዛዲግ አብርሃ በበኩላቸው አንድ ተቋም ስኬታማ እንዲሆን ከተፈለገ መዋቅራዊ ትስስር (ecosystem integration ) ያስፈልጋል፡፡ አንድ ተቋም ብቁ አመራር ፈጥሯል የሚባለው መዋቅራዊ ትስስሩ አመራር መፍጠር የሚችል የፖሊሲ ግልጽነት፣ የአመራር ልማት ፕሮግራም ሲኖር፣ የአመራር ብቃት መለኪያ፣ የአመራር ልቀትና እና በተቋም ላይ የመተግበር ብቃት መሠረት ያደረገ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

አንድ አመራር ውጤታማ የሚሆነው ግልጽ የሆነ የፖሊሲ ሲኖር ነው። አካዳሚው ቀጣይነት ያለው የአመራር ልማት ፕሮግራም ላይ እየሠራ ነው። ከቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር የተደረገው ስምምነት ፖሊሲውን የተረዳ ብቁ አመራር ለመፍጠር ነው። በሁለቱ ተቋማት ያለውን እምቅ አቅም በመጠቀም ለሀገራዊ ዕድገት እንዲውል ማድረግና ጠቅላላ አመራር ልማት ፕሮግራም እና የቱሪዝም ዘርፍ ልዩ አመራር ልማት ፕሮግራም ሥርዓተ ሥልጠና (ካሪኩለም) ቀረጻ ሥራዎችን በጋራ መሥራት መሆኑን ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል።

# “የኮሪደር ልማት ዋነኛ ግብ ለትውልድ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አመራሩ የኮሪደር ልማት ሥራውን በሚመለከት ከከተማዋ ነዋሪዎች ጋር ተቀራርቦ ለመሥራት ያከናወናቸውን ሥራዎች አድንቀው፣ በመጀመሪያው ምዕራፍ በተከናወኑ የኮሪደር ልማት ሥራዎች የተመዘገቡ ስኬቶች በሁለተኛው ምዕራፍ ላይም ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

በቀጣይ የልማት ሥራዎቹ በተቀመጠላቸው ጊዜና ጥራት እንዲጠናቀቁ በትኩረት መሥራት እንደሚገባ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስገንዝበዋል።

በመዲናዋ እየተከናወኑ ያሉ የሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ሥራዎች፣ የአረንጓዴ ሥፍራ፣ የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ መኪና ማቆሚያ፣ ብስክሌት መንገድ፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ጨምሮ ሌሎች ከተማዋን የሚያዘምኑና ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ የልማት ሥራዎች መሆናቸውም ተገልጿል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው የሁለተኛው ዙር የኮሪደር ልማት ሥራ ያለበትን ሁኔታ ትናንት ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጋር በመሆን መገምገማቸውን አስፍረዋል።

ከንቲባ አዳነች 2ኛውን ዙር የኮሪደር ልማት ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ጋር በጋራ መገምገማቸውን ጠቁመው፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰጡን አቅጣጫ 2ኛውን ዙር የኮሪደር ልማት በፍጥነትና በጥራት እናከናውናለን ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አመራሩን በማበረታታት ለልማት እየተባበሩ ያሉ የከተማዋን ሕዝብ፣ ሥራ ተቋራጮች፣ ባለሀብቶችን እንዲሁም በበጎ ፈቃደኝነት አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ የሚገኙ ወጣቶችን ማመስገናቸውንም ከንቲባዋ ገልፀዋል።

# ታሪክ ቀያሪዎቹ የቱሪዝም...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በማስተሳሰር አዳዲስ የቱሪስት እድሎችን እንዲከፈቱ መደላድል እየፈጠሩ ይገኛሉ ነው ያሉት።

እነዚህ አቅሞች የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከቱሪዝም በእጅጉ ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋሉ። የውጭ ምንዛሪ ገቢን ያሳድጋሉ፣ የሀገር ውስጥ ሀብትን በማንቀሳቀስ ሰፊ የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ። እንደ ታዳሽ ኃይል፣ ቸርቻሮ እና የምግብ ማቀነባበሪያ ያሉ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ ይላሉ።

የቱሪዝም የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንቶቹ ፈርጀ ብዙ ፋይዳ አላቸው ያሉት አያሌው (ዶ/ር)፣ ማህበረሰቦችን የሚያጠናክር እና የተፈጥሮ ሀብቶችን የሚጠብቅ ሁሉን አቀፍ፣ አካባቢያዊና አካታች እድገትን ያበረታታሉ ሲሉም ተናግረዋል።

ከዚህ በፊት በመሠረተ ልማት እጦት ከተጓዦች ተደብቀው የቆዩትን መንፈስን የሚያድሱ የመስህብ ሥፍራዎችን፣ መልከዓ ምድሮች፣ እጅግ የተለዩ አዕዋፋት እና ዕጽዋቶችን በትስስሩ በተፈጠሩ ዕድሎች ለጎብኚዎችና አሳሾች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታን እየፈጠሩ መሆኑን ገልጸዋል።

ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት የተመረቀው እጅግ ውብ የሆነው “ቤኑና መንደርን”ም እነዚህን ውጥኖች ይበልጥ እንደሚያሳካ ገልጸው፣ በተለይ ለምስራቁ የቱሪዝም መስመር እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ነው የተናገሩት።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መንደሩን መርቀው በከፈቱበት ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት፣ ቤኑና መንደር ይቻላልን በዓይናችን ያየንበት ነው ብለዋል። አካባቢው በጣም አስቸጋሪ የአየር ጠባይና መልከዓ ምድር እንዳለው ጠቅሰው፣ ይህን በመቋቋም ውብ ገጽታ ያለውን መንደር እውን ማድረግ ተችሏል ነው ያሉት።

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ይታሰብ ሥዩም በበኩላቸው፣ በሀገሪቱ የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ሆቴሎችና የሬስቶራንቶች ጥራት ያለውና የደንበኛን ፍላጎት የሚያረካ አገልግሎት ከመስጠት አኳያ ወጥነት የላቸውም። ይህም በሀገሪቱ የቱሪስት ፍሰትና የገቢ ምንጭ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሲያሳድር ቆይቷል ሲሉ ይገልጻሉ።

ኢትዮጵያ በቱሪዝሙ ዘርፍ ያላትን ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በተለይም የሆቴልና መሰል አገልግሎቶችን ማሳደግ ይገባል ያሉት አቶ ይታሰብ፣ ኢንስቲትዩትም ከሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ለኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል ነው ያሉት።

ከመስተንግዶ ሠራተኞች የደንብ ልብስ አለባበስ ጀምሮ የሚጠቀሙት ቋንቋና መስተንግዶ ደረጃቸውን የጠበቁ መሆን አለባቸው ያሉት አቶ ይታሰብ፣ የሆቴሎች አገልግሎት አሰጣጥና መሠረተ ልማት በማሟላት ጥሩ መስተንግዶ በመስጠት የሀገርን ገጽታ መገንባትና የቱሪስት ቆይታ ጊዜ እንዲያራዝም ማድረግ እንደሚገባ ተናግረዋል።

ከዚህ አኳያ በገበታ ለሸገር፣ በገበታ ለሀገርና በገበታ ለትውልድ የተሠሩና እየተሠሩ የሚገኙ ፕሮጀክቶች በሀገሪቱ የሚታዩትን የቱሪስት መዳረሻዎች ውስንነት ችግር የሚቀርፉ ናቸው። ፕሮጀክቶቹ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ በመሆናቸው የቱሪስት ፍሰቱን የሚጨምሩ መሆናቸው ነው የገለጹት፡፡ ይህም የቱሪዝም ዘርፉ በኢኮኖሚ ዕድገቱ ጉልህ ድርሻ እንዲያበረክት ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል ነው ያሉት፡፡

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የቡናን ምርታማነት የሚያሳድግ አዲስ ምዕራፍ

**ወርቅነሽ ደምሰው**




ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ተወዳጅ የሆነው አረቢካ ቡና መገኛ ብቻ ሳትሆን ቡናን ለዓለም ያበረከተች ሀገር መሆኗ ይታወቃል። ቡና የሀገሪቱ የኢኮኖሚ መሠረት በመሆኑ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ረገድ በመጀመሪያ ደረጃ የሚጠቀስ ነው። በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሀገሪቱ ለቡና ተስማሚ የሆነ አምስት ነጥብ 47 ሚሊዮን ሄክታር መሬት፣ ምቹ ሥነ ምህዳር፣ በቂ የሰው ጉልበት ያላት፣ በልዩ ንጥረ-ነገር ይዘታቸውና ጣዕማቸው በዓለም እጅግ ተወዳጅ የሆኑ የቡና ዝርያዎች ባለቤት መሆኗ ተናግረዋል። ኢትዮጵያ የቡና ምርትን በብዛትና በጥራት ለዓለም ገበያ በማቅረብ ያላትን ደረጃ ከፍ እንደምታደርግም ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ‹‹ባለፉት ስድስት ዓመት ቡናን ከአረንጓዴ ዐሻራ ጋር አስተሳስረን በመትከላችን ምርታችን የቡና ምርት በየዓመቱ በ100 ሺህ ቶን እየጨመረ መጥቷል። በባለፈው የበጀት ዓመት በቡና የውጪ ንግድ አንድ ነጥብ 43 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር አግኝታለች›› ሲሉ መናገራቸው የሚታወስ ነው።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ ባለሥልጣኑ በ2017 በጀት ዓመት ብዛትና ጥራት ያለው ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን ከፍ ለማድረግ በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ነው። በተያዘው በጀት ዓመት ከ400 ሺህ ቶን በላይ የቡና ምርት ለውጭ ገበያ በማቅረብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ታቅዷል። በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ብቻ 115 ሺህ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ በመላክ 520 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል። በእነዚህ ሦስት ወራት የተገኘው የውጭ ምንዛሪ በበጀት ዓመቱ ለማግኘት የታቀደውን የሁለት ቢሊየን ዶላር ገቢ ዕቅድ ማሳካት እንደሚቻል አመላካች መሆኑ ተጠቁሟል።

ባለሥልጣኑ በበጀት ዓመቱ የተያዘውን ዕቅድ ለማሳካት የቡና ምርትና ምርታማነትን መጨመር እንዲሁም ጥራት ያለው ቡና ወደ ገበያ ለማቅረብ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑ ተገልጿል። የኢትዮጵያ ቡና በዓለም አቀፍ ገበያ ያለውን ተፈላጊነት ማሳደግ የሚያስችል ብራንድ የማስተዋወቅ ሥራ በሰፊው መሥራት በመቻሉ የኢትዮጵያ ቡና በዓለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪና ተመራጭ እንዲሆን ማስቻሉን ተመላክቷል።

የኢትዮጵያ የውጭ የቡና ገበያ መዳረሻ ሀገራት ጀርመን፣ ጃፓን፣ ሳዑዲ አረቢያ፣ ቤልጂየምና አሜሪካ ናቸው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ቻይና፣ ደቡብ ኮሪያና ጆርዳን የኢትዮጵያን ቡና በስፋት የሚገዙ ሀገራት እየሆኑ መምጣታቸውን የባለሥልጣኑ መረጃዎች ያመላክታሉ።

ሀገሪቱ ቡና በማምረትና ለዓለም ገበያ ተደራሽ እያደረገች የምትገኘው በአብዛኛው በቡና አምራች አርሶ አደሮች ቡናውን በማልማት ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በርካታ ኢንቨስተሮች በልማቱ ተሰማርተዋል።

ከእነዚህ መካከል አንዱ የሚድሮክ ኢንቨስት መንት ግሩፕ ነው። ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ በሀገሪቱ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ ተሰማርቶ እየሰራ ሲሆን፣ በአግሮ ፕሮሰሲንግ ዘርፍ፣ በቡናና በአትክልትና ፍራፍሬ ልማትም ተሰማርቶ እየሰራ መሆኑ ይታወቃል። በርካታ የቡና እርሻዎች ያሉት ሲሆን፣ ቡና ከመትከል ጀምሮ በማልማትና ለውጭ ገበያ በማቅረብ ይታወቃል። የቡናን ምርትና ምርታማነት ለመጨመር የተለያዩ ሥራዎች ሲሰራ መቆየቱንም የድርጅቱ መረጃዎች ያመላክታሉ።

ባለፈው ሳምንት በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ከሆነው ኒውማን ካፌ ግሩፕ ጋር ያደረገው ስምምነትም የዚሁ የቡናን ምርታማነት ለማሳደግ የሚያደርገው ጥረት አካል ነው። ስምምነቱ ቴክኒካል ድጋፍና የገበያ ተደራሽነት ላይም ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ተመላክቷል። ኒውማን ካፌ ግሩፕ መሠረቱን ጀርመን ያደረገ፣ 60 ድርጅቶችን በስሩ ያቀፈና በ30 ሀገራት በቡና ገበያ የሚታወቅ ድርጅት ነው።

የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጀማል አሕመድ በስምምነቱ ወቅት እንደተናገሩት፤ ስምምነቱ ለሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ትልቅ እምርታ የሚፈጥር ነው። ስምምነቱን ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ እንደነበረ ገልጸው፤ በተለይ በቡና ዘርፍ ላይ ትልቅ ሥራዎችን ከሚሰራው ዓለም አቀፍ ተቋም ኒውማን ካፌ ግሩፕ ጋር የተደረገ ስምምነት መሆኑ የኢትዮጵያን ቡና ምርታማነት ለማሳደግ ወሳኝ መሆኑን አስታውቀዋል።

ስምምነቱ የቡናን ምርታማነት ለማሳደግና የበለጠ ተሞክሮ ለመውሰድ ያስችላል። ኒውማን ካፌ ግሩፕ በቡና ገበያው ላይ ያለውን ልምድ ለሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ በማጋራትና የቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ ገበያው ላይ ለውጥ ለማምጣት ያለመ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንደሚሉት፤ ስምምነቱን ያደረገው ኒውማን ካፌ ግሩፕ ኢትዮጵያን ከልቡ የሚወድ ድርጅት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሮ መክፈት ብቻ ሳይሆን የኮፊ ፋውንዴሽን ያለው (የአርሶ አደር ማህበራት የሚረዳ) ድርጅት ሲሆን፣ ድርጅቱ ብራዚል ውስጥ ሰፊ የቡና እርሻ ያለውና በሄክታር 25 ኩንታል ቡና የሚያመርት የቡና እርሻ ባለቤት ነው።

የኒውማን ኮፊ ግሩፕ በቡና ምርቱ ከሚታወቁ ድርጅቶች መካከልም አንደኛው ነው። የቡናን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ረገድ ለአፍሪካ ሀገራት ቴክኒክ ድጋፍ እያደረገም ይገኛል። ይህም የአፍሪካ ቡና አመራረት ስለሳይንሱ በእጅጉ እንዲያውቅ አድርጎታል።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ ድርጅቱ አፍሪካ ውስጥ በኡጋንዳና ኬንያ ከአፍሪካ ውጭ ደግሞ በቬትናም ሰፊ የቡና እርሻ ያለውና ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ነው። በገበያ ተደራሽነቱም ሰፊ የሆነና በዓለም አቀፍ ደረጃ አሜሪካ፣ አውሮፖ፣ በደቡብ ኤዥያ በሚገኙ ከ30 ሀገራት በላይ ትላልቅ ድርጅቶች አሉት። በመላው ዓለም ትላልቅ ድርጅት ካላቸው ሀገራት ጋርም የገበያ ትስስር አለው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ስቶክ ማርኬቶች ላይም አተኩሮ ይሰራል።

ይህንን ድርጅት የተለየ የሚያደርገውና ከሚድሮክ ጋር የሚያገናኘው አንዱና ዋንኛ ጉዳይ ልክ እንደ ሚድሮክ ኩባንያ ባለቤት ሼክ መሀመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ ሚስተር ኒውማን የቤተሰብ ድርጅት መኖሩ ነው ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ‹‹ስምምነቱ ቤተሰባዊ ግንኙነቱን አጠናክረን ፤ ቤተሰብ ለቤተሰብ ተስማምተን አላማችንን የጋራ መሆኑን ከተረጋገጠ በኋላ እኛ የሚጎድለንን እነርሱ እንዲሸፍኑልን ማድረግን ያለመና ለረጅም ጊዜ ስንፈልገው፣ ስንሞክረው የነበረ ነው›› ሲሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚው አስታውቀዋል።

የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ 45 ድርጅቶችን በኃላፊነት እንደሚያስተዳድር የጠቀሱት ሥራ አስፈጻሚው፤ በአግሮ ፕሮሰሲንግ ሥር ከሚነሳው ዘርፍ አንዱ ቡና ብዙ ተግዳሮት እንዳለበት ጠቁመዋል። ይህንን ችግር መሻገር ፈተና ሆኖበት መቆየቱን ጠቅሰዋል።

ቡናን በተሻለ ዋጋ በዘላቂነት ለማቅረብ የተለየ ጥረት ማድረግን እንደሚጠይቅ አመልክተው፣ ይህንን ሥራ በራስ መሥራት ስላልተቻለ ጠንካራ አጋር ፍለጋ መገባቱን ይናገራሉ። ለዚህም ሲል ሚድሮክ የቡናን ምርታማነት ለማሳደግ ከኒውማን ኮፊ ግሩፕ ስምምነት መፈጸሙን ይገልጻሉ። ይህ ድርጅት አፍሪካን እንዲሁም ኢትዮጵያን በደንብ የሚያውቅ መሆኑንም ጠቅሰው፣ ይህም የተፈለገው ዓላማ ግብ እንዲመታ ለማድረግ የሚያስችል ስለመሆኑ እምነቱ እንዳላቸው ተናግረዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው ከቡና ጋር ተያይዞ የሚነሱት ጉዳዮች ዋነኛው የዋጋ ጉዳይ መሆኑንም አመልክተዋል። ቡና መሸጥ ባይከብድም እንዴት በምን ያህል ዋጋ ተሸጠ የሚለው ላይ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻሉ።

ባለፉት ሦስት ዓመታት በሀገር ደረጃ ቡና ለውጭ ገበያ በመላክ የሚገኘው ገቢ በጣም ማደጉን ጠቅሰው፣ ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ግን በዚያ ደረጃ እንዳላደገ ይገልጻሉ። በመሆኑም ሜድሮክ የቡና ምርታማነትን ማሳደግ ላይ መሥራት እንደሚጠበቅበት ገልጸው፣ ይህን ለማድረግ ብዙ ቴክኖሎጂዎች ቢሞከርም የተፈለገውን ውጤት ማምጣት ሳይቻል መቆየቱን ገልጸዋል። ከኒውማን ካፌ ግሩፕ የተደረገው ስምምነት ቴክኒካል ድጋፍ የሚያስገኝና በገበያ ተደራሽነት ላይም ትኩረት ያደረገና ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን አመላክተዋል።

ሚድሮክ ወደፊት ይህንን ተሞክሮ ለምርምር ተቋማትም ሆነ ለማህበራት እንደሚያጋራ ጠቁመው፣ ‹‹በኢትዮጵያ የቡና ምርት ላይ የራሳችንን ዐሻራ ለማስቀመጥ ይጠቅማል›› ሲሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ተናግረዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንዳሉት፣ ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ቡናን በምርት መጠን፣ በጥራት እና በተደራሽነት ደረጃ ማሳደግ ላይ ትኩረት ያደረጋል። ኒውማን ካፌ ግሩፕ 60 ድርጅቶችን በስሩ ያቀፈና በ30 ሀገራት በቡና ገበያ የሚታወቅ ድርጅት መሆኑ ስምምነቱ ከሚድሮክ ባለፈ የኢትዮጵያን ቡና ለማስተዋወቅ ይረዳል። ስምምነቱም በጋራ ተጠቃሚነት ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ዘርፉን በአጭር ጊዜ ውስጥ ማሳደግ ያስችላል።

የኒውማን ካፌ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሚስተር ዴቪድ ኒውማን ካፌ በበኩላቸው፤ በስምምነቱ ደስተኛ መሆናቸውን ገልጸው፤ የኢትዮጵያን ቡና በማስተዋወቅ እና ምቹ ገበያን በመፍጠር ረገድ ከሚድሮክ ጋር በትብብር እንደሚሰሩ አረጋግጠዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ልዩ ጣዕም ያለው ቡና ባለቤት ናት። ድርጅታቸውም በኢትዮጵያን በደንብ ይታወቃል። ቡና ላይ ያለውን ልምድ ተጠቅሞ ከሜድሮክ ጋር የተሻለ ሥራ ይሠራል። ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የቴክኒክ ድጋፎችን በመስጠት የቡና ምርት ምርታማነትን ለማሳደግ ይሰራል። የሜድሮክን የቡና ማምረት አቅም በማሳደግ የተሻለ ደረጃ ላይ ለማድረስ ጥረት ያደርጋል። ድርጅታቸው የረጅም ጊዜ ልምዱን ተጠቅሞ የኢትዮጵያን ቡና በዓለም ገበያ የበለጠ ለማስተዋወቅም ይሰራል።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አዱኛ ደበላ (ዶ/ር) የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ የቡናን ምርታማነት ለማሳደግ ከዓለም አቀፉ ኒውማን ካፌ ግሩፕ ጋር ስምምነት መፈራረሙ የቡና ምርታማነት በማሳደግ ረገድ ዘርፉ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለውና አዲስ ምዕራፍን እንደሚከፍትም ተናግረዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ለቡና ልማት ምቹ አካባቢ ያላት ሀገር ናት። የኢትዮጵያ ቡና ምርታማነት ግን ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው። የቡና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራሽነትን ማስፋት ይገባል።

ስምምነቱ ቴክኒካል ድጋፍ በማድረግ ቡናን ለዓለም አቀፍ ገበያ የሚያስተዋወቅ መሆኑ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ያስችላል ሲሉ ዋና ዳይሬክተር ተናግረዋል። ከአርሶ አደሮች እስከ ተጠቃሚዎች ድረስ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ ሀገሪቱ ከቡናው ዘርፍ ማግኘት ያለባትን ጥቅም እንድታገኝ የሚሠራው ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

## ጎሜ

# የባሕል ሕክምና ታካሚዎች

**ምሕረት ሞገስ**

ዘውዴ መታፈሪያ በጠና ታሟል፤ መቀመጥ አቅቶታል። በሽታው ብዙ ከመቀመጥ እና በቂ ውሃ ካለማግኘት ጋር ተያይዞ የሚመጣው የኪንታሮት በሽታ ነው። ድርቀትን ተከትሎ የመጣበት ይኸው በሽታ እያሠቃየው ይገኛል። ገብረየስ ገብረማሪያም ይህቺን ሕመም በደንብ ያውቃታል። መንግሥቱም የአንድ ሰሞን ተጠቂ ነበር።

ሁለቱም ይህንን በሽታ መዳን የቻሉት ሐኪም የሚላቸውን ሰምተው በመፈፀማቸው ነው። ሁለቱም ውሃ መጠጣት፤ ጥራጥሬ እና ቴምር እንዲሁም ድርቀት እንዳይመጣ የሚከላከሉ ምግቦችን በመመገብ እና ቅባት በመቀነስ በተጨማሪ የተሰጣቸውን መድኃኒት በአግባቡ በመውሰዳቸው ከኪንታሮት በሽታ ተላቀቁ።

ዘውዴ ግን ሥራ ቀርቶ ቤት መዋል ከጀመረ ውሎ አድሯል። ገብረየስ እና መንግሥቱ ምንም እንኳ ቤታቸው ከዘውዴ በእጅጉ የራቀ ቢሆንም፤ ሕመሙ እንደፀናበት ሲሰሙ ሊጠይቁት ቤቱ ድረስ ሔዱ። ገብረየስ ገብረማሪያም እና መንግሥቱ፤ ዘውዴን በደንብ ተረድተውታል። ነገር ግን የዘውዴ ሕመም በጣም የከበደ መሆኑ ትንሽ ግር አሰኝቷቸዋል።

መንግሥቱ ገና እንደገባ፤« ወንድሜን ምን ነካህ? » አለው። ዘውዴ እንደምንም ከተኛበት ቀና ብሎ «ጋዜጠኞችን ሰምቼ ጉድ ሆንኩኝ» እያለ ለሰላምታ እጁን ዘረጋ። ገብረየስም በበኩሉ፤ «አይዞን ! ምን ጉድ ነው ? ... ይሔ ነገር ከባድ በሽታ ሆነብህ፤ ለመሆኑ ሕክምና ቦታ ሔደሃል?» ሲል ጠየቀው።

ዘውዴ ሕክምና ቦታ ሄዶ ነበር። ነገር ግን ኪንታሮቱን ለማስወገድ ቀዶ ጥገና ያስፈልግሃል በመባሉ ሕክምናውን አቋርጦታል። ስለዚህ የሕክምና ክትትል አድርጌያለሁ ወይም አላደረግኩም ለማለት ተቸገረ። በግልፅ ሐኪም ቤት ሄዶ የተባለውን አልነገራቸውም። «የባሕል ሕክምና አድርጌያለሁ። ነገር ግን ከመሻል ይልቅ ጭራሽ ባሰብኝ። » ሲል ምላሽ ሰጠ።

መንግሥቱ በስጨት አለ። «አንተ የተማርክ እና ብዙዎችን የምታስተምር ሰው ሆነህ እንዴት የባሕል ሕክምና ለመውሰድ ተነሳህ?» ሲል በቁጣ ድምፅ ጥያቄ አቀረበ። ዘውዴ አልጋ ላይ መቀመጥ እንኳ አቅቶት ነበር። ከዘውዴ ቀድሞ ገብረየስ ምላሽ ሰጠ። «የባሕል ሕክምና ምንም አያድንም ብለህ እንዳትከራከር። » ሲል ተግሳፅ በሚመስል ድምፅ ተናገረ።

መንግሥቱ «እንግዲህ እንደጋዜጠኞቹ ምርጥ የባሕል ሕክምና አለ፤ በሳንጃ የተወጋን እናድናለን፤ ለሰላቢ እና ለምቀኛም መድኃኒት አለን። እያልክ ማስታወቂያ ለምን አትሠራም?» ሲል፤ ገብረየስ በመንግሥቱ ንግግር ሳያስበው ሳቁ አመለጠው። ዘውዴ ግን የመንግሥቱ ንግግር ቢያስቀውም ሕመሙ እንዲስቅ አልፈቀደለትም። ሳቁን ተቆጣጥሮ ፈገግ አለ።

ዘውዴ ከግራ ወደ ቀኝ የሚላወሰው በግድ ነው። መንግሥቱ እና ገብረየስ ሲያዩት ፈሩ እና ተያዩ። መንግሥቱ፤ « እባክህ ጓዴ ሐኪም ቤት እንውሰድህ? » ሲል ጥያቄ አቀረበ። የዘውዴ ሚስት ተዋበች በፍጥነት፤ « እባካችሁ... ሊሞት እኮ ነው። ሐኪም ቤት ውሰዱት። እኔ ሐኪም ቤት ይሻልሃል ማለት ከጀመርኩ ቆይቼያለሁ አልሰማ አለኝ። » ስትል አቤቱታ መሰል ሃሳብ በመሰንዘር ድጋፏን ገለፀች። ንግግሯ ባሏ ዘውዴ ሐኪም ቤት አልሔድም ብሎ እጅግ እንዳስቸገራት የሚያሳብቅ ነው።

ዘውዴ በበኩሉ ሐኪም ቤት መሔድ አልፈለገም። ነገር ግን የሚስቱ እና የጓደኞቹ ጭንቀት እርሱንም አስጨነቀውና ሐኪም ቤት ለመሔድ ተስማማ። ሚስቱ በፍጥነት ነጠላ ጫማ እና ጋቢ አቀረበች። መንግሥቱ እና ገብረየስ ዘውዴን ደግፈው ከአልጋ ላይ ሲያነሱ ሱሪው በደም ተጨማልቆ ነበር። መቀመጥ አቅቶት እንደምንም ሱሪውን ቀይሮ መኪና ውስጥ አስገቡት።

> **በደንብ የማይችል የባሕል ሐኪም ሕክምና አደርጋለሁ ብሎ ሲንቀሳቀስ ሰዎች ላይ ሞት ሊያስከትል የሚችል ችግር ያስከትላል**

መንግሥቱ እና ገብረየስ በዘውዴ መታመም ይበልጥ ተሳቀቁ። ሚስቱ የእነርሱን ሁኔታ እያየች በመሸማቀቅ « የባሕል ሕክምና እያለ ለመሞት ጫፍ ደረሰ እኮ!» አለች። በመኪና ተከታትለው ኮሪያ ሆስፒታል ደረሱ። መንግሥቱ ፈጠን ብሎ ካርድ አወጣ። ዘውዱ ጭራሽ ባሰበት። በዊልቸር ሐኪም ፊት ቀረበ። ሐኪሙ አስፈላጊውን ምርመራ ካካሄደ በኋላ፤ ዘውዴ ተኝቶ መታከም እንዳለበት እና መለስ ካለለት በኋላ ቀዶ ጥገና እንደሚደረግለት ተናገረ።

ሐኪሙ ሚስቱ ተዋበችን ጠርቶ፤ «የሚዲያው ማስታወቂያ ሰምታችሁ መጠኑ የማይታወቅ ነገር መድኃኒት ነው በሚል ሲሰጠው እና እርሱም አምኖ ተቀብሎ ሲቀባ ሰውነቱ በስብሶ ሞት አፋፍ ላይ እስከሚደርስ ምን እየሠራሽ ነበር?» ሲላት የምትሰጠውን መልስ አጣች።

መንግሥቱ ለዘውዴ ሕክምና ከፍተኛ ገንዘብ ቢጠየቅም ከመክፈል ወደ ኋላ አላለም። ክፍያውን ጨርሶ፤ ዘውዴ አልጋ ያዘ። ወዲያው ግሉኮሱን ጨምሮ የመድኃኒት መዓት ታዘዘ። ነርስ እና ሐኪሞቹ በጥድፊያ ይንከባከቡት ጀመር። « አይ ገንዘብ ደጉ፤ ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ» እንደሚባለው፤ ቅልጥፍና የተሞላበት እንክብካቤ ሲደረግለት፤ እነመንግሥቱ ዘውዴ ሕክምና እያገኘ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ የዘውዴ ሚስት ምግብ እንድትበላ እና እነርሱም አረፍ ለማለት ከሆስፒታሉ ወጥተው በአቅራቢያው ወደሚገኝ ምግብ ቤት መሄድ ጀመሩ።

ወደ ምግብ ቤት በዝግታ ሲራመዱ፤ ገብረየስ ከመንግሥቱ እና ከተዋበች መሐል ሆኖ ሁለቱንም እጆቹን ሁለቱም ኪሶቹ ውስጥ ጨምሮ በዝግታ አቀርቅሮ እየተራመደ «የባሕል ሕክምና መጥፎ አይደለም። ነገር ግን ሕክምናውን መስጠት ያለበት ትክክለኛ የባሕል ሕክምና በሚያውቅ ሰው ብቻ ነው። እነቻይና በባሕል ሕክምና ትልቅ ውጤት አምጥተዋል። በዩኒቨርስቲዎቻቸውም ሳይንሳዊ ሳይሆን የባሕል ሕክምናን ብቻ ለ10 ዓመታት የሚማሩ እና የተማሩ የባሕል ሐኪሞች አሏቸው።

በኢትዮጵያ ግን የባሕል ሕክምናው የሚተላለፈው በውርስ መልክ ከአባት ወይም ከእናት ወደ ልጅ ነው። ልጅ ደግሞ ፍላጎት ላይኖረው ይችላል። በተጨማሪ ቢያለማምዱትም በደንብ ላያውቅ ይሆናል። በደንብ የማይችል የባሕል ሐኪም ሕክምና አደርጋለሁ ብሎ ሲንቀሳቀስ ሰዎች ላይ ሞት ሊያስከትል የሚችል ችግር ያስከትላል።» አለ። ተዋበች ምንም አላለችም። መሬት መሬት እያየች እርሷም ከባሏ ጓደኞች ጋር እርምጃዋን ቀጠለች።

መንግሥቱ «በምንም መልኩ የባሕል ሕክምና ብሎ ነገር አይዋጥልኝም። ሙሉ ነገሩ ድፍረት የተሞላበት ነው። በዕውቀት ሳይሆን በድፍረት ሐኪም ነኝ ብሎ መድኃኒት ማዘዝ ማዳን ሳይሆን መግደል ነው። ...» ብሎ ያጋጠመውን ሊናገር ሲል፤ ገብረየስ ዕድል አልሰጠውም።

«በጭፍን መደገፍም ሆነ መቃወም ትክክል አይደለም። የባሕል ሕክምና ላይ ጥናት እና ምርምር በማካሄድ ከሳይንሱ ጋር አዋሕዶ ሕክምና የሚሰጥበትን ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም። ከዛ ውጪ ሕጋዊ ማረጋገጫ እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸትም ያስፈልጋል። በደፈናው ይቅሩ ማለት ያለንን ትልቅ ሃብት እንደማባከን ወይም እንደማጣት ነው። በሳይንስ ያልተገኙ ብዙ መድኃኒቶች በባሕላዊ መንገድ ተገኝተው ስንቱን በሽታ እየፈወሱ ነው የሚለውን ማወቅ የግድ ነው። » በማለት ገብረየስ መንግስቱን ለመገሰፅ ሞከረ።

ወደ ምግብ ቤቱ ገብተው ሲቀመጡ፤ ተዋበች « አሁን አሁን በየመገናኛ ብዙኃኑ የሚተዋወቀው የባሕል ሕክምና ብቻ ይመስላል። የታመመ ሰው ደግሞ የሚፈልገው መዳን ነው። ማስታወቂያውን አይቶ ምናልባት እድን ይሆናል ብሎ ይጓጓል። በሚዲያ የተነገረ ሁሉ እውነት የሚመስለው ብዙ ሰው አለ። » አለች።

ገብረየስ በበኩሉ፤ «በእርግጥ ሚዲያዎቹ የሚያዩት የሚከፈላቸውን ገንዘብ ብቻ ነው። ሕጋዊ ማረጋገጫ የሌለውን ተቋምም ሆነ አገልግሎት እንዳያስነግሩ ለእነርሱም መመሪያ መስጠት ያስፈልጋል። የዘውዴ መጥፎ አጋጣሚ ነው። ነገር ግን ደግሞ ብዙዎች በሳይንሳዊ ሕክምና ሳይድኑ በባሕላዊ መንገድ ታክመው የዳኑ ብዙ ናቸው። » አለ።

ምግብ ካዘዙ በኋላ፤ መንግሥቱ፤ «እኔ ለባሕላዊ ሕክምና ጥላቻ ያደረብኝ እንዲሁ በደፈናው በጭፍን አይደለም። አብሮ አደግ ጓደኛዬን ያጣሁት በዚሁ ምክንያት በመሆኑ ነው። መድኃኒት ብለው ቀምመው ሲሰጡት የነበረው ነገር ለሞት አበቃው። አሁንም ሐኪሞቹ እንደተናገሩት ዘውዴ ከዚህ በላይ ቢቆይ ኖሮ ለሞት ይቀርብ ነበር። በተጨማሪ አሁንም ቢሆን ቁስሉ አስጊ ነው። የካንሰር ምርመራ እናደርግለታለን እያሉ ነው። በጊዜ ዘመናዊ ሕክምና ባለመውሰዱ ከፍተኛ ዋጋ ሊከፍል ይችላል። ይህ እየታየ ባሕላዊ ሕክምናን መውደድ ለእኔ ጤነኝነት አይደለም። » ሲል ምላሽ ሰጠ።

መንግሥቱ ቀጠለ፤ «ሰው ያለው አቅም ውስን ነው። ቅድም እንደነገርኳችሁ ለበሽታዎች ሁሉ መድኃኒት አለን እያሉ ማስነገር፤ ለማለት ያህል እንጂ በዓለም ላይ ያሉ ታዋቂ የሕክምና ባለሙያዎችም ለመላው ሕመም መድኃኒት አለን አላሉም። እንኳን ለመላው ለሁለት እና ለሦስት ሕመም እንኳ ተለማምደው፤ ከሌሎች ተሞክሮ ወስደው፤ ምርምር አድርገው ሂደቱን ጨርሰው መድኃኒት ለመስጠት ብዙ ጊዜ መውሰዱ የማይቀር ነው። ስለዚህ ለእኔ ከላይ እንደጠቀስኩት ባሕላዊ ሕክምና ብሎ ነገር ድፍረት የተሞላበት በስህተት የታጀበ ሰዎችን ማወናበጃ እና ገንዘብ የመሰብሰቢያ መንገድ ነው።» በማለት ሃሳቡን ደመደመ።

ገብረየስ በበኩሉ፤ «አንተ በእርግጥም ጭፍን ጥላቻ ውስጥ ነህ። ዳማከሴ ለብዙ ነገር መድኃኒት ሲሆን አይቻለሁ። በተደጋጋሚ እኔም ሞክሬው ሐኪም ቤት ሳልሔድ ድኛለሁ። ዝንጅብል እና ነጭ ሽንኩርት፤ ጥቁር አዝሙድ እና ፌጦን የመሳሰሉ ባሕላዊ መድኃኒቶች ባሉበት ሀገር ሳይንሳዊ ሕክምናን ብቻ ሙጥኝ ማለት ትርፍ የለውም። ሁሉንም በልክ ማየት ያስፈልጋል። » አለ።

ተዋበች እንደመንግሥቱ የባሕል ሕክምና መልካም ነው ብላ አታምንም። እርሷም በተመሳሳይ መልኩ የኪንታሮት በሽታን በባሕላዊ መድኃኒት እናጠፋለን በሚሉ አወናባጆች የአጎቷ ሕይወት እንዲጠፋ አድርገዋል። ባሏም የአጎቷ ዕጣ እንዳይደርሰው ሰግታለች። ተዋበች የአጎቷን ተሞክሮ ለእነገብረየስ ነገረቻቸው።

የተዋበች አጎት ለሕመሙ ብሎ የወሰደው የባሕል መድኃኒት ሰውነቱን አበስብሶት ሐኪም ቤት ሲሔድ፤ መፀዳዳት ተስኖት የበላው ምግብ ሆዱ አካባቢ በጎን በኩል ተቀዶ በቱቦ ሲጠቀም እንደነበር አስታውሳ ሁኔታውን እያንገሸገሻት ነገረቻቸው። ይህ ነገር ባሏም ላይ እንዳይደርስ ፀሎት ስታደርግ መቆየቷን እና በኋላም እነርሱ መጥተው ሐኪም ቤት ስላደረሱት መደሰቷን ገልፃ ለሁለቱም ምስጋና አቀረበች።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# ትዝታና ስንብት

ሙሉጌታ ብርሃኑ

“በድንገት ያለፈውን ጊዜ በትዝታ
ባስበው ተጉዤ ወደኋላ
እንባ ባይኔ ሞላ”

ይህ የትዝታ እንባ ደርሶ ዛሬ ላይ እኛኑ ሆድ ሊያባባን ይመስላል። መሄድ በራሱ አንድ ሆድ የሚያስብስ ነገር አለው። ትዝታን ጥሎ መሄድ ደግሞ ይባስ ፍቅር የወለደው መከፋት ይወራል። በትዝታ ዳር ድንበሩ ሁሉ ሰፍሮ፣ ለዘመናት ስሜታችንን ሲንጠው ከቆየ በኋላ አሁን በቃኝ ስንብትን ሽቻለሁኝ ሲለን ጊዜ ባር ባር ቢለን እውነት አለን።

ከእንግዲህ ወዲያ ከአዳዲስ ትዝታዎች ጋር ልንመለከተውና ልናደምጠው እንደማንችል እያሰብን በሀሳብ ትዝታ ብንብከነከን ግድ የሆነው እውነታ አንዳች ጎዶሎ ስሜት ሊጥልብን ሁሉ ይችላል። ምክንያቱም ትዝታን የምንወድ ሁሉ ንጉሷን ከፊታችን ለማጣት አንፈልግምና። በትዝታ ነግሦ ያነገሣት ጌታዋ ግን በቀሪ ዘመኑ እፎይታን ተመኝቷል። ግን ትዝታ አባዜ ናትና እንዲሁ እንደዋዛ በይ ደህና ሁኚ ለማለት አይቻልም። ቀኑ ሲገፋ ደግሞ ትዝታ ታይላለች።

እድሜ ከኋላ ተነስቶ ድክ ድክ ሲል፣ ወደ ጀንበር መጥለቂያ ሲገሰግስ ትዝታውም ይበረታል። ኖረው ኖረው አመሻሹ ላይ ከተራራው አናት የምትታየው ወርቃማ ጀንበር ልብን በትዝታ ታላውሳለች። የመጡበት መንገድ፣ ያለፉት ትናንት ዛሬ ላይ ቆመው በትውስታ የሀሳብ በረሃ ሽቅብ እየወጡ፣ ቁልቁል መውረድ ነው።

ትዝታ ጣፋጬ የምናብ ፈገግታና ስቅታ ናት። ማንም ሊመለከታት የማይችል፣ የብቻችን የሆነች የሰላም ውቅያኖስ፣ የህይወታችን አድማስ ናት። እዚህ ከራስ ጋር በትዝታ ሲነጉዱ ልባችን በሀሴት ይጥለቀለቃል። አዕምሯችን በፈገግታ ይፍነከነካል። ኋላ ዞረን በሄድንበት ሩቅ መንገድ ፊት አሻግረን እንመለከታለን።

ሰማይ ከደመና፣ ተራሮችም ከምድር አይጋርዱንም። ታዲያ በዚህ ዓለም ላይ መንግሥት ማለት ከመታደል ሁሉ በላይ ነው። ይሄው ንጉሥ ግን ዙፋኑን ማውረስ ተመኘ።

ስሙን ሳይጠሩ ይህን ንጉሥ ካላወቁ እርሱ “ዝምታ ነው መልሴ” ሲል እኔም “ትዝብት ነው ትርፉ” ብል እውነት አለኝ። ትዝታና ፍቅርን፣ ህይወትና ሙዚቃን እንደ ጢቢኛ በአንድ ጠፍጥፎ ያበሰለ፣ እንደ መሀሙድ አህመድ ያለውን ፈልጎ ለማግኘት የሚቻል አይመስለኝም።

ትዝታ ከአራቱ የሀገራችን የሙዚቃ ቅኝቶች አንደኛዋ ናት። ትዝታ ከዘመነ መሀሙድ አስቀድማ የነበረች ናት። ትዝታን ያላንጎራጎረ እውቅ ድምጻዊ የለም። ታዲያ ግን ከዚህ ሁሉ ነገር መሃል አልፎ የትዝታው ንጉሥ መሀሙድ አህመድ የሆነው እንዴትስ ነው? እርግጥ ነው ከመሀሙድ በፊት አስቀድማ ትዝታ ተወልዳ ነበር። ግን መሀሙድ ላይ ደርሳ ዳግም በእርሱ መወለድ አማራት። ዘመናይ ሆና ከዘመኑ ጋር መሽቀርቀርን ስለሻተች “አባቴ ሁን?” ስትል ጠየቀችው።

“ትዝታዬ ለኔ ትዝታዬ ላንቺ
የሚሏት ዘፈን የሚሏት ዘፈን
ታጫውተኛለች ብቻዬን ስሆን”

በቃ እርሱም ያለ እርሷ ለመኖር የማይቻለው መሆኑን ገለጸላት። እርሱ ሙዚቃን ብሎ አንድ እርምጃ ባነሳ ቁጥር ሁሉ ፊቱ ድቅን የምትለው ትዝታ ናት። ይሄዳል በትዝታ። ይቆማል አሁንም በትዝታ። ደግሞ ጥቂት ያስብና ቃል ያወጣል በዚህቹ ትዝታ። መነሻውም፣ መድረሻውም እሷ ብቻ ናት።

“በትዝታ ቅኝት በሀሳብ ተጉዤ
ይሄው ለዚህ በቃሁ
ስንቱን ነገር ይዤ”

ይሄው ነው ህይወት ሙሉ ትዝታው። ይሄው ሰው ነው ዛሬ ከትዝታ ደጃፍ መሄዴ ነውና ስንብቴን ባርኩልኝ ያለው። አዲስ ነገር ሳንጠብቅ በሰጠን ብቻ ስናንጎራጉር ልንኖር ነው። እድሜ የሚሏት አጭር ገመድ፣ እርጅና የሚሉት ክፉ መንገድ መጥቶ ፊት ተደነቀረና መድረክ ለቆ፣ ትዝታን ተሰናብቶ መሄዱ ግድ አለው። “ምነው ትዝታ ሲሄድ አንቺም ጨክነሽ ዝም አልሽ?” ቢሏት “መሸ በሩን ዝጉት ከቀረ ልማዴ፤ እርሱንስ ስሸኘው ቅር እያለው ሆዴ” ነበር ምላሽዋ።

ታዲያ ይህ ሁሉ ስንብት ምንድነው? ወዴትስ ነው



ሽኝቱ? የሚሸኝስ ማነው? ጉዳዩ እንግዳ ነው። ከዚህ ቀደም እንዲህ ያለውን የስንብት አጀብ ሰምተንም ሆነ ተላምደን አናውቅም። ከሁለት ሳምንት በፊት ግን የሰማነው ይህንኑ ነበር። እንደሚታወቀው የክብር ዶክተር አርቲስት መሀሙድ አህመድ ትዝታውን አዝሎ በሙዚቃው የተራራ አናት ሲወጣ፣ በሃሳብ ስምጥ ሸለቆ ሲንደፋደፍ፣ በኮረብታው ሲያስተክዘን ደግሞ በሜዳው ፈገግ ሲያሰኘን፣ በስሜት ጫካው አብሮ ሲያስማስነን እልፍ የትዝታ ዘመናት አልፈው እርሱም ድክም ብሎታል።

እድሜው እየገፋ በእርጅና ወጥመድ ስር ለመውደቁ አናቱ ላይ የሰፈሩት ሽበቶች ይናገራሉ። ካደለን ሁላችንም ተያይዘን ወደዚያው ወደሚሄድበት ነን። እርሱ ግን የሙዚቃን ዳገት ከዚህ በላይ የመውጣት አቅሙ በመሚጠጥ ላይ ስለሆነ ቀሪ ዘመኑን በእረፍት ለማሳለፍ ወስኗል። ከሙዚቃው ውጣውረድ ተገሎ ለራሱ ህይወት፣ ራሱን የሚያደምጥበት የዝምታ ጊዜ አስፈልጎታል። ደግሞም ያስፈልገዋል።

ግን ውለታው ከንቱ፣ ድካሙም መና፣ መልሱም ዝምታ እንዳይሆን አድናቂ ወዳጆቹ አልፈቀዱለትም። ብዙዎች ያላገኙትን ትልቅ ዕድል አግኝቶ በህይወት ሳለ ወግ ማዕረጉን ሊያይ ነው። እናም እስከዛሬ ድረስ በሙዚቃ ህይወቱ ላበረከትልን ምስጋና፣ ለውለታው ታላቅ ክብር፣ ለቀሪ ዘመኑ መልካም ምኞታችንን ገልጸን፤ እርሱን ለመሰናበት የታሰበ ልዩ ዝግጅት የሚጠብቀው ጥር 3ቀን2017 ዓ.ም ነው።

ታላቁ የጥበብ ሰው የቀሪ ዘመን የእረፍት ሻንጣውን ሸክፎ ለስንብት ሲሰናዳ በዝምታ የሚተወው የለም። ትክክለኛው ነገር በትክክለኛው ሰው ተጀምሯል፤ ያለፈው የሚያሳዝን ቢሆንም። ይህን መሰል የስንብት መድረክ ለማዘጋጀት እድሜ ጌታው ነው። በሥራ ላይ ናቸው ብለን “አሉ...አለሁ” እያሉም ድንገት አለመኖር ይከሰታል። በጉብዝና ወራት ላይ ያለውን “እንሰናበትህ” ሊሉት ስለማይችሉ ስንብቱም መቃብር ላይ በጉንጉን አበባ ይሆናል። ቢኖርም በእድሜ ገና ሳሉ ለተለዩን ጸጸቱ ስንብትን የማያካትት ይሆናል።

ሆኖም ግን በእርጅናም ይሁን በሌላ ወደ መጨረሻው ማክተሚያ መዳረሳቸውን እያወቅን በዝምታ የሸኘናቸውም ቀላል አይደሉም። ለአብነትም፤ ከድምጻዊያኑ የክብር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠን እንኳን ብንመለከት አሳዛኙን አካሄድ ነበር የሄደው። ሰውነቱ በድን ሆኖ አስክሬኑ ወደ መቃብር ሲሸኝ ቢናገረው ኖሮ ምናልባትም በመሀሙድ ሙዚቃ እንዲህ ባለ ነበር፤

“ለዋልኩት ውለታ ይሄ ነው ወይ ውርሴ
ልፋቴ ድካሜ ይሄ ነው ወይ ውርሴ
እንግዲህ ምን ልበል ይህ ከሆነ ቅርሴ
አሀሀሀ ዝምታ ነው መልሴ”

በእርግጥም የሞተ ሰው ጩኸቱም በዝምታ ነው። ፍርጃም ቢሉት እጣ ፈንታ የዛሬውን ውዳሴ ያገኘውም መቃብር ከዋለ በኋላ ነበር። መሀሙድንም ከሚያብከነክኑት ነገሮች አንዱ ይሄው የጥላሁን ጉዳይ ነው። ታላቁ ድምጻዊ ያጣውንና የተነፈገውን በማስታወስ ምን ያህል እንደሚያንገበግበው ሲናገርም ሰምተን ይሆናል። ይሁንና ለትንሽ ትልቁ አሳቢነቱና ተቆርቋሪነቱ መሀሙድ ዛሬ ላይ እንዲታሰብለት አድርጎታል። “ነግ በኔን” በቅጡ የተረዳ ውለታ አብሳይ ነው።

የክብር ዶክተር አርቲስት መሀሙድ አህመድ የአንድ የራሱ ብቻ የሆነ የጥበብ ሰው አይደለም። ገሚስ ማንነቱና ህይወቱ ዙሪያው ለተሰበሰቡት አድናቂና ወዳጆቹ ነው። እነርሱም ለእርሱ ያላቸው ክብርና ታማኝነት ከየትኛውም ደቀመዝሙር የተለየ ነው። በጥቂቱ ከዚህ ቀደም ያደረጋቸው ኮንሰርቶችን ማጤን በቂ ነው።

ለኮንሰርቱ ታዳሚ ይበቃል ተብሎ የተዘጋጀ የመግቢያ ትኬት ገና በጊዜ እጥብ ብሎ በሽሚያ ለመግባትም የማይቻልባቸው ነበሩ። በጊዜ መፈራረቅ መካከል ሳይለዋወጡና ሳይለወጥ፣ ሲከተሉትና ሲያስከትላቸው ዛሬ ላይ ደርሰው አሁን ደግሞ ለስንብት የተሰናዱለትም እነርሱው ሆነዋል። ሥራ የጋራ ቢሆንም ሀሳብ ግን ከአንድ ጉድጓድ ሊፈልቅ ይችላል። ከሁለት ዓመታት በፊት እኚሁ አድናቂ፣ ወዳጆቹ ሰብሰብ ብለው አንድ ሀሳብ ከሰቱ። “ሁላችንም በግልጽ እንደምንመለከተው ጋሼ እድሜው ገፍቶ፣ ከእረፍት ዘመኑ ላይ ተቃርቧል። ስለዚህ አንድ የስንብት መድረክ ብናዘጋጅስ” የተባባሉ ይመስለኛል።

ይሄን መሰሉ ቅዱስ ሀሳብ የማይታለፍ ነበርና በሀገራችን ያልተለመደ ቢሆንም በውሳኔ ቆርጠው ገቡበት። የወተት ላምን ከወደዱ ከነኩበቷ ነውና ሊገጥማቸው የሚችለውን ከነ ፈተናው ለመቀበል ተዘጋጅተው ገቡበት። ጥቂቶችም ተመራርጠው ኮሚቴ አዋቀሩ። “ይህን ጉዳይ ይዘን የተለያዩ ሰዎች ጋር ስንሄድ ምን ሆነ መሀሙድ ሲሉ ይጠይቁናልና ለመከበር ምንም መሆን የለበትም። ጋሽ መሀሙድ እኮ ታላቁን የሚያከብር ሰው በማይገኝበት ዘመን ታናሹን የሚያከብር ሰው ነው” ሲል ከኮሚቴዎቹ መካከል አንዱ የሆነው፣ እውቁ የሙዚቃ ባለሙያ አብርሃም ወልዴ ነበር የተናገረው።

እናም ያሰቡት ሰምሮ፣ የዘሩት አሽቶም ከሁለት ዓመታት ድካም በኋላ በጥር 3 ቀን እውን ሊሆን ነው። የልፋትን ፍሬ መብላት እንዴት ያለውን ሀሴት የሚቸር መሆኑን ከእነርሱ የተማሩም ነገ በሌላ ታላቅ ሰው መቀጠሉ አይቀርም። እነርሱ ግን ፊተኞች ሆነው አስቀድሰውታል።

“የክብር ዶክተር አርቲስት መሀሙድ አህመድ ከክብር ክብር! ክብር! ክብር! ይገባዋል በማለት አድናቂና ወዳጆቹ ተሰባስበን ኮሚቴ በማዋቀር ላለፉት ሁለት ዓመታት የተለያዩ ሥራዎችን ስንሠራ ቆይተናል” በማለት የሁለቱን ዓመታት ጉዞ፣ የአሁኑን መዳረሻና የስንብት መጀመሪያውን ኮሚቴው አስቀምጦታል። ለአርቲስቱ ስንብት ደፍ ደፍ በተባለባቸው በእኚህ ሁለት ዓመታት ምንስ ታሰበ፣ ምን ተሠራ? ሁሉንም ነገሮች ጉዟቸው ወደ ጥር 3 ነው።

ከተሠራባቸው ነገሮች አንዱ የስንብት ኮንሰርት ነው። ኃላፊቱን ከኮሚቴው ወስዶ በሰፊው ሲንቀሳቀስበት የቆየው ጃርካ የሁነት አዘጋጅ ተቋም ዝግጅቶቹን በጥራት ስለማገባደዱ ጥቅምት 22 ቀን 2017ዓ.ም ከኮሚቴው ጋር ሆኖ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫው አስታውቋል። በሁለተኛነት የታላቁን የጥበብ ሰው የህይወት ታሪክ የሚዳስስ መጽሐፍ ሥራው ተጠናቆ ለንባብ የሚበቃ ይሆናል።

ከዚህ ቀደም የክብር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠን የህይወት ታሪክ ጽፎ የነበረው ጋዜጠኛና ደራሲ ወሰን ደበበ አሁን ደግሞ የመሀሙድን ህይወት ከልጅነት እስከ ሽበት፣ እንዲሁም የሙዚቃ ህይወቱን በሰፊው የሚተርከውን መጽሐፉን አጠናቆታል። በሁለቱ ዓመታት ውስጥ ሲለፋባቸው የከረሙ ሌሎች ሦስት ጉዳዮች ደግሞ መጨረሻቸውን በጥር 3ቱ መድረክ ይፋ የሚደረጉ መሆናቸውን ኮሚቴው ተናግሮታል።

በመንግሥት ደረጃ ተቀባይነትን አግኝቶ ስፍራ ያልተወሰነለት አንደኛው ጉዳይም በስሙ መንገድና አደባባይ ማሰየም ነው። ምናልባትም ደግሞ “መሀሙድ ጋር...” እንደሚሆን ይጠረጠራል። በሂደት ላይ ያለው ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ ምስለ ቅርጽ ማቆም ነው። በህይወት ሳለ ይህን የራሱን ምስለ ቅርጽ ቆሞ የተመለከተ ዕለት ለርሱም ለሌላውም ትልቁ የህይወት ዘመን ስኬት ይሆናል። ይህ ሁሉ ሲሆን ታዲያ መሀሙድስ ተቀብሎ ብቻ ሊወርድ? አያደርገውም! በእርግጥም አላደረገውም። የመጨረሻውን የሙዚቃ ስጦታ፣ የትዝታውን መታወሻ ሲዲ ያበረክትልናል። ለዕለቱ መድረስ አለመድረሱን ኮሚቴውም እርግጠኛ ባይሆንም አዲሱን ገጸ በረከቱን በቅርቡ ልናደምጥ መሆኑ ግን እሙን ነው።

ጥር 3 የትዝታውን ንጉሥ በክብር ለመሸኘት ወገቧን ታጥቃ፣ መቀነቷን አስራ ከወዲሁ ሽር ስትል እንዳለች ታሳብቃለች። ሁሌም መታወሻው ሆና ስለምትኖር ለርሷም ቢሆን ትልቅ ዕድል ነው። ከቀናት ሁሉ ልዩ ቀን ለመሆን በመብቃቷ ኩራትም ደስታም እንዳፈናት ግልጽ ነው። ከአመሻሹ ላይ ግን የእንባ ሲቃ ሳይተናነቃት አይቀርም። ስንብቱ ብቻ ሳይሆን እንዲያ ፈክታ የዋለችባቸውን ሰዓታት ጥር 4 ደርሶ ሊቀበላት መቃረቡን ስታስብ የእውነትም ቅር ሊላት ይገባል።

ጥር 3 ቀን 2017ዓ.ም ሚሊኒየም አዳራሽ፣ መሀሙድና ጥር 3 ትልቁ የዘመን ግጥምጥሞሽ ይሆናሉ። ዕለቱስ ምን ያስመለክተን ይሆን? መሀሙድ የዚያን ዕለት መድረክ ቆሞ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ትውልዱን ይሰናበታል። ጥበቡን ከአደራ ጋር ያወርሳል። የተሰማውንና ለዘመናት ሲሰማው የነበረውን ይናገራል። ብዙዎች ከአዳራሹ ሆነው በደስታ ወይ በእንባ ያደምጡታል። የሚናገረውን ተናግሮ፣ የሚመክረውን መክሮ፣ የሚዘክረውን ይዘክራል። ትዝታውን እያወጋን፣ ትዝታውን ጥሎብን ይወርዳል።

ዝግጅቱ ለመሀሙድና የመሀሙድ ቢሆንም ብቻውን ተናግሮ፣ ብቻውን ዘፍኖ፣ መድረኩን ለብቻው አይጨርሰውም። ሌሎች ዝግጅቶች እንዳሉ ሆነው በዕለቱ ከሚቀርቡት አንዱ ሙዚቃ ካልሆነማ የስጋ ነጋዴውን ሰርግ በሽሮ እንደመሰረግ ነው። ከዳቢቱም፣ ከምላስ ሰንበሩም፣ ብርንዶውን ካልቆረጡማ ምኑን ተሰረገ...ታዲያ እነማን ይሆኑ የተመረጡት ሚዜዎች? ብለን ማሰባችን አይቀርም። ይሁንና የኮንሰርቱ ቀኛዝማች ጃርካና የድግሱ ፊታውራሪው ኮሚቴ በይደር ይዋል ሲደርስ እንገልጻዋለን ብለዋል።

ነገር ግን የሙዚቃ ድግስ ስለሆነ ብቻ ማንም ና! ውጣ የሚባልበት መድረክ አለመሆኑን አበክረው ተናግረውታል። “ራሱን መሀሙድን የሚመጥን ድምጻዊ ሊሆን የግድ ነው” ሲሉ ይበልጥ መድረኩ ላይ የሚወጣውን ድምጻዊ ዳጉተን እንድንጠብቀው አድርገውታል። እነርሱ እንዲያ ቢሉም መገመት አያስነውርምና እኛ ግን አንደኛውን እንገምታለን። የመገመቱን ዕድል ከሰጣችሁኝ ዘንዳ ምናልባትም ከመሃከል አንደኛው ጎሳዬ ተስፋዬ ይሆናል እላችኋለሁ። እንዴትስ እሱን ልትል ቻልክ ያላችሁ እንደሆን ግን... ድምጻዊ ጎሳዬ የተቀዳው ከመሀሙድ አህመድ የትዝታ ወንዝ ላይ ነው።

ከላይ መግቢያው ላይ መሀሙድ ከጀመራት የትዝታ ስንኝ ጎሳዬ ይቀጥልባታል።

“...ይቅርና ማሰብ በትካዜ
አጫውተኝ ስላለፈው ጊዜ” ይለዋል።

ትዝታን በአደራ፣ ጥበብን በፍቅር እንጀራ ይጎራረሳሉ። ጎሳዬ ለመሀሙድ ጋቢውን ሲደርብለት ያለችዋንም ቅጽበት አንረሳትም። አንዱ ጥበብ አውራሽ፣ ሌላውም ክብር አልባሽ ነው። ጥር 3 ግን ሚሊኒየም አዳራሽ ጀንበር አትጠልቅም።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ራስን ሰጥቶ ሌሎችን ማትረፍ

ቤዛ እሸቱ

ከህመሟ በላይ “እኔ ብሞት ልጄ ምን ትሆናለች?” የሚለው ያሳስባታል። ልጇ እሷን ለማስታመም አብራት ስትንከራተት ከትምህርቷ ተስተጓጉላለች። “እናቴን በሞት ላጣ ነው እያለች ስታስብ እንደኔ ከሰውነት ተርታ ወጣች” ስለምትላት የመጨረሻ ልጇ ትጨነቃለች። ወይዘሮ ወይዘር ማሞን ያገኘናት ከልጇ ጋር ባረፈችበት ዓለም ፍሬ ፒንክ ህውስ ካንሰር ፋውንዴሽን ነው። ያለፉትን አራት ዓመታት በመሃል ወደ ሀገሯ ራያ ቆቦ ብትሄድም አብዛኛውን ጊዜ በማእከሉ አሳልፋለች፡፡

ወይዘሮ ወይዘርን ከመንደሯ አርቆ ወደ አዲስ አበባ ያመጣት የማህጸን በር ጫፍ ካንሰር ህመም ነው። መጀመሪያ ከማህጸንዋ ያልተጠበቀ ደም መፍሰስ ጀመረ፤ የወር አበባ ማየት ካቆምኩ አምስት ዓመታት በኋላ እንዴት ይሄ ሆነ ? ስትል በአቅራቢያዋ ወደሚገኝ የጤና ተቋም አመራች። ህመሟ ከህክምና ተቋሙ አቅም በላይ በመሆኑ ወደ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሪፈር ተጻፈላት። “ምን መጣብኝ” በሚል ድንጋጤ በእንባ ታጅባ ወደቤቷ ተመለሰች። በወቅቱ በሥም እንጂ በአካል ከማታውቀው አዲስ አበባ የምታርፍበት ዘመድ የላትምና አልሄድም ብላ አንገራገረች ። ሆኖም በልጇቿ ጉትጎታ ሃሳቧን ቀይራ ወደ አዲስ አበባ መምጣት ቻለች ። የማታውቃት አዲስ አበባ በጥየቃ ብትደርስም የምታውቀው ሰው የለምና ለሁለት ቀናት የጥቁር አንበሳ ኮሪደሮች ላይ ካርቶን አንጥፈው ከልጇ ጋር ማደራቸውን ታስታውሳለች ። ከዛም ማረፊያ እንደሌላት ያዩ የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ባለሙያዎች መጠለያ ለሌላቸው ችግረኛ ህመምተኞች ድጋፍ ከሚያደርግ የርዳታ ድርጅት ጋር የምትገናኝበትን ሁኔታ አመቻችተውላታል።

ይሄ ለእሷ ትልቅ እድል ነበር። ጤናዋን ያለ ችግር ለመከታተል በር ከፍቶላታል። ከቤቷ የተሻለ በልታና ጠጥታ ንጽህናዋን ጠብቃ በነጻነት እንደተቀመጠች ትናገራለች። ይህ ድርጅት ባይኖር ኖሮ እንኳን ረጅም ጊዜ ይቅርና ለሁለት ቀን ወጪዋን መሸፈን እንደማትችል ታነሳለች። በተለይ የመኖሪያ አካባቢዋ ሰላም አለመሆኑን ተከትሎ ያለሃሳብ ህክምናዋን እስክትጨርስ በድርጅቱ እንድትቀመጥ በመደረጉ የተሰማትን ደስታ ትገልጻለች ። የርዳታ ድርጅቱ መሥራች ዶክተር ፍሬሕይወት ደርሶ ነዋሪነቷ በአሜሪካ ሲሆን ፋውንዴሽኑን ለመመሥረት ያነሳሳት ዋናው ምክንያት ከ15 ዓመት በፊት እህቷን በጡት ካንሰር ማጣቷ እና ያ አጋጣሚ የሌሎች ህመምተኞች ሥቃይ እንድታይ መነሻ ስለሆናት ነበር።

የጡት ካንሰር ሕብረተሰቡ በደንብ ያልተገነዘበው ሴቶችን ግን እየገደለ ያለ በሽታ ነው። በሀገራችን በቀዳሚነት የጡት ካንሰር በመቀጠል የማህጸን ጫፍ ካንሰር ሴቶችን በመግደል ቀዳሚ መሆኑን ትናገራለች። በወቅቱ እህቷ ስለጡት ካንሰር ምንም መረጃ አልነበራትም። ሆኖም አንድ ቀን ብብቷ ስር ከወትሮው የተለየ እባጭ ትመለከታለች፤ በወቅቱ በሥርግ ግርግር እቃ ሳወጣና ሳወርድ በተፈጠረ የሥራ ጫና ነው ብላ ደምድማለች። እብጠቱ ወደጡቷ ሲሻገርም ብዙም ትኩረት አልሰጠችውም ። እያደር ግን የጡቷ እብጠት ሲጨምር ጡቷ ከበዳት፤ ሕመምም ተሰማት ። ያኔ ወደ ህክምና ተቋም ሄደች፤ በወቅቱ “ኢጢሽ ወደ ነቀርሳ ተቀይሯል” ተባለች። በሽታውን በተገቢው ልክ አልተረዳችምና የተሻለ ሊያሳክሟት ለሚችሉት እህቶቿም ሳትነግር በሚስጥር ይዛው ቆየች፡፡

ቀላል እያለ ያልገባት በሽታ ወደ ደረጃ ሁለት ሲሸጋገር በደንብ እየተረዳችው ሄደች። ቀዶ ጥገናውን ለማድረግ በወረፋ ምክንያት ረዥም ጊዜ ጠበቀች። በወቅቱ እህቷን ለማስታመም ከአሜሪካ የመጣችው ዶክተር ፍሬሕይወት ስለካንሰር በሕብረተሰቡ ዘንድ ባለው አናሳ ግንዛቤ ሰው መገለልን በመፍራት በካንሰር መያዙን እንደሚደብቅ አስተዋለች። ሕክምናውን ለማግኘት ካሉበት የገጠር አካባቢ ወደ ከተማ የሚመጡት የተወሰነ ከተማ ዘመድ ያላቸው ብቻ ናቸው። ለህክምናው የመጡት አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል ስለበሽታው ተገቢው መረጃ እንደሌላቸውና ከህክምና ባለሙያዎችም “እጢ አለብሽ፣ ነቀርሳ አለብሽ ወይም ወደ ካንሰር ተቀይሮአል” የሚል ጥቅል መረጃ ከመስጠትና የህክምና አማራጮችን ከማሳየት በዘለለ ብዙም ዝርዝር መረጃ አያገኙም። እህቷ በጊዜው ህክምና አልጀመረችምና ካንሰሩ በመሰራጨቱ ሕይወቷን አጣች። ያኔ ገንዘብ እያላቸው በወቅቱ ስለካንሰር መረጃ በማጣት እህታቸውን ካጧት ሌሎች ላይማ ችግሩ ይከፋል፤ በሚል እህቷን መታደግ ባትችልም በእሷ ሞት ሌሎች አለምጻህዮችን ለመታደግ በሚል “ዓለም ፍሬ ፒንክ ህውስ ካንሰር ፋውንዴሽን” ተቋቋመ።

ድርጅቱ በአዲስ አበባ ሥራውን የጀመረው በመንግሥት ተቋማት ክትትል ጀምረው ረዥም ወረፋ የሆነባቸውንና በግል ለመታከም አቅም የሌላቸውን የጡት ካንሰር ህመምተኞችን በግል የህክምና ተቋማት የሚታከሙበትን ወጪ በመሸፈን ነበር። ዶክተር ፍሬህይወት በቀጣይም በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የካንሰር ታማሚዎችን የህክምና ሂደት ለማየት በሆስፒታሉ ተገኘች። በወቅቱ በርካታ ህክምና ፈላጊዎች በኮሪደር ላይ ለእንግዳ ማረፊያ በተቀመጡ አግዳሚ ወንበሮች ላይ ጎናቸውን አሳርፈዋል፤ ሌሎቹ ደግሞ መሬት ላይ ካርቶን አንጥፈው ተኮራምተው ተኝተዋል። የቀኑ ውሏቸው በዚህ መልኩ ያልፍና ሲመሽ በጥበቃ ሠራተኞች ይባረራሉ። መንገድ ሲወጡም ወጪ ወራጁ ይሰርቀን ይሆን በሚል ይጨነቃሉ፤ አለፍ ሲልም የያዟትን ጥሪት መዘረፍ ያጋጥማቸዋል ። በዚህ ምሬት የያዙትን ጥቂት ስንቅና ገንዘብ አራግፈው ተገቢ ህክምና ሳያገኙ ወደመጡበት እንደሚመለሱ በመስማቷ ለዚህ ችግር መፍትሄ ማፈላለጉን ሥራዋ አደረገች ። በመጀመሪያ አነስተኛ ቤት ተከራየች፤ አስፈላጊውን ቁሳቁስ በማሟላትና ባለሙያ በመቅጠር ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል መጠለያ የሌላቸውን የጡት ካንሰር ህመምተኞችንና አስታማሚዎቻቸውን ማገዝ ተጀመረ። በማረፊያ ማዕከሉ የምግብ፣ የመጠለያ፣ የንጽህና መጠበቂያ፣ የትራንስፖርት፣ የመድሃኒትና የካውንስሊንግ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

ዶክተር ፍሬሕይወት እንደምትለው ፤ በአሜሪካ የተሻለ ስለ ካንሰር ግንዛቤና ህክምና ቢኖርም ከኢትዮጵያ የሄዱት አብዛኞቹ ችግሩን በጥልቀት የተረዱት አልነበሩም። አብዛኞቹ እናቶች ኢንሹራንስ ኖሯቸውም በጊዜ ወደ ህክምና ተቋም አያመሩም። “እናቶች እነሱ ሲኖሩ ነው ሥራ የሚሠሩት ፣ ልጆቻቸውን የሚያሳድጉት ነገር ግን በሽታው እንዳለባቸው እያወቁም ልጄ እስኪመረቅ፣ እዚ ደረጃ እስኪደርስ/እስክትደርስ ለማንም አልናገርም በማለት ያጋጠማቸውን ችግር ይደብቃሉ፡፡” ትላለች።

ፋውንዴሽኑ ይህንንና መሰል ሁኔታዎችን ለማስወገድ በአሜሪካ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የምክር አገልግሎት ይሰጣል። የቋንቋ ችግር ስለሚያጋጥምም የሀኪሞችንና የላብራቶሪ ውጤቶችን በመቀበል የማስተርጎም አገልግሎት ይሰጣል። በተጨማሪም እናት ህክምና ላይ በምትሆንበት ወቅት ልጆችን ወደ ትምህርት ቤት የመውሰድና የመመለስ፣ የቤት ጽዳትና ቤት ኪራይ እስከመሸፈን ወጪን የመጋራት ሥራ ይሠራል ፡፡

ፋውንዴሽኑ በሀገር ውስጥ ከአዲስ አበባ በተጨማሪም በጎንደር ማረፊያ አለው። በሌሎች ከተሞች በተለያየ ጊዜ በመሄድ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራና የካንሰር ምልክት ያለባቸውን በመለየት ከህክምና ተቋማት ጋር የማገናኘት ሥራ ይሠራል። በቀጣይም በጎንደር ከከተማ አስተዳደሩ በተሰጣቸው ቦታ ላይ ትልቅ ማረፊያ የመገንባትና በሌሎች አካባቢዎች ቅርንጫፍ የመክፈት እቅድ አላቸው።

ዶክተር ፍሬሕይወት ቀጣይ ህልሟ ተንቀሳቃሽ ክሊኒክ መክፈት ነው። የትራንስፖርት ወጪ ሳይኖራቸውና ህክምና ወረፋ ሆኖባቸው በቤት ውስጥ ልሙት ብለው ቁጭ ያሉ እናቶችን መታደግ እፈልጋለሁ ትላለች። ለዚህም የሚያስፈልጋትን ድጋፍ የሚያደርግ አጋዥ ትሻለች።

# ዓለም አቀፍ



## ትራምፕና ቢሊየነሩን መስክን ሾሙ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ተመራጩ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ቢሊየነሩ ኢለን መስክን አዲስ በሚቋቋመው ተቋም ሚና እንዲኖረው ከትናንት በስቲያ ሾመውታል።

ሹመቱ ለትራምፕ እንዲመረጡ በርካታ ሚሊዮን ዶላሮች ፈሰስ ያደረገው መስክን የበለጠ ተጽእኖ እንዲኖረው የሚያደርግ ነው ተብሏል።

መስክ እና የቀድሞው የሪፐብሊካን ፕሬዚዳንታዊ እጩ ቪቬክ ራማስዋሚ ትራምፕ የተጓተተውን የመንግሥት አሠራርን በማሳጠር ቀልጣፋ አሠራር እንዲኖር ያስችላል ያሉትን አዲስ የተቋቋመውን ‘ዲፓርትመንት አፍ ገቨርንመንት ኢፊሽንሲ’ ወይም የውጤማነት ቢሮ ይመራሉ።

ትራምፕ ባወጡት መግለጫ መስክ እና ራሜስዋሚ “የእኔ አስተዳደር የመንግስት ቢሮክራሲ እንዲያፈርስ፣ ብዙ መመሪያዎችን እንዲቀንስ፣ ብክነትን እንዲቀንስ እና የፌዴራል ኤጀንሲዎችን መዋቅር እንዲያስተካክል መንገድ ይጠርጋሉ” ብለዋል።

አዲሱ ዲፓርትመንት የሪፐብሊካን የረጅም ጊዜ ህልም እንደሆነ እና “ከመንግሥት ውጭ ሆኖ ምክር እና መመሪያ እንደሚሰጥ” የገለጹት ትራምፕ የመስክ እና የራማስዋሚ ሹመት የሴኔት ይሁንታ የማያስፈልገው ይፋዊ ያልሆነ ሹመት መሆኑን አመላክተዋል። መስክም በትራምፕ ከተሰጠው ኃላፊነት በተጨማሪ የግዙፍ ማህበራዊ ሚዲያ ኤክስ፣ የቴስላ እና የስፔስ ኤክስ ኃላፊ ሆኖ እንዲቀጥል ያስችለዋል ተብሏል።

ትራምፕ እንዳሉት አዲሱ ዲፓርትመንት “መጠነሰፊ የመዋቅር ለውጥ ለማፋጠን እና የቢዝነስ አሠራርን ለመፍጠር” ከኃይትሀውስ እና ከበጀት ቢሮ ጋር ይሠራል።

ሥራው የአሜሪካ ነጻነት በታወጀበት 250ኛ ዓመት መታበሲያ ዕለት ሐምሌ 2026 ይጠናቀቃል ተብሏል።

በፎርብስ መጽሄት የዓለም ቁጥር አንድ ሀብታም ደረጃን የተቆናጠጠው መስክ ኩባንያዎቹ በትራምፕ ድል ምክንያት በተሻለ ሁኔታ እንዲታዩ ለማድረግ እየሠራ ነው።

መስክ ለትራምፕ የምርጫ ቅስቀሳ ሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ከመስጠት ባለፈ በአደባባይ አብሯቸው በመታየት ድጋፉን ገልጿል።

መስክ በመንግሥት ሥራ መሳተፉ እንደ አርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ እና ክሪፕቶከረንሲ ያሉት ኩባንያዎቹ የገበያ ዋጋ እንዲጨምር ሊረዳው ይችላል።

ዶናልድ ትራምፕ የዲሞክራቷን እጩ ካማላ ሀሪስን በማሸነፍ በድጋሚ ወደ ኃይት ሀውስ መግባት ችለዋል። ትራምፕ ለኃይት ሀውስ ኃላፊነት ጨምሮ ለበርካታ የመንግሥት የሥልጣን ቦታዎች አጋሮቻቸውን እየሾሙ እና እያጩ ይገኛሉ።

## ኢራን በአስገድዶ መድፈር ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ዜጋዋን በስቅላት ቀጣች

በጋዜጣው ሪፖርተር



ኢራን በአስገድዶ መድፈር ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ዜጋዋን በስቅላት ቀጣች፡፡

የመካከለኛ ምስራቋ ሀገር ኢራን በአስገድዶ መድፈር ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ የተባለ ዜጋዋን በአደባባይ ላይ በስቅላት ገድላለች፡፡

ሞሀመድ አሊ የተባለው ይህ ኢራናዊ የ43 ዓመት ጎልማሳ ሲሆን በርካታ ሴቶች እንደሚያገባቸው ቃል በመግባት አስገድዶ ደፍሯቸዋል ተብሏል፡፡

ግለሰቡ ባሳለፍነው ጥር ወር ላይ በፖሊስ በቁጥጥር ስር የዋለ ሲሆን ከአንድ ወር በፊት በተከሰሰበት የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች ጥፋተኛ ሆኖ እንደተገኘ አል አረቢያ ዘግቧል፡፡

እንደ ዘገባው ከሆነ መሀመድ አሊ ከ10 በላይ ሴቶችን አስገድዶ ደፍሯል የተባለ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የተወሰኑት ከእሱ የጸነሱትን ልጅ እንዲያስወርዱ መድሃኒት ሰጥቷልም ተብሏል፡፡

በምዕራባዊ ኢራን ክፍል በምትገኘው ሀሜዳን ከተማ የሚኖረው ይህ ሰው ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ 200 ሴቶች ደፍሮናል ሲሉ ክስ መስርተውበት ነበር፡፡

በግለሰቡ ተደፍረናል ያሉ ሴቶች ቁጥር መጨመርን ተከትሎ በርካታ ኢራናዊያን ሕጋዊ ርምጃ እንዲወሰድበት የሚጠይቅ ሰላማዊ ሰልፍም ተደርጎበት ነበር፡፡

ኢራን በየጊዜው በርካታ ዜጎች በስቅላት ከሚቀጡባቸው የዓለማችን ሀገራት መካከል አንዷ ስትሆን ተመድን ጨምሮ በርካታ ሠብዓዊ ድርጅቶች የሞት ቅጣት እንዲቀር በመጠየቅ ላይ ናቸው፡፡

እንደ አምንስቲ ኢንተርናሽናል ሪፖርት ከሆነ የሞት ፍርድ ቁጥር እየጨመረ የመጣ ቻይና ብዙ ዜጎቿን በስቅላት በመቅጣት ከዓለማችን ቀዳሚዋ ሀገር ስትሆን በዓመት በአማካኝ አንድ ሺህ ዜጎችን ትገድላለች፡፡

ኢራን ደግሞ በየዓመቱ ከ570 በላይ ዜጎችን በስቅላት ስትቀጣ አፍሪካዊቷ ግብጽም ዜጎቿን በስቅላት ከሚቀጡ ሀገራት መካከል ተጠቅሳለች፡፡

ሳውዲ አረቢያ፣ አሜሪካ እና ሲንጋፖር በተጨማሪነት የተጠቀሱ ሀገራት ሲሆኑ ሀገራቱ ዜጎቻቸውን በሞት እየቀጡ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

# የረሃብ ነገር ከተነሳ...!?

"ከረሃብ የፀዳች ዓለምን እውን ማድረግ ይቻላል፤" በሚል መሪ ቃል በመዲናችን ዓለም አቀፍ ጉባኤ ተካሂዷል። እውነቱን ለመናገር ጉባኤውን በሀገራችን መካሄዱ ተምሳሌታዊ ወይም ሲምቦሊክ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። አዎ ለበርካታ ዓመታት የድርቅና የረሃብ ምሳሌ ሆና ስሟ ሲወሳ በኖረች ሀገር፤ ይሄን የጠለሸ ስሟን ለማደስ ጥረት እያደረገች በምትገኝበት ወሳኝ መታጠፊያ ሀገር ጉባኤው መካሄዱ በብዙ መልኩ ተምሳሌታዊ ነው።

በጉባኤው ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ኢትዮጵያ ባለፉት 6 ዓመታት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ሰፊ ሥራዎች ማከናወኗን፤ በተለይም ባለፉት ዓመታት በ3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት የስንዴ፣ ጤፍና ሩዝ ምርትና 40 ቢሊዮን ችግኝ በመትከል ገልጸዋል። የኩታ ገጠም ግብርና ለማስፋት፣ የግብርና ሜካናይዜሽን ለማሳደግ፤ በየደረጃው መስኖን በመጠቀም ዓመቱን ሁሉ ለማልማት የተሄደበት ርቀት፤ አንድም መሬት ጦም እንዳያድር የሚደረገው ጥረት እና እየተመዘገበ ያለው አበረታች ውጤት ተስፋ የሚያሰንቅ ሆኖ እያለ ነው እንግዲህ ይሄ ጉባኤ የተካሄደው።

ታሪካችን የአልበገር ባይነት፣ የነፃነት፣ የጥንታዊ ሥልጣኔ እንደሆነው ሁሉ፤ የጦርነትና የረሃብ ጭምር መሆኑን በልኩ ማጤን የነገውን መንገዳችንን ለመትለም ያግዛል። ስለሆነም የድርቅና የረሃብ ታሪካችን መለስ ብሎ መቃኘት ያሻል። በነገራችን ላይ ረሃብ በአውሮፓ በእስያ በላቲን አሜሪካ በአፍሪካና በመላው ዓለም ተከስቷል። ረሃብ በኢትዮጵያ የተጀመረ በኢትዮጵያም የሚያበቃ አይደለም። እያንዳንዱ ሀገር የድርቅ የረሃብ ታሪክ አለው። ከዘፍጥረት ጀምሮ የሰው ልጆችን ሲፈትን የኖረ ተፈጥሯዊ ክስተት ነው። ይሄን የምለው ግን ታሪካችንን በሌላ ታሪክ ለማጥፋት ወይም ረሃብ በእኛ የተጀመረ አይደለም ብሎ ለመጽናናት አይደለም። በምንጭነት ቆየት ያለ የአዲስ አድማስ ጋዜጣን ተጠቅሜያለሁ።

የረዥም ዘመኑን ረሃብ ለጊዜው እናቆየውና የዛሬ መቶ ዓመት አካባቢ በኢትዮጵያ ስለደረሰው ድርቅና ረሃብ በተለይም በፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት መጽሐፍ የሰፈረውን ስንመለከት። በኢትዮጵያ ከደረሱት በጣም ትልቅ የድርቅና የረሃብ ዘመናት አንዱ ከ1888-1892 ማለትም አጼ ዮሐንስ በሞቱበት ጊዜ የነበረው መሆኑን እናረጋግጣለን። በዚህ ጊዜ የነበሩት የሮም ሚሲዮኖች እንደመዘገቡት፤ የአየሩ ሁኔታ ባልተለመደ መልኩ ሞቃት ሆነ። ይህም የአየር ንብረቱን አዛባው። እንደ ሰደድ እሳትም መላውን ምድር አጥለቀለቀው።

የአየር ንብረቱ መዛባት ለሱማሊያና ለደቡባዊ ሀገሮችም ተረፈ። በወቅቱ ኢትዮጵያን የጎበኘ ማርቲ የተባለ ግለሰብ ስለ ድርቁ ሲገልጽ፡-«በእራፊ አዳፋ ጨርቅ የተሸፈነ ሬሳ እዚህም እዚያም ወድቆ ይታያል። በዚያ ሐሩር ፀሐይ ላይ ወድቀው ከሚታዩት አስከሬኖች ከንዶችና እግሮች ላይ ነፍሳት ሲርመሰመሱ ማየት እጅጉን ያሰቅቃል። እንዲህ ያለው ድርቅ የተከሰተው ከ1888-1892 ብቻ አልነበረም። እንደ ማርቲን ያለ ፀሐፊ አያጋጥመው እንጂ በኢትዮጵያ የረሃብ ታሪክ ማህደር ሰፍሮ እንደምናገኘው፥ ከ1131-1145፣ በ1258፣ በ1261፣ በ1262፣ በ1274 ረሃብና በሽታ ደርሶ ነበር። ሆኖም መንስኤዎቻቸው እንደ አየር ንብረት መዛባትና ሰው ሠራሽ ችግሮች ሳይሆን እንደ ፈጣሪ ቁጣና አንድም ሕዝቡ ለንጉሦች ባለመታዘዙ ወይም ንጉሦች የተሰጣቸውን መለኮታዊ አደራ ባለመወጣታቸው እንደተከሰተ ተደርጎ ሲጠቀስ ቆይቷል። ስለዚህም ጉዳይ የታሪክ ጸሐፍቱ ሲገልጹ፡-

"እግዚአብሔር የረሱትን መንግሥታት በበሽታ፣ በረሃብና በጦርነት ይቀጣል። እነዚህ መንግሥታት እውነተኛውን እምነትና የተቀደሱ ሕግጋቱን ትተው በሐሰት ስለሚበከሉ የጥፋትንና የእርግማንን መንገድ የሚከተሉ ናቸው" ይሏቸዋል። በተለይም ከ1315-1344 በነበረው የአጼ አምደጽዮን ዘመን መንግሥት እጅግ አስከፊ ድርቅና ረሃብ እንደነበር ይነገራል። ይህንንም የድርቅ ዘመን አቡነ አሮን የተባሉ በቤጌምድር የነበሩ ቅዱስ ሰው፤ በአምደ ጽዮንና በሰይፈ አርአድ ዘመነ መንግሥት በተከሰተው ድርቅ፣ ረሃብና በሽታ በመላው ኢትዮጵያ ተስፋፍቶ እንደነበር ያወሳሉ። ያኔ ከአቡነ አሮን ተማሪዎች ብቻ 1400 ሞተው ቤተክርስቲያኗን ሞልተዋት ነበር።

የደብረ ቢዛን (ትግራይ) ገዳም መነኩሴ የነበሩት አባ ዮሐንስ (በኮንቲሮዝ ግምት ከ1369-1448) ባለው ጊዜ ድርቅ በገዳሙ እንደተከሰተና የገዳሙን መነኮሳት እንደጨረሳቸው ጠቅሰዋል። በ15ኛው ክፍለ ዘመን የደረሰውን የረሃብ እልቂት በተመለከተ የተጠናከረ መረጃ ባይኖርም አል-ማግሪቢ የተባለ የአረብ ታሪክ መዝጋቢ፣ በአጼ ዘርአያቆብ ዘመነ መንግሥት (1434-1568) በተለይም ከ1434-6 በነበረው ጊዜ ረሃብ ብዙ ሕዝብ እንደ ፈጀና በመላው ሀገሪቱ የሕዝብን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እንደቀነሰ ዘግቧል።

ከ1508-1540 በነበረው የአጼ ልብነድንግል ዘመን መንግሥትም በዝናብ እጥረት ምክንያት በርካታ ሰዎች አልቀዋል። ከአጼ ልብነድንግል በኋላም በተለይም በአጼ ገላውዲዮስ ዘመነ መንግሥት (1540-1569) ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ ቸነፈር ደርሶ ነበር። በ1611 ማንንትታ፣ በ1683 ለባብል፣ በ1693 ታናካ የተባሉ በሽታዎች ብዙ ሕዝብ ጨርሰዋል። በአጼ እያሱ ዘመን መንግሥት በተለይም በ1706 የደረሰው ረሃብ፣ የጎንደርን ሕዝብ ከዚህ መቅሰፍት አድነን በማለት ንጉሡ ነገሥቱን እንዲማጸን አድርጎታል። ከዚህም በተጨማሪ በ1747 እና በ1748 በተከታታይ አንበጣ ሰማዩን እንደ ጉም ይሸፍነው እንደነበርና ይኸም ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአንበጣ መንጋ የቆላውንና የደጋውን ሕዝብ ለረሃብ እንዳጋለጠው እንዲሁም ለጉንፋንና ለሌሎችም ብዙ በሽታዎች በመዳረግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ ከምድረ ገጽ እንዳጠፋ ይታወቃል።

ከ1772/73 በነበረው ዘመን ቀጭኔ የሚባል ረሃብ እንደገባ፣ ከ1750-1769 በምጽዋ በተለይም በሐርቂቆ የተከሰተው ረሃብ ወደ ሌላው የሀገሪቱ ክፍል የተስፋፋ ሲሆን ከዚያም ከ1788/89 መላውን ክልል አዳርሶ፣ በ1796 ብዙ ወረዳዎችን አጥፍቷል። በ1842 ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረው ቻርልስ ጆንሰን የተባለ እንግሊዛዊ ሐኪም እንደገለጸው፤ ከ1828-29 በሸዋ ውስጥ አሰቃቂ ድርቅና ረሃብ ደርሷል። በዚህም ጊዜ ጆይ ኤል ክራፍ የተባለ ሚሲዮናዊ፣ ረሃቡ የወሎን ሕዝብ እንደቅጠል አርግፎ እንደጨረሰው ዘግቧል። በ1889 በሸዋ፣ በሱማሌ፣ በከፋና በጅማ - በጥቅምት፣ በኅዳር፣ በግንቦት ብዙ ሰዎችንና ከብቶችን ገድሏል።

ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ቀደም ሲል የተጠቀሰውን "ዘ ሂስትሪ ኦቭ ፋሚን ኤንድ ኤፒደሚክ ኢን ኢትዮጵያ ፕራየር ቱ ዘ ትዌንቲዝ ሴንቸሪ" በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፍ በርካታ የታሪክ መጻሕፍት አጣቅሰው ሲያቀርቡ፣ ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም ደግሞ ከዚያ ቀጥሎ ያለውን የረሃብ ዘመን «ሩላር ቮልነረብሊቲ ቱ ፋሚን ኢን ኢትዮጵያ» በሚል ርእስ በሳተሙት መጽሐፋቸው በዝርዝር አቅርበውታል። በመግቢያቸው ላይ ስለረሃብ ምንነት ሲገልጹም፡-"ረሃብ የተመሠቃቀለ ትዕይንትን ይፈጥራል። የሕመም ስቃይ ዝቅተኛ መሆንን፣ ተስፋ መቁረጥንና በአንደበት የማይገለጥ ነገር ግን አጥንት በአጥንት ከሆነ ፊት የሚነበብ ውስጣዊ ብስጭትን ያስከትላል።

ረሃብ ለመሞት የብዙ ወራት ጉዞ የሚደረግበት ነው። ረሃብ የሚታይ ጭንቀት፣ ሰቆቃና ፍርሃት ነው። ከሰዎች መካከል የታደሉት አይተውት ይሆናል። ግን ሞት አፋፍ ላይ ያለው ወይም ከእውነተኛው ሞት ጋር ፊት ለፊት የተጋፈጠው በእውን የሚያየውን ያህል አይሆንም። የረሃብን ያህል ሰው በሰው ላይ የሚፈጽመውን ኢ-ሰብዓዊነት የሚያጋልጥ የለም። የባሕልና የሃይማኖት ዋጋ ግብዝነትና መመጻደቅ እንደሆነ የሚያሳይም ረሃብ ነው። ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት አልበኝነት የሚፈጥርም ረሃብ ነው።

"... ያለፉትን በመቶ የሚቆጠሩ የረሃብ ዓመታት በትዝታ ዓይን እያየን እንለፋቸው እንዳንል ትግራይ ላይ በ1958 ተከስቷል። በዚያን ጊዜ ረሃቡን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳያውቀው ይፈለግ ስለነበር ለቤተክርስቲያንም ይሁን ለመስጊድ ማደሻ፣ ለመንገድም ይሁን ለትምህርት ቤት ማሰሪያ ብቻ ለምን እንደሆነ ለማያውቀው ጉዳይ ግን መዋጮ እንዲያዋጣ ተጠየቀ። ረሃቡ በገባ በሶስተኛ ዓመቱም በ1961 ላይ የአሜሪካ መንግሥት 7.5 ቶን እህል ሲረዳ መቶ ሺህ ያህል ሕዝብ አልቆ ነበር። " ይላሉ።

ረሃብ ሲከሰት በሽታም ይከተላል። ያኔ ፈንጣጣ፣ ተስቦ፣ ክፉኝ፣ ወባ እና ሌሎችም በሽታዎች ምህረት የለሽ ክንዳቸውን ያሳዩበትና ሕዝብ እንደ ቅጠል የረገፈበት ጊዜ ነበር። ድርቁ በአንድ አካባቢ ብቻ አልረጋም። ወደ ሰሜን ወሎ በተለይም ወደ ዋግና ላስታ ተዛምቶ ሕዝቡን በጭካኔ ረፍርፎታል። ይህ ረሃብ ከሰሜን ወደ ማዕከላዊ ሀገር ተዛመተ። ተመሳሳይ እልቂትም ፈጽሞ ወደ ደቡብ ሸዋ ሽምጥ ሸለቀ፣ ሐረርጌ፣ ሲዳማ፣ ጋሞጎፋ፣ ኢሉባቦር፣ ወለጋ፣ ጎጃም ተስፋፋ።

በ1975/77 ደግሞ በድርቅ ተጠቅተው የማያውቁት አርጆ፣ ባህርዳር፣ ደብረ ታቦር፣ ጨቦና ጉራጌ፣ ሳይቀሩ በረሃብ አለንጋ ተገረፉ። ምንም እንኳን የአጼ ኃይለሥላሴ መንግሥት ረሃቡ በኢትዮጵያ ሕዝብና በዓለም ሕዝብ እንዳይታወቅ ለማፈን ቢፈልግም የሚቻል አልሆነም። በ121 አውራጃዎች 6,478,760 ማለትም በማዕከላዊ ግምት በየአውራጃው 53,543 ሰዎች ድርቁ ባስከተለው ረሃብ አልቀዋል። በዚህም ስሌት መሠረት፣ በ20 ዓመት ውስጥ የረሃብ ሰለባ የሆነው ሕዝብ 25,111,887 ይደርሳል። የመንግሥት መረጃ ደግሞ በ63 አውራጃዎች 263,578 እንደሆነ ያመለክታል። ይህስ ቢሆን በወቅቱ ደራሽ አጥቶ ታፍኖ ማለቅ ነበረበት?

ከአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በፊት በነበሩ መንግሥታት በፈጣሪ ቁጣ ወይም ነገሥታቱን ባለመታዘዝ ወይም በጥጋብ እንደተከሰተ ተደርጎ ሲወሰድ፣ ለአጼ ኃይለሥላሴ መንግሥት ደግሞ መንኮታኮቻ ምክንያት እንደሆነ ይታወቃል። ነገሩ "አንበሳን ፈርተው ዛፍ ላይ ቢወጡ ነብር ጠበቃቸው" እንደሚባለው ሆነ እንጂ የዚያን ሥርዓት ፈላጭ ቆራጭነት ባህርይም የበለጠ ጉልህ አድርጎታል።

ድርቅና ረሃብን በተመለከተ ገና በብዛት መጠናትና መጻፍ ያለበት ቢሆንም ከጤና አኳያ ከተነተኑት መካከል አብርሃ ግዛው የተባሉ ምሁር «ኤኮሎጂ ኦፍ ሄልዝ ኤንድ ዲዝዝ ኢን ኢትዮጵያ» በሚል ርእስ ዜይን አሕመድ ዜን እና ሄልሙት ኩልስ ባዘጋጁት መጽሐፍ (1988) ላይ እንዳሰፈሩት፤ ምንም እንኳን ከአብዮቱ በኋላ የርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ረሃብ ከመድረሱ በፊት የቅድሚያ ጥንቃቄ አገልግሎት እንዲሰጥ ጭምር ቢመሠረትም ረሃቡ እየተባበሰ እንጂ እየተሻሻለ ሲሄድ አልታየም።

እንዲያውም በወሎና በትግራይ የተከሰተው ዓይነት ረሃብ፣ በ1977 በአጋዴንና በባሌ በተለይ በኤልካሬ፣ በኢሊባቦር፣ በተለይም በቡኖ በደሌ፣ በሰሜን ሸዋ ተስፋፋ። በ1979 ላይም ከፍተኛ ምርት በማምረት በምትታወቀው በአርሲ፣ በደቡብ ሸዋ፣ በሲዳሞ፣ በጋሞጎፋ ታየ። በ1981 ምሥራቅ ጎንደር በድርቅ ተመታ። የድርቁ ጥቃት አይሎ በቀጠለበት በ1984 ላይ የደርግ መንግሥት ከወሎ 367,016፣ ከሸዋ 108,241፣ ከትግራይ 89,716፣ ከምሥራቅ ጎጃም 16.425፣ ከምስራቅ ጎንደር 6387፣ በአጠቃላይም 600 ሺ ሰፋሪዎችን፤ በወለጋ 253,282፣ በጎጃም 101,785፣ በኢሊባቦር 147,915፣ በከፋ 72830፣ እና በምዕራብ ጎንደር 6378፣ አሰፈረ። ይህ ግን ድርቁና ረሃቡ የሚያስከትሉትን ችግሮች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊያስቀር የሚችል ርምጃ አልነበረም።

በመሠረቱ የተፈጥሮ ሰለባ የሆነችው ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን በሳህል በረሃ ውስጥ የሚጠቃለሉት ሀገሮች በተለይም ሱዳን፣ ናይጄሪያ፣ ማሊ፣ ኡጋንዳ፣ ሞሪታንያና ሌሎችም ሀገሮች ጭምር ናቸው። አንድ የጣና በለስ ፕሮጀክት መጽሔት (1985 አትሙ) እንደገለጸው፤ "በነዚህ ሀገሮች በተለይም በ1977 የደረሰው ድርቅ ባስከተለው የረሃብ ቸነፈር በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ሰዎች ሞተዋል።

የችግሩ ስፋትና ያስከተለው አሰቃቂ ጉዳት መላውን ዓለም ያስደነገጠ፣ የበለጸጉ ሀገሮች እንዲህ ያለው ጥቃት ለሚደርስባቸው ሀገሮች የሚቻላቸውን ድጋፍ ሁሉ እንዲያደርጉ ያነሳሳና ሥር የሰደደውን ችግር በአንድ ጊዜ ለማስወገድ ባይቻልም እንኳን ቀስ በቀስ ለመቅረፍ ሃሳብ የቀረበበት፤ የአፈር መሸርሸር፣ የአየር መዛባት፣ የተፈጥሮ ሀብት በትክክል ለመጠቀም አለመቻል ቴክኖሎጂያዊና ኢንዱስትሪያዊ እንቅስቃሴ እንዲዘረጋ የታመነበት ጊዜ ሆነ" ይላል።

አሰፋ ወልደ ገብርኤል የተባሉ ምሑር፤ «ዘ ኢኮሎጂ ኦቭ ሔልዝ ኤንድ ዲዝዝ ኢን ኢትዮጵያ» በሚል ርእስ በጻፉት መጽሐፍ እንዳቀረቡት፤ ኢትዮጵያ የግብርና ሀገር ብትሆንም፣ ከሕዝቧ 86% የሚሆነው ገበሬ መሆኑ ቢረጋገጥም፣ ሀገሪቱ በማንኛውም ጊዜ ሊታረስ የሚችል 15.8 ሚሊዮን ሄክታር መሬት እንዳላት ቢታወቅም፣ 69 ሚሊዮን የቀንድ ከብት፣ 62 ሚሊዮን ዶሮ ቢኖራትም፣ እድገቷ ዝቅተኛ በመሆኑ እያንዳንዱ ሰው በቂ ምግብ አያገኝም።

ይህም የሆነው እርሻው የሚታረሰው ኋላቀር በሆነ ዘዴ በመሆኑ፣ በክምችት ወቅት በሚደርሰው ብክነት፣ በቂ የመጓጓዣ አገልግሎት ባለመኖሩ፣ ስለጤንነት ጉዳይ ትምህርት ባለመሰጠቱ፣ ስለ አመጋገብና ስለ ቤተሰብ ቁጠባ ባለማወቅ፣ በአንድ በልምድ በተመረጠ እህል ላይ የተመሠረተ አመጋገብ ጋር የሙጥኝ በማለት፣ በተላላፊ በሽታዎች መስፋፋት፣ ምግብ ለመግዛት አቅም በማጣትና ድርቅ በመኖሩ ነው። እንዲህ ያለውን ችግር ለማስወገድ ጥረት የተደረገ መሆኑን የሚጠቁሙ መረጃዎች ቢኖሩም ውጤቱ የሚያረጋግጠው ግን ለመፍትሔነት አለመብቃቱን ነው።

ይሁንና የኢትዮጵያ በተደጋጋሚ በድርቅ አደጋ የመጠቃት፣ ከዚህም የተነሳ ሕዝቧ ለረሃብና ለእርዛት የመጋለጡ ጉዳይ በርግጥ የማይፈታ እንቆቅልሽ ነው? ሁኔታዎች ከተመቻቹለት 85 በመቶ የሚሆነው ገበሬ፣ ራሱን ችሎ 15 በመቶ የሚሆነውን ሕዝብ መደገፍ ይሳነዋልን? ብለን መጠየቃችን አልቀረም። ነገሩ በጣም ውስብስብም ነው። በመሠረቱ ያለፈውንም ሆነ ያለውን ሥርዓት በየምክንያቱ እየኮነንን መኖር ብቻውን የትም አያደርሰንም።

ሥር የሰደደው ችግራችን የተከሰተው ደጋግሞ በሚያጠቃን ድርቅ ምክንያት ነው። የአስተራረስ ዘዴያችን በጣም ኋላ ቀር በመሆኑ ነው። በመሠረቱ የኢትዮጵያ የግብርና ኢኮኖሚ ደካማ በመሆኑ ሕዝቡ በተደጋጋሚ ለረሃብ ይጋለጣል፣ ሲባልም ሆነ የዕለት ምግቡ ከአማካዩ ዝቅተኛ ካሎሪ እንኳን ያነሰ ነው ሲባል የአንድ ዓመት ወይም የሶስት አራት ዓመታት ችግር ውጤት ሳይሆን ከዚያ በፊት የነበሩት ሃያና ሰላሳ ዓመታትንም የሚዳስስ ነው።

ሻሎም ! አሜን።

# ስፖርት





# ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ- ከታላቅ ስኬት ማግስት

**ብርሃን ፈይሳ**

ኢትዮጵያ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ በትውልድ ቅብብሎሽ በምታፈራቸው ከዋክብት አትሌቶቿ አማካኝነት ዓለም ‹‹የሯጮች ምድር›› ብሎ የክብር ካባ ደርቦላታል። ይሁን እንጂ አትሌቶቿ በዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ መድረኮች የነገሱትን ያህል ትልልቅ ዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ውድድሮችን በሯጮቹ ምድር ለማስተናገድ አልታደለችም።

የውድድሮቹ ደረጃ አከራካሪ መሆኑ እንዳለ ሆኖ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከሚዘጋጁት ዓመታዊ ‹‹የአበበ ቢቂላ ማራቶን›› እና ‹‹የጃን ሜዳ ኢንተርናሽናል ሀገር አቋራጭ ውድድር›› መኖራቸው ይታወቃል። ኢትዮጵያን የሚመጥን ገጽታዋንም በመገንባት ረገድ አንድ ውጤታማ ውድድር ግን በጀግናው አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ የተመሰረተው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ነው።

ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በሁሉም ረገድ እያደገ የመጣው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ከጊዜ ወደ ጊዜ ዐይነ ግቡ ሆኖ የተለያዩ ዓለም አቀፍ እውቅናዎችን ማግኘቱን ቀጥላል። በቅርቡም ለጎዳና ላይ ውድድሮች እውቅናና ደረጃ የሚሰጠው የዓለም አትሌቲክስ ደረጃ ውስጥ አስገብቶታል። ይህም በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ውድድር አድርጎታል።

የዓለም አትሌቲክስ በዓለም ላይ ለሚካሄዱ የጎዳና ላይ ውድድሮች የተለያዩ መመዘኛዎችን አስቀምጦ ‹‹ሌብል›› በሚል ይሰይማል። በዋናነት ኢሊት ሌብል፣ ጎልድ ሌብልና ፕላቲኒየም ሌብል የሚሉ ስያሜዎች እንደየውድድሮቹ ደረጃ ይሰጣል። ውድድሮች እነዚህን ደረጃና ስያሜዎች በሂደት ከማግኘታቸው በፊት ግን በደፈናው ‹‹ሌብል›› የሚል ስያሜና እውቅና ያገኛሉ። ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ያገኘውም ይህን ‹‹ሌብል›› የተሰኘ እውቅናና ደረጃ ነው።

የዓለም አትሌቲክስ እነዚህን እውቅናዎች ወይም ደረጃዎች ለመስጠት በዋናነት የውድድሩን አጠቃላይ ዝግጅትና ጥራት፣ ደህንነት፣ የተወዳዳሪዎች ልምድ፣ የሕዝብና የመንግሥት አካላት ድጋፍ፣ የአበረታች ንጥረ ነገሮችን ተጠቃሚነት ለማስቀረት በፋይናንስ ረገድ የሚደረግ ያላሳለሰ ጥረት ወዘተ እንደ መስፈርት ይጠቀሳሉ። የዓለም አትሌቲክስ ቀጣይ ደረጃና ስያሜዎችን ለመስጠት ደግሞ ከቴክኒክ ጋር የተያያዙ የተለያዩ መስፈርቶችን ይመለከታል፡፡

ዘመናትን ለተሻገረው የኢትዮጵያና አትሌቲክስ ጠንካራ ትስስር ታላቁ ሩጫ ያስመዘገበው ስኬት በቂ ባይባልም በዚህ ስኬቱ ማግስት በኢትዮጵያ ስፖርት ቱሪዝም ፈርቀዳጅ ሆኖ ዘንድሮ በዚሁ ህዳር ወር ለ24 ጊዜ ሊካሄድ ዝግጅቱን እያጠናቀቀ ይገኛል። መነሻና መድረሻውን በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ ባደረገው የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ 10 ኪሎ ሜትር ዓመታዊ ውድድር ዘንድሮ 50 ሺ ሰዎች የሚሳተፉበት ሲሆን፤ ይህም ከአፍሪካ ተሻግሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙ ቁጥር ያለው ህዝብ በማሳተፍ ከጥቂቶች መካከል አንዱ አድርጎታል።

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አሁን ላይ በርካታ ሺ ኢትዮጵያውያን የሚናፍቁት፣ ከተለያዩ የዓለም ሃገራት ዓመቱን ጠብቀው በመምጣት በህብረቀለም ያሸበረቀው ውድድር አካል ለመሆን የሚመኙት ሆኗል። ትልቅ ስም ካላቸው ኢትዮጵያውያን አትሌቶች አንስቶ የረጅም ርቀት ውድድሮች ከዋክብት የሆኑ የዩጋንዳ እና ኬንያ አትሌቶች የዚህ ታላቅ ውድድር ተፎካካሪ መሆናቸውም እየተለመደ መጥተል።

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ከጊዜው ጋር ራሱን ማዘመኑ እንዲሁም ጥራቱን እንደጠበቀ መቀጠሉ አሁን ላገኘው እውቅናና ደረጃ ዋነኛው ምክንያት ሆኗል። ከዚህ በኋላም ጥቂት ቀሪ መስፈርቶችን ካሟላ ወደቀጣዩ ደረጃ (ሌብል) ለመሸጋገር እንደማይከብደው የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ሥራ አስኪያጅ ዳግማዊት አማረ ገልፃለች፡፡



**ዳግማዊት አማረ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ሥራ አስኪያጅ፣**

እንደ ዳግማዊት ማብራሪያ፤ አስቀድሞም በዓለም አቀፍ የጎዳና ሩጫዎች ላይ ያሉ ልምዶችን በኢትዮጵያዊ መንገድ መተግበር ከመቻሉ ባለፈ ደረጃ ለማሟላት የተለየ ስራ ሲከናወን ለዚህ መብቃት ኩራት ነው። ከዚህ ዓመት አንስቶም ስፖርቱን የሚቆጣጠረው የዓለም አትሌቲክስ ከሚያስቀምጣቸው መስፈርቶች ውስጥ የሚቀሩትን ወደ ተግባር ለመቀየር በጋራ ይሰራል። በተለይም ዓለም አቀፍ የሚድያ ተደራሽነቱን ማሳደግ፣ የአየር ብክለትን ከመቀነስ አኳያ ያለውን ስራ ማጠናከር፣ በርካታ ታዋቂ አትሌቶች በውድድሩ የሚካፈሉ ቢሆኑም ከምሥራቅ አፍሪካ ባለፈ የሌሎች ሀገራትንም ማካተት፣… ትኩረት የሚደረግባቸው ናቸው። ከዚህም ጋር ተያይዞ ዓለም አቀፍ የአንድ ቀን ውድድሮችን ወደ ኢትዮጵያ ማምጣት የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ሌላኛው ግቡ ነው።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ድጋፍና ለዓለም አትሌቲክስ ግብረ መልስ መስጠቱም ለዚህ እንዳበቃው የጠቆመችው ሥራ አስኪያጇ፣ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ እዚህ ለመድረሱ ከራሱ ጥረት ባለፈ አብሯቸው የሚሰራቸው ባለድርሻ አካላትም ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ተናግራለች። በቀጣይም ከኢፌዴሪ ቱሪዝም ሚኒስትር ባለፈ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጋር በቅርበት የሚሰራ ይሆናል። በጋራ ተጋግዞ መስራት ከተቻለ በርካታ ለውጥ ሊመጣ ይችላል የሚል እምነትም አላት።

‹‹መሰል ታላላቅ ውድድሮችን ወቅቱን ጠብቆ ማካሄድ በርካታ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ቢኖሩትም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር በቅርበት መስራት መቻሉ ሁኔታዎችን አቅልሏል ። በመሆኑም በሩጫው የራሳቸውን ጠንካራ ሚና በመወጣት ላይ ላሉ አካላት ምስጋና ይገባቸዋል፡፡›› ብላለች።

ከቀናት በኋላ ህዳር 8/2017 ዓ.ም የሚካሄደው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ 10 ኪሎ ሜትር ውድድር 50ሺ ሰዎችን የሚያሳትፍ ሲሆን፤ በሁለት መነሻም ይካሄዳል። ይኸውም 10ሺ የሚሆኑት ፈጣን ሯጮች መነሻቸውን ከጊዮን ሆቴል የሚያደርጉ በመሆኑ ከ1ሰዓት በፊት ስፍራው ላይ መገኘት ይኖርባቸዋል። የተቀረው የመዝናኛ ሯጭ ደግሞ በተለመደው ስፍራ መነሻውን ያደርጋል።

ዘንድሮ በውድድሩ አሸናፊ የሚሆኑ አትሌቶች የሽልማት ገንዘብ መጠንም ጨምሯል፤ ለዚህም 1ነጥብ31 ሚሊዮን ብር ተዘጋጅቷል። ከኢትዮጵያዊያን ባለፈ የዩጋንዳና ኬንያ አትሌቶች እንደተለመደው በውድድሩ የሚካፈሉ ሲሆን፤ በቅርቡ በተካሄደው የቺካጎ ማራቶን የዓለም ክብረወሰንን ያሻሻለችው ኬንያዊቷ አትሌት ሩት ቼፕንገቲች በክብር እንግድነት ትገኛለች።

## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

የፍ/ባለመብት ዳንኀቴ የማሽኒያ ዕቃዎች ኃ/የተ/የግ/ማበር እና በፍ/ባለዕዳ ተጂቱ ኢንተርፕራይዝ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 91982 በ25/7/2015 ዓ.ም እና በመ/ቁ በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 5 ውስጥ የሚገኝ የተለያዩ የማሽነሪ እና የቀላል ተሽከርካሪ መለዋወጫ እቃዎች የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 4,633,075 (አራ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺ ሰባ አምስት ብር) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ታህሳስ 8 ቀን 2016 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል። የተጫራቾች ምዝገባ በ4፡30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል። የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ጀምሮ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ባለበት ቦታ ድረስ በመውሰድ መጎብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በንግድ ባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል። ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ C.P.O የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም። በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በፍ/አ/ዳ/ስም CPO አሰርተው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከፈተ አሰርቶ ሙሉ ገንዘቡን በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት የፍ/አዳያ ሬክቶሬት ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በሀራጅ ስለመሸጡ ለሚመለከተው አካል ማስረጃ ከመፃፍ ባለፈ ስም የማዞወር ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**

## የጨረታ ማስታወቂያ

በሰመራ ሎግያ ከተማ መስተዳድር በ2017 ዓ.ም በጀት አመት የግራኒፊኬሽን ስራ በያዘው በጀት መሰረት በዘርፉ ፍቃድ ያላቸውን አወዳድሮ ለማሰራት ይፈልጋል፡፡

ስለዚህ በጨረታው ለመወዳደር የምትፈልጉ ተጫራቾች ከዚህ በታች የተገለጹትን ነጥቦች በማሟላት መወዳር የምትችሉ ሲሆን፤-

1. ተጫራቾች ግዴታ ማሟላት ያለባቸው የቅድሚያ መወዳደሪያ መስፈርቶች ማለትም፡-

1.1.1. ከሚፈለገው አገልግሎት ጋር የተዛመደ የንግድ ስራ ፍቃድ ያለው፤

1.1.2. በዘርፉ በዘመኑ የታደሰ ንግድ ፍቃድ፤

1.1.3 የንግድ ፍቃድ ምዝገባ ሰርተፊኬት ያለው፤

1.1.4. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርትፊኬት ያለው፤

1.1.5. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ( TIN ) ሰርትፊኬት ያለው፤

1.1.6. የጨረታ ሰነድ ግዥ መፈጸም

1.1.7. በጨረታ ሰነድ ላይ በዝርዝር የተቀመጡትን መስፈርት የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

2. ተጫራቾች ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 15 ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት የሰመራ- ሎግያ ከተማ መስተዳድር ፋይ/ኢኮ/ ጽ/ቤት ውስጥ የግዥና ንብ/አስ/የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 105 የማይመለስ ብር 500.00/ ( አምስት መቶ ብር ) በመክፈል የጨረታ ሰነዱን መግዛት ትችላላችሁ፡፡

3. ተጫራቾች በእያንዳዱ በሚያቀርቡት የጨረታ ሰነዶች ላይ የተጫራቾች ወይም የህጋዊ ወኪል ፊርማና ማህተም ሊኖራቸው ይገባል፡፡

4. ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ከማንኛውም ተጫራቾች የሚቀርብን የውድድር ጥያቄ መ/ቤቱ አይቀበልም።

5. የጨረታው ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን 5/3/2017 ዓ.ም ጀምሮ ተከታታይ ባሉት 15 ቀናት የሚቆይ ሆኖ በ16ኛው ቀን ማለትም ህዳር 20/2017 ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ የጨረታ ሳጥን የሚዘጋ ሆኖ በእለቱ ከግማሽ ሰዓት በኋላ 4:30 በከንቲባው ፋይናንስ ጽ/ቤት የግዥና ንብ/አስ/የስራ ሂደት ክፍል ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በይፋ ይከፈታል፡፡

6. ቢሮው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

7. ለተጨማሪ መረጃ በቢሮችን በአካል በመቅረብ ወይም በቢሮ በስክ ቁጥር፡-033 666 0583 ደውሎው ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡

**በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰመራ-ሉግያ ከተማ መስ/ፋይናንስ ሲኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት**